

«ሕወሓት ሕዝብና ሠራዊቱ እንዳይታረቅ አድርጎ ነበር ያጣላው»

- ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ጤናው (ቻቻው) ወታደርና ደራሲ

ገጽ 6

ዓባይ እያንዳንዳችንን ነው

ገጽ 15


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

81ኛ ዓመት ቁጥር 204 መጋቢት 24 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# የብሔራዊ ምክክሩ አሳታፊነት የሚሳካው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሂደቱን መደገፍ ሲችል መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገለፁ



አዲስ አበባ፤ የብሔራዊ ምክክሩ አሳታፊነት የሚሳካው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በቀናነትና በባለቤትነት ሂደቱን መደገፍ ሲችል መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ገለፁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ባስተላለፉት መልዕክት አካታች ብሔራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ሒደቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መከናወን እንዳለበት ጠቁመዋል።

"ይኸም የሚሆነው ሁላችንም የምክክር ሂደቱን በበላይነት የሚመራውን የምክክር ኮሚሽን በተለያዩ መንገዶች መደገፍ፣ ማትጋትና ማጽናት ስንችል ነው" ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳብራሩትም ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት ታሪክ የሚቀይሩ ወርቃማ የለውጥ ዕድሎች ገጥመዋታል። ፖለቲካችንን አንድ ደረጃ ወደፊት የሚያስፈነጥሩና ቀጣይ ዘመናችንን ብሩህ የሚያደርጉ አያሌ የለውጥ ችቦዎች ተለኩሰዋል። እነዚያ ለውጦች የሚያመሳስላቸው አንድ ነገር አለ፤ ቁጭት። በቁጭት ተጠንስሰው፣ በቁጭት ተካሂደው፣ በቁጭት ይጠናቀቃሉ።

የብሔራዊ ምክክሩ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ‹‹የትኛውም ፈተና ከለውጥ ጉዞ ሊያስቆም እንደማይችል ትምህርት ወስደንበታል››

- አቶ ሞገስ ባልቻ
የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የትኛውም ፈተና ከለውጥ ጉዞ ሊያስቆም እንደማይችል ከተመዘገቡ ስኬቶችና ካጋጠሙ ተግዳሮቶች ትምህርት ወስደንበታል ሲሉ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር ገለጹ፡፡

በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ዘርፍ ኃላፊ ሚኒስትር አቶ ሞገስ ባልቻ እንዳመለከቱት፤ አገር ከማፍረስ የጠላት እንቅስቃሴ አንስቶ እስከ ተፈጥሮአዊ ፈተናና በተለያየ መንገድ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች ሲታዩ ለውጡ የትኛውም አይነት ፈተና እንዳላቆመው ያመላከተ ነው። የኢትዮጵያ ብልጽግና የኢትዮጵያውያን ቀጣይ መልካም ዕጣ ፈንታ አስተማማኝ መሆኑን በፈተና ውስጥ አልፎ ውጤት ሊመጣ የሚችል መሆኑም ትምህርት የተወሰደበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ባለፉት አራት ዓመታት የለውጥ ጉዞ የገጠሙንን ፈተናዎች አልፈን ተሻግረናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ፈተናዎቹ ቀላል የማይባል መስዋዕትነትና ዋጋ ማስከፋላቸውን፣ ነገር ግን አገር ከመበተንና የባሰ ችግር ውስጥ እንዳትገባ



በማድረግ መታደግ ተችሏል ሲሉ ጠቁመዋል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድ ላይ ከቆመ የትኛውንም አይነት ፈተና ማለፍ እንደሚቻል እንዲሁም በኅብረት መቆም ትልቅ አቅም መሆኑን ትምህርት ተወስዶበታል ብለዋል። የኔ ብቻ የሚል ያለፈው ጊዜ ችግር የትም እንደማያደርስ ለፖለቲከኞችም ሆነ ለገዢው ፓርቲ ትምህርት መስጠቱንም አክለው ገልጸዋል፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ የዴሞክራሲን ምህዳር በማስፋት ሠላማዊ የፖለቲካ ትግል እንዲኖር መደረጉን፤ በዚህም ከአገር ውጭ የነበሩ ፖለቲከኞች ወደ አገር ቤት እንዲገቡ መደረጉን ጠቅሰዋል። ከዚህም ባሻገር በማረሚያና እስር ቤት የነበሩ ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች መፈታታቸው፤ አሳሪ የነበሩ ሕጎች እንዲሻሻሉ መደረጉ፣ የተገለሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ከአጋርነት ወደ አንድነት መጥተው አገርን ማጠናከር የሚያስችል ሥራ መሠራቱ፤ እንደ ምርጫ ቦርድ፣ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የመሳሰሉ የዴሞክራሲ ተቋማት ግንባታ፤ የአሠራር ነጻነት መኖር፤ የጸጥታና ደህንነት እንዲሁም የፍትሕ ተቋማት ሪፎርም ለውጡ ያስገኛቸው ትሩፋቶች መሆናቸውን አቶ ሞገስ ገልጸዋል። ለየት ያለ የፖለቲካ ባህል የታየበትና ኢትዮጵያ አሸናፊ የሆነችበት ምርጫ በ2013 ዓ.ም እንዲሁ ለውጡ ያስገኘው ስኬት እንደሆነም ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ፤ ምንም እንኳን በኢኮኖሚው፣ በማኅበራዊ ሆነ በፖለቲካ እንዲሁም በዲፕሎማሲው

‹‹የትኛውም ፈተና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ‹‹መንግሥት የህዳሴ ግድብን ከዳር ለማድረስ የሄደበት ርቀት ውጤታማ ነው››

-ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት በህዳሴ ግድብ ላይ የገጠሙ የቴክኒክ ችግሮችን በመሻገርና በዲፕሎማሲው መስክ የነበሩ ተግዳሮቶችን በማለፍ የግድቡን ግንባታ ከዳር ለማድረስ የሄደበት ርቀት ውጤታማ ነው ሲሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩና የዓባይ ውሃ ጉዳይ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ ገለጹ። ግድቡን ከፍፃሜ ለማድረስም የሕዝብና የመንግሥት

‹‹መንግሥት የህዳሴ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል






ዜና



በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በከር ሻሌ (ዶ/ር)

# ሚኒስቴሩ የሳውዲ ዓረቢያ ተመላሾችን ለማቋቋም የተለያዩ ስልጠናዎች ማዘጋጀቱን አስታወቀ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከሳዑዲ ዓረቢያ ተመላሾችን ለማቋቋም የሚረዱ የተለያዩ የሙያ ስልጠናዎች ማዘጋጀቱን አመለከተ።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ በከር ሻሌ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣በአሁኑ ጊዜ ከሳዑዲ ዓረቢያ እየተመለሱ ያሉ ዜጎቻችችን ለማቋቋም ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ አገር አቀፍ ግብረ ኃይል መቋቋሙን ገልጸው፣ ተመላሾቹም በቀጣይ እንዲቋቋሙና መደበኛ ሕይወታቸውን መምራት እንዲችሉ አጋዥ የሆኑ የሙያ ስልጠናዎች መዘጋጀታቸውን አመልክተዋል።

መንግሥት በአገር ደረጃ ከሳዑዲ ወደ 100ሺህ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ለመመለስ እንዳቀደ ቀደም ሲል ይፋ ማድረጉን ያወሱት ዶ/ር በከር፣ ሚኒስቴሩ ሁሉንም ተመላሾች እንደየፍላጎታቸው ለማሰልጠን በቂ ዝግጅት ማድረጉን ገልጸዋል።

ለተመላሾቹ ለጊዜው የተዘጋጁት ስልጠናዎች አጫጭር መሆናቸውን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው በቀጣይ የረጅም ጊዜ ስልጠና ለመስጠት መታቀዱንም ተናግረዋል። ተመላሾቹ ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተውጣጡ በመሆናቸው በአንድ ማዕከል ወይም በአንድ አካባቢ ማሰልጠን ስለማይመች በአካባቢያቸው ሆነው ስልጠናውን እንዲወስዱ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን አስታውቀዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የተመላሾችን ፍላጎት ባማከለ መልኩ ተደራጅተው በመሥራት ውጤታማ የሚደርጓቸውን ክህሎቶች ለማስጨበጥ ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርግ ጠቅሰዋል።

ወደ ውጭ አገር ሄደው ለመሥራት ፍላጎት ላላቸው ተመላሾችም በዋናነት የስነልቦና ዝግጅት ስልጠና ለመስጠት መታቀዱን ሚኒስትር ዴኤታው ጠቁመው፣ በሚሄዱበት አገር በስራቸው ውጤታማ እንዲሆኑም የሙያና የቋንቋ ክህሎት ስልጠና መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲልም በሕጋዊ መንገድ ውጭ አገር ሄደው መሥራት ለሚፈልጉ ሰዎች በተለይ በቤተሰብ እንክብካቤና የቤት ውስጥ አገልግሎት ስልጠና ሲሰጥ መቆየቱን አስታውሰው፣ አሁንም በሙያው ስልጠና ለሚፈልጉ ተመላሾች ምቹ ሁኔታዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

በሳዑዲ ዓረቢያ በዜጎች ላይ በርካታ እስርና እንግልት ሲደርስ ቆይቷል። ይህ ጉዳይ ያሳሰበው የኢትዮጵያ መንግሥትም ከሳዑዲ ዓረቢያ ባለስልጣናት ጋር በመነጋገር ዜጎቹን ወደ አገር የመመለስ ሂደት ጀምሯል። አሁን ላይ ከ1ሺ200 በላይ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ቀሪዎቹ በቀጣይ ቀናት የሚመለሱ ይሆናል።

# ‹‹አገራዊ ምክክሩ አገርን በማስቀጠል ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው››

- ባሻ ዳምጠው ገብረሕይወት የቀድሞ ሠራዊት አባል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ምክክሩ አገርን በማስቀጠል ረገድ ጠቀሜታው የጎላ ነው ሲሉ የቀድሞ ሠራዊት አባሉ ባሻ ዳምጠው ገብረሕይወት ገለጹ።

ባሻ ዳምጠው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አገራዊ ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ ሁሉም ኃላፊነቱን መወጣት አለበት።

ምክክሩ አገርን ለማስቀጠል ጥሩ መሆኑን በማመን የሚደግፉት መሆኑን የገለጹት ባሻ ዳምጠው አገርን በሚያቀናና በሚያስቀጥል መልኩ ተግባራዊ እንዲደረግ ርብርብ ሊደረግ እንደሚገባውም ገልጸዋል።

እንደ ባሻ ዳምጠው ገለፃ፤ አገራዊ ምክክሩን ስኬታማ ለማድረግና አገራዊ አንድነትን ባስጠበቀ መልኩ ለመከወን እንዲቻል ሁሉም ኃላፊነቱን መወጣት አለበት።

አገርን የማስቀጠል ሥራውን በሚያደናቅፉና አገራዊ ምክክሩ እንዳይከናወን በሚያደርጉ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃ መወሰድ እንዳለበት የጠቆሙት ባሻ ኅብረተሰቡም አገር እስካለች ድረስ ብቻ እንደሚኖር አውቆ ለምክክሩ ተፈፃሚነት የድርሻውን መወጣት እንዳለበትም ገልፀዋል።

አገራዊ ምክክሩን ስኬታማ ለማድረግ መንግሥት ውስጡ ሆነው አገር የሚበጠብጡትን ሥርዓት ማስያዝ



(ፎቶ በበላይ አሰፋቸው)

አለበት ያሉት ባሻ ዳምጠው፤ መንግሥት ምክክሩ ተግባራዊ እንዳይደረግ የሚያደርጉ አካላትን አደብ ማስገዛት ይገባዋል ሲሉም ገልጸዋል።

በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሆነው የሕዝብና መንግሥታቸውን ፍላጎት የማያሟሉ ትክክለኛ አገራዊ ስሜት የሌላቸው ሥርዓተ አልበኞች አደብ ሊገዙ እንደሚገባቸው የጠቆሙት ባሻ፤ መሰል ሰዎች ለራሱ ለመንግሥትም አደጋ ስለሚሆኑ ሊገሰፁና ከድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባቸውም ገልጸዋል።

ምክክሩ አገራዊ ወገናዊ ስሜት ኖሯቸው የጎደለውን በመሙላት ኃላፊነት በሚሰማቸው ሰዎች ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል ያሉት ባሻ ዳምጠው፤ ሁሉን አሳታፊ እንዲሆንም የጠነከረ ሥራ ሊሠራ እንደሚገባውም ተናግረዋል።

ለአገራዊ ምክክሩ ተፈፃሚነት ከቀበሌ ጀምሮ ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ የጠቆሙት ባሻ ዳምጠው፤ ቀበሌ መፈታት ያቃተው ችግር ወረዳ ላይ ወረዳ ያልተፈታውም ዞን በዞን አካባቢ ለተከሰተ ችግርም ክልሎች በመፍታትና በተዋረድ ኮስተር ያለ እርምጃም እየተወሰደ ለተፈፃሚነቱ ጥብቅና መቆም እንደሚሻም ገልጸዋል።

ባሻ ዳምጠው ገብረሕይወት የቀድሞ ሠራዊት ባልደረባ ሲሆኑ ከ1956 እስከ 1982 ድረስ በውትድርና አገራቸውን ሲያገለግሉ የነበሩ ናቸው።

# እየጣለ ያለውን የበልግ ዝናብ በአግባቡ ለግብርና ሥራ መጠቀም እንደሚገባ ተጠቆመ

**ስምስም መንግሥቱ**

አዲስ አበባ፤ የበልግ ዝናብ አብዛኛውን የአገሪቱን አካባቢዎች የሸፈነ መሆኑና መዘናጋት ሳይኖር የተገኘውን እርጥበት በመያዝ በአግባቡ ለግብርና ሥራ ማዋል እንደሚጠበቅ ብሔራዊ ሚትዮሮሎጂ ኤጀንሲ አስታወቀ።

የብሔራዊ ሚትዮሮሎጂ ኤጀንሲ ምክትል ዳይሬክተር አቶ ክንፈ ኃይለማርያም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ የዘንድሮ የበልግ ወቅት ዘግይቶ የጀመረ ቢሆንም፣የዝናብ ስርጭቱ አብዛኛውን የአገሪቱን አካባቢዎች የሸፈነ መሆኑን የኤጀንሲው ትንበያዎች ያመለክታሉ።

ቀሪው የበልግ ወቅት አልፎ አልፎ ዝናብ ቢኖረውም ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና የተቆራረጠ ሊሆን እንደሚችልም ተተንብየዋል። መዘናጋት ሳይኖር በመረጃው የተገኘውን እርጥበት በመያዝ በአግባቡ ለግብርና ሥራው መጠቀም ያስፈልጋል።

በተሰጠው ትንበያ መሰረት ደቡብና ደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ከመደበኛው ያደላ የዝናብ መጠን እንደሚያገኙ መተንበዩንና በሰሜን ምሥራቅ የበልግ ተጠቃሚዎችም ወደ መደበኛ የተጠጋ ዝናብ እንደሚያገኙ አቶ ክንፈ ጠቁመው፣በምዕራብ አጋማሽ ደግሞ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ በትንበያው



ማረጋገጥ መቻሉን አመልክተዋል።

በየአስር ቀኑ፣የወቅት አጋማሽ ላይ እና በአጭር ጊዜ ደግሞ በየ24 ሰዓት ኤጀንሲው የራሱን ድረ ገጽ ጨምሮ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች ወቅታዊውን መረጃ በማሰራጨት የግብርና ሥራውን በማገዝ ኃላፊነቱን ይወጣል ብለዋል።

ከኤጀንሲው የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የበልግ ወቅት የሚባለው ከየካቲት እስከ ግንቦት ወራቶች ያሉት ጊዜያቶች ናቸው። በእነዚህ ወቅቶች በአንዳንድ የኢትዮጵያ ክፍሎች በተለይም በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የበልግ ዝናብ የሚያገኙበት ዋነኛው ወቅታቸው ነው።

# ‹‹መንግሥት የህዳሴ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ጠቁመዋል።

ባለፉት ዓመታት የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ እንዲስተጓጎልና እንዳይቀጥል በዓለማቀፉ ማኅበረሰብ የተለያዩ ጫናዎችና መሰናክሎች ሲፈጠሩ መቆየታቸውን ያወሱት ፕሮፌሰር ያዕቆብ፤ በተቃራኒው በመንግሥት በኩል ከውጭም ሆነ ከውስጥ የሚመጡ ጫናዎችንና መሰናክሎችን በብልሃት ለማለፍ የተደረገው ጥረት ውጤት አምጥቶ የመጀመሪያው ተርባይን ኃይል ለማመንጨት በቅቷል።

መንግሥት የግንባታውን ሥራ ለደቂቃም ቢሆን ባለመቋረጥና በቁርጠኝነት በመገንባት እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በመሥራትና ሲያስፈልገም ውይይቶችንና ድርድሮችን በማድረግ በግድቡ ላይ የተጋረጡ ተግዳሮቶችን ማለፍ መቻሉን ፕሮፌሰር ያዕቆብ ገልጸዋል።

ፈተናዎቹን በመቋቋም ኃይል እስከ ማመንጨት የደረሰ ስኬት የተሄደባቸው ርቀቶች በሁለት ዋና ዋና ተግባራት እንደሚጠቃለሉ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አብራርተዋል።

በአንደኝነት ግድቡን ያለ እረፍት አንድም ቀን ሳይስተጓጎል በመሥራትና የትኛውንም ቀን ያለ ሥራ ባለማሳለፍ የተሄደበት መንገድ እንዲሁም ግብፅና ሱዳን እንዲሁም ሌሎች ታዛቢዎች ባሉበት መድረክ ሁሉ እውነታውን በማስረጃ በማስደገፍ የሄደችበት መንገድ ኢትዮጵያን ባለ ድል እንዳደረጓት ፕሮፌሰር ያዕቆብ ተናግረዋል።

ባለፉት ዓመታት የህዳሴውን ግድብ በተመለከተ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ዓለም ውጤታማ የሚባል ወቅት ማሳለፏን የገለጹት ፕሮፌሰር ያዕቆብ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ መለስተኛ ክርክር በማካሄድና ዲፕሎማሲያዊ ትግል በማድረግ የአገሪቱን ክብር አስጠብቆ መዝለቁን ጠቁመዋል።

ፕሮፌሰር ያዕቆብ በግድቡ ዙሪያ ያለው የሕዝብ ትኩረትና ፍላጎት እንዲሁም የግንባታ ሥራው መቀጠሉ ቀሪውን የ16 በመቶ ግንባታ ለማጠናቀቅ እንደሚያስችልና ከዘንድሮ ሙሌት ጋር ተደማምሮም በቀጣይ ሁለትና ሶስት ዓመታት ሙሉ በሙሉ ኃይል ማመንጨት ይችላል የሚል ተስፋ እንዳላቸውም ገልጸዋል።

ግንባታው ከተጀመረ 11 ዓመታትን ያስቆጠረው ታላቁ የህዳሴው ግድብ ግንባታው ከአፍሪካ ትልቁ የኃይል ማመንጫ ግድብ ሲሆን ግድቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ባሳለፍነው የካቲት ወር 375 ሜጋባይት ኃይል ማመንጨቱ ይታወሳል።

ዜና

# አገራዊ ለውጡ መልካም ውጤቶች የታዩበት ቢሆንም ቀሪ ሥራዎች እንዳሉበት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተናገሩ

**ውብሸት ሰንደቁ**



አቶ ያየህ አሥማረ



አቶ የሸዋስ አሠፋ



አቶ ሲሳይ ኃይለማርያም

አዲስ አበባ፡- አገራዊ ለውጡ መልካም ውጤቶች የታዩበት ቢሆንም በርካታ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉበት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ገለፁ፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በለውጡ ዙሪያ ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ ፓርቲ (ኢዜማ)፣ ራዕይ ፓርቲ እና እናት ፓርቲ አገራዊ ለውጡ መልካም ውጤቶች የታዩበት ቢሆንም ብዙ ቀሪ ሥራዎች እንዳሉበት ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማበራዊ ፍትሕ ፓርቲ ሊቀመንበር (ኢዜማ) አቶ የሸዋስ አሠፋ በለውጡ የታዩ ጠንካራ ጎን ያሏቸውን ነጥቦች አንስተዋል።

አቶ የሸዋስ ለውጡ በብዙ መስዋዕትነት የመጣ እንደሆነና የለውጡ ባለቤት ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን ተናግረው የመጀመሪያ ወራት የተዘጉ ሚዲያዎች መከፈታቸው፣ በተወሰነ ደረጃ ምርጫ ቦርድን፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንን የመሳሰሉ ተቋማት ሪፎርም ለማድረግ መሞከራቸው በአወንታ የሚታይ ነው ብለዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተስፋ ሰጪ በርካታ ንግግሮች በመልካም የሚነሱ መሆናቸውንም አክለዋል፡፡በአንፃሩ ቃል የተገቡ ነገሮች በትክክል እየተፈፀሙ አለመሆናቸው በለውጡ ከታዩ ደካማ ጎኖች ውስጥ የሚካተት ነው ብለዋል፡፡

መሠረታዊ ለውጥ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች በሪፎርም ስም ተድበስብሰው ባሉበት እንዲቀጥሉ መደረጋቸው የለውጡ ድክመት ነው ብለው በጥቅሉ አስቀምጠዋል።

የዜጎች ደህንነት ጉዳይ ላይ ብዙ አልተሠራበትም ያሉት ሊቀመንበሩ አንድ ዜጋ ተዘዋውሮ የመሥራትና ወጥቶ የመግባት መብቱ አደጋ ውስጥ መግባቱን አንስተዋል።

አቶ የሸዋስ የተቋማት ነፃነት ላይ ጥሩ ሥራዎች ቢሠሩም ከዚህ በላይ ነፃ ማድረግ ይቻል ነበር ባይ ናቸው። ለማሳያም ሚዲያዎች በስንት ትግል ነፃ የወጡ ቢሆንም አሁን አሁን ወደ ቀድሞው የመመለስ አዝማሚያ ውስጥ ገብተዋል ብለዋል።

የውጪ ተፅዕኖ፣ የፓርቲዎችና የሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚጋሩት ችግር እንዳለ ሆኖ ሕወሓት የፈጠረው ችግር በታሰበው ፍጥነት አለመፈታቱን እንደ ጉድለት እንደሚያዩት ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም አሠቃቂ የሆኑና እንግዳ የሆኑ ግድያዎች መታየታቸው አገራዊ ለውጡ ላይ የተከሰቱ ድክመቶች አድርገን እናያቸዋለን ብለዋል።

ሌላው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የራዕይ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ሲላይ ኃይለማርያም ረዳ ባለፉት ዓመታት የታዩ ብዙ አወንታዊ የሆኑ ለውጦች እንዳሉና ለውጡ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ዜጎችን ማንም እንደልቡ ወስዶ የሚገርፋቸውና የሚደበድባቸው ጊዜ ላይ አይደለንም ያሉት አቶ ሲላይ የዜጎች እስራት በተለይም ከዚህ በፊት ሰዎችን ቶርች የማድረግ እና ሌሎች ነገሮች መቅረታቸውን በአወንታ አንስተዋል፡፡

እንደ አብነት የራዕይ ፓርቲ መቋቋምን በማንሳት ሕወሓት ሥልጣን ላይ ቢኖር ራዕይ ፓርቲ መፈጠር እንደማይችል ገልጸው አሁን ላይ በፖለቲካ አመለካከት የሚያሳድድ ኃይል አለመኖሩ በበጎ እንደሚመለከቱት ገልጠዋል፡፡

እርስ በርስ የማጨራረስ ሴራዎችና ኢትዮጵያን እንዲበትኑ የተተከሉ ብዙ ደማሚቶች በሚታይ መልኩ መክሸፍ መቻላቸው እንደ አንድ ትልቅ ጸጋ የሚወሰድ ነው ብለውታል፡፡

አቶ ሲላይ አሁን ያለው ሕገ መንግሥት ኢትዮጵያን የሚከፋፍል እንጂ አንድ የሚያደርግ ባለመሆኑ ይህ በሂደት እንደሚስተካከል ተሥፋ እንዳላቸው ገልጸው መንግሥት ሕወሓት ላይ ከመጀመሪያው ጀምሮ እስካሁን የሚወስደው እርምጃ ብዙም የሚያረካ እንዳልሆነ ይናገራሉ። አክለውም ሕወሓት ቢጠፋ ኖሮ ይህ በየቦታው ያለው ችግር ይጠፋል የሚል እምነት አለኝ ይላሉ።

ሕወሓት መጥፋት እንዳለበትና ካልጠፋ አገሪቱ ልትበለፅግ ስለማትችል እዚህ ላይ ጠንከር ያለ እርምጃ መወሰድ ይገባዋል ሲሉ ይመክራሉ፡፡

የእናት ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ያየህ አሥማረ በበኩላቸው ኢትዮጵያ የሚለው ስም ተዘንግቶ እንደነበርና ሥሙን በታላላቅ መሪዎች ጭምር ከፍ ለማድረግ የተሄደበት ርቀት እንዲሁም ደብዝዞ የነበረው የኢትዮጵያዊነት ስሜት እንዲመጣ የተደረገበትን ጥረት እናደንቃለን ብለዋል፡፡

በሚዲያዎች ላይ የነበረው አፈና ከሞላ ጎደል ለቀቅ ማለቱ፣ የግል ሚዲያዎች ፈቃድ አግኝተው እንዲሠሩ ሕዝቡ የተለያየ የመረጃ አማራጭ እንዲኖረው መደረጉ እንዲሁም ምርጫ ቦርድን ጨምሮ አንዳንድ ተቋማት በተወሰነ መልኩ ገለልተኛ ሆነው እንዲቋቋሙ መደረጉ በጥሩ መልኩ የሚነሱ ነገሮች መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

የብሔር አባዜ እስካሁን ድረስ አለመልቀቁ ግን ድክመት ነው ብለውታል አቶ ያየህ። ለዚህም ማሳያ ሰዎች በማንነታቸው ምክንያት ያለማቋረጥ ለተከታታይ አራት ዓመታት እየሞቱ፣ ንብረታቸው እየተዘረፈ እና እየተፈናቀሉ መሆናቸው ሁላችንንም አንገት ያስደፋ የታሪክ ምዕራፍ ነው ሲሉ ገልፀውታል፡፡

አገሪቱ ላይ ያለው የሰላምና የመረጋጋት ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መሆኑ፣ በኢኮኖሚው ረገድ በየጊዜው ዕለት በዕለት የዋጋ ግሽበትና መናር መከሰቱ እንዲሁም ከተፈጥሮም ከሰው ሰራሽ አደጋ ጋር ተዳምሮ የመጣው ኑሮ ውድነት ዜጎች ላይ ፈተና መጋረጡን በለውጡ የታዩ ድክመቶች ናቸው ብለዋል፡፡

# መንግሥት ዜጎችን ከሳዑዲ የማጓጓዝ ሥራ ከጀመረበት ቀን አንስቶ 3 ሺህ የሚጠጉ ስደተኞችን መመለሱን አስታወቀ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ዜጎችን ከሳዑዲ የማጓጓዝ ሥራ ከጀመረበት ቀን አንስቶ 3 ሺህ የሚጠጉ ስደተኞችን መመለሱን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዴኤታ አምባሳደር ብርቱካን አያኖ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ በሳምንት 9 በረራዎችን በማድረግ በእቅዳችን መሠረት እየሄድን ነው። ዜጎችን ከሳውዲ የማጓጓዝ ሥራ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ከ2 ሺህ 800 በላይ ዜጎችን መመለስ ተችሏል። በአንድ በረራ 4 መቶ 80 ዜጎች እንዲሳፈሩ በማድረግ የማጓጓዝ ሥራው ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በትናንትናው ዕለት በሳውዲ ዓረቢያ በተለያዩ እሥር ቤቶች ውስጥ ታስረው በስቃይና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን መካከል ከሪያድና ከጂዳ በጥቅሉ በሶስት በረራዎች 1 ሺህ 173 ዜጎችን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡



ፎቶ፡-እዮብ ተፈራ

« በአቀድነው መሠረት ወደ አገር ውስጥ መግባት ያለባቸውን ዜጎቻችን በተገቢው ሁኔታ እየገቡ ነው። ዜጎችን ከየትኛውም አገር ተቀብሎ የማስተናገድ ኃላፊነት የመንግሥት በመሆኑ ተቀብሎ የሥራ እድል የሚፈጠርበትን ሁኔታ እያመቻቸ ነው» ብለዋል።

ከሳዑዲ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ቆይተው ወደ አገራቸው የተመለሱ ኢትዮጵያውያንን መልሶ የማቋቋም ሥራ በትኩረት እንደሚሠራ ተናግረዋል። በሚኒስቴሩ አስተባባሪነት የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተካተቱበት ብሔራዊ ኮሚቴ ከስደት ተመላሾችን ለማቋቋም የተለያዩ ሥራዎች እየሠራ መሆኑንም ገልፀዋል።

ተመላሾችን የመቀበሉ ሥራ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ መሆኑን የገለጹት አምባሳደሯ፤ ከሳዑዲ ከመጡ በኋላ አንድ ቀን አርፈው ወደ መጡበት ክልል እየተመለሱ ነው። ክልሎችም ስደተኞችን ለመቀበል እየተዘጋጁ ነው፤ በተለይ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሶስት መጠለያ ጣቢያዎችን አዘጋጅቶ ለመቀበል በዝግጅት ላይ ነው ብለዋል፡፡

ችግሩን በዘላቂነት ለመከላከል የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ ያሉት አምባሳደሯ፤ ሕገወጥ የሰው አዘዋዋሪዎችን በመቆጣጠርና ለሕግ በማቅረብ፣ በአገር ውስጥ ገፊ የሆኑ ምክንያቶች እንዲቀንሱ በማድረግና በሀገር ውስጥ የስራ ፈጠራን በማጠናከር ሕገወጥ ስደተኝነትን ለመቀነስ መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ አንጋዮ ኦዳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የደቡብ ክልል ከስደት ተመላሾችን ተቀብሎ ወደ ሥራ ለማስገባት እስከ ወረዳዎች ድረስ በተቀናጀ መልኩ እየሠራ ነው። የመጠለያ ጣቢያዎችን በማዘጋጀትና ከዛም ወደየመጡበት ቦታ የመመለስ ሥራ እየተሠራ ነው።

እንደ አምባሳደር ብርቱካን ገለጻ ከስደት ተመላሾቹ ከጭንቀት እንዲወጡ የማድረግ ሥራ ይሠራል፤ በቋሚነት በአገራቸው ሠርተው እንዲበለጽጉ ከሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር ሰፊ ሥራ ይከናወናል ።

ዜና

# ኢትዮጵያ ከቡና ኤክስፖርት ለመጀመሪያ ጊዜ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ለማግኘት እየሠራች ነው

**በግርማቸው ጋሻው**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በስድስት ወራት ብቻ ከ137ሺ. ቶን ቡና ወደ ውጭ ልካ ከ645ሚሊዮን ዶላር በላይ ያገኘች ሲሆን ይህ አካሄድ በቀጣዮቹ ወራት ይህንን አጠናክሮ በማስቀጠል ከዘርፉ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት እየሠራች መሆኑ ተገለፀ።

የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ግዛት ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ኢትዮጵያ ባለፉት ሰባት ወራት 162,818.04 ቶን ቡና ወደ ውጭ በመላክ 645.10 ሚሊዮን ዶላር ያገኘች ሲሆን ይህ አፈጻጸምም ከቀደመው ጋር ሲወዳደር ከፍተኛ እመርታን አሳይቷል፡፡

አቶ ግዛት እንዳብራሩትም ለቡና ኤክስፖርት መጨመር ዓይነተኛ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው ብራዚልን ያጋጠማት ተከታታይነት ያለው ድርቅ እና የአረቢካ ቡና አብቃይ አካባቢዎች ሳኦ ፓውሎ እና ሚናስ ጌሬስ ባለፈው ዓመት ለሦስት ተከታታይ ቀናት በውርጭ መመታታቸውና ከፉኛ መጎዳታቸው ነው።

ይህን ተከትሎ በዓለም አቀፍ ገበያ መቅረብ የነበረበት ቡና በ24 ሚሊዮን ከረጢት ቅናሽ አሳይቷል።



የቡና አቅርቦት እጥረትን ተከትሎ እ.አ.አ በግንቦት 2019 ዝቀተኛ የቡና ዋጋ 0 ነጥብ 87 ዶላር በፓውንድ የነበረ ሲሆን፣ በየካቲት 2022 ዋጋው በሦስት እጥፍ ጨምሮ ወደ 2ነጥብ 60 ዶላር ከፍ ብሏል። ለዋጋ ጭማሪው ምክንያት የሆነው የቡና ምርት አቅርቦት በዓለም አቀፍ ገበያ መቀነሱ እንደሆነ አቶ ግዛት አብራርተዋል።

በዓለም አቀፍ ገበያ የቡና ፍላጎት መጨመርን ከግምት ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ የምታቀርበው ቡና በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣቱን የተናገሩት አቶ ግዛት፣ አገሪቱ ባለፉት ስምንት ወራት 740 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ገቢ ልታገኝ መቻሏን ተናግረዋል።

«በእርግጠኝነት ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ስድስት ወራት ውስጥ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች ተብሎ ይጠበቃል። በአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ቢኖር ደግሞ ከቡና ዘርፍ ብቻ 1ነጥብ 67 ቢሊዮን ዶላር ይገኝ ነበር» ብለዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ የይርጋጨፌ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ በብዛት ከሚፈለጉት ቡናዎች መካከል አንዱ ሲሆን ጉጅ፣ ሲዳማ እና አዲስ መጤዎቹ ነንሰቦ በተመሳሳይ የደንበኞችን ቀልብ የሚስቡ ሆነዋል። ቡና ተመራጭ የሚያደርገው ጣዕሙ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ ላኪዎች የቡና ምርቶችን በደንብ የሚያስተዋውቁ ከሆነ የኢትዮጵያ ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊነቱ ይጨምራል። አንዳንድ ጥረቶች ቢኖሩም የኢትዮጵያ ቡናን ብራንዲንግ በማድረግ ረገድ ብዙ ይቀረናል ሲሉም አክለዋል።

በ1969 የተመሠረተው የኢትዮጵያ ቡና ላኪዎች ማኅበር ባለፉት ዓመታት የኢትዮጵያን ቡና በዓለም አቀፍ ገበያ ለማስተዋወቅ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። ማኅበሩ የኢትዮጵያ ቡናን በዓለም አቀፍ ገበያ ከማስተዋወቅ ባለፈ የአገሪቱን ገጽታ ለመገንባት የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል።

# በአዲስ አበባ 50ሚሊዮን ኪሎ ግራም የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ተከማችተዋል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተደረገ ጥናት ወደ 50 ሚሊዮን ኪሎግራም የሚጠጋ የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ክምችት መኖሩ ተገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የአሌክትሪካል እና ኮምፒውተር ኢንጂነሪንግ ኮሌጅ መምህርና የኤሌትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ማስወገጃ ጥናት አጥኝ ቡድን መሪ ዶክተር ፈጠነ ሙሉጌታ እንደገለጹት፣ በመዲናችን በተደረገው የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ክምችት እያደገ መጥቷል።

በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት ስር የተቋቋመው የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ማስወገጃ ጥናት አጥኝ ቡድን ባደረገው ጥናትም በመዲናዋ ወደ 50 ሚሊዮን ኪሎግራም የሚጠጋ የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ክምችት መኖሩን ዶክተር ፈጠነ ገልጸዋል፡፡

ተረፈ ምርቶቹም በአግባቡና በጥናት በተደገፈ መንገድ መወገድ መቻል አለባቸውም ብለዋል፡፡ይህ ካልሆነ ደግሞ ለጤና ጠንቅ እንደሚሆኑ ዶክተር ፈጠነ ተናግረዋል።

በመሥሪያ ቤቶችና በየአካባቢው ተከማችተው የሚገኙት ኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች በተገቢው ሁኔታ ካልተወገዱ ለአካባቢ ብክለት ይዳርጋሉ። ለጤና ጠንቅ ይሆናሉ። የአካባቢን ምርትና ምርታማነትን ይቀንሳሉ። የአካባቢ አየር ንብረት ለውጥን ያስከትላሉ። የተለያዩ ጉዳቶችን በሰዎች ሕይወት ላይ ያደርሳሉ ብለዋል፡፡

በየተቋማቶች የሚገኙት የተለያዩ ኤሌክትሮኒካል እቃዎች አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ መወገድ ባለባቸው መንገድ በማስወገድ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት መቀነስ ከመቻሉም በላይ ተረፈ ምርቶቹን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡



የኤሌክትሪካል ዕቃ ተረፈ ምርቶች በውስጣቸው ባለው የተለያዩ ይዘቶች ለሰው፣ ለአካባቢ፣ ለከርሰ ምድር ውሃ ብክለትና ጉዳት ያደርሳሉ ያሉት ዶክተር ፈጠነ፣ ተረፈ ምርቶቹ በሁሉም ላይ ሰፊ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ሁሉም በየአካባቢውና ተቋሙ ኃላፊነቱን በመወጣት ሊያስወገዳቸው እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች ማስወገጃ ጥናት አጥኝ ቡድን አባልና መምህር አቶ ነብዩ ዮናስ እንደተናገሩት፣ በመዲናችን የኤሌክትሮኒካል እቃዎች የተረፈ ምርት ክምችት በየዓመቱ በአምስት በመቶ እየጨመረ እንደሚሄድ በጥናት ተረጋግጠዋል ብለዋል፡፡

የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶች በተገቢውና በተቀናጀ መንገድ ካልተወገዱ ፣ የአካባቢ ብክለት ያመጣሉ፣ አየር ሁኔታ መዛባትና ሙቀት መጨመር መንስኤ ይሆናሉ፣ ምርትና ምርታማነት ይቀንሳሉ፣ የንጹህ ውሃ መጠጥ በመበከል የነዋሪዎችን ጤና መጓደል ያስከትላሉ ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኤሌክትሮኒካል እቃ ተረፈ ምርቶቹ ማስወገድ ካልቻልን እራሳችንንና ማኅበረሰባችንን እንጎዳለን ያሉት አቶ ነብዩ ፣ ለመታደግ የበኩላችንን ድርሻ ልናበረክት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በመዲናችን ብቻ ሳይሆን በአገር ደረጃም የአወጋገድ መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ አሠራሮችን መተግበር መቻል አለበት ሲሉ አቶ ነብዩ ተናግረዋል፡፡

# ‹‹የትኛውም ፈተና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መስከ በለውጡ ስኬት ማምጣት የተቻለ ቢሆንም፤ እልህ አስጨራሽ የሆነ ተግዳሮትም እንደነበር ጠቅሰዋል። ለውጡን ለመቀልበስ የዜጎች መፈናቀል፣ ሞትና መሰል ችግሮች በጥፋት ኃይሎች በተለይም በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን መፈጸሙን አንስተዋል። መደበኛ ያልሆኑ አደረጃጀቶችና የጽንፈኝነት አመለካከትም ለውጡን ለመቀልበስ ትልቅ ተግዳሮት እንደነበር ገልጸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ ምክንያት የተከሰተው የኑሮ ውድነትን እንዲሁም በአግባቡ ያልተመራው የንግድ ሥርዓት ፈታኝ ከሚባሉ ተግዳሮቶች ውስጥ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

እንደ አቶ ሞገስ ገለጻ፤ በፈተናና ስኬት ታጅቦ የመጣው ለውጥ ኢትዮጵያ ያላት አቅምና የማደግ ተስፋዋና እድሏ ሰፊ መሆኑ የታየበት ነው። በተለይም ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ የተሠሩ ፕሮጀክቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ማለቃቸውና የአካባቢን ገጽታ መቀየር መቻላቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ትልቅ ቦታ ላይ መድረስ እንደምትችል ማሳያ ነው።

እንደ ኃላፊ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ዋናው የለውጡ ባለቤት ሕዝቡ እንደሆነ ጠቅሰው፤ በቀጣይ ፍጥነት የታከለበት ውጤት ለማምጣት እንደሚሠራ ተናግረዋል። የተገኘውን ልምድ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ለሰላም እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ ላይ በመሥራት ሠላምን ማጠናከር፣ አገራዊ ተግባቦትን መፍጠር በሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ በሰከነ መልኩ መወያየት፣ የልማት ሥራዎችን ጠንክሮ በመሥራት አገርን መቀየር መንግሥት በተለየ ሁኔታ ካስቀመጣቸው ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋና ምርቶችን በአገር ውስጥ አቅም መሸፈን ቀጣይ ከታሰቡት የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ መሆናቸውን አንስተዋል። ወጣቶች በትምህርት ተቀርጸውና በቴክኖሎጂ ተደግፈው መጪው የኢትዮጵያ ባለቤቶች እንዲሆኑ በአዕምሮና በሥነ ምግባር በማነጽ ብቁ እንዲሆኑ የማድረግ ሥራም ትኩረት ይደረግበታል ብለዋል፡፡

## የብሔራዊ ምክክሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አብዛኛውን ጊዜ የለውጥ ምዕራፎች በሚጀምሩበት ወቅት የምንሰንቃቸው የለውጥ ሐሳቦች ዳር ከመድረሳቸው በፊት ሲኮሰምኑ በተደጋጋሚ አይተናል። በለውጥ በሂደት ወቅት ግባችንን ለማሳካት ከመተባበር ይልቅ በጥቃቅን ጉዳዮች እርስ በእርስ መጓተቱን ስለምናስቀድም በመጀመሪያ ያስጎመጅ የነበረው የለውጥ ፍሬ በመንገዱ መሐል ተጨናግፎ ይቀራሉ። መጨናገፉቸውን ልብ የምንለው ዘግይተን በመሆኑ ዕድሎቹ ካለፉ በኋላ እንደ አገር መልሰን እንቆጭባቸዋለን።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለው እንዳሉትም እኛ የቀደመውን ትውልድ "ይሄንና ያንን ቢያደርግ ኖሮ" እያልን እንደምንወቅሰው ሁሉ፣ የቀደመው ትውልድም ከእሱ በፊት የነበረውን ትውልድ ሲኮንን ነበር። ከዚህ የታሪክ አዙሪት ለመውጣት እስካልወሰንን ድረስ ነገ የእኛም ዕጣ ካለፈው የተለየ አይሆንም። ዛሬ በቸልታ የምናልፋቸው አጋጣሚዎች ተደምረው ነገ ላይ የልጅ ልጆቻችን እኛን የሚወቅሱበት ምክንያት ይሆናል። ይህ እንዳይሆን ዛሬ እጃችን ላይ የሚገኙ የለውጥ ዕድሎችን ሁሉ አሟጥጠን ለመጠቀም መረባረብ አለብን።

ለዘመናት እየተንከባለሉ ዛሬ ላይ የደረሱ የፖለቲካ ፈተናዎቻችንን በጉልህ መቅረፍ የሚያስችለንና መጻዒ ዘመናችንን አዲስ መሠረት ላይ የማቆም አቅም ያለው ብሔራዊ የምክክር ሂደት ዛሬ በእጃችን ላይ ያለ ወርቃማ ዕድል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህን ወርቅ የሆነ አጋጣሚ የስንት ልፋት እና የስንት ታሪክ ሂደት ውጤት መሆኑን ዘንግተን እንደ ጠጠር ከቆጠርነው በቀላሉ ልናጣው እንችላለን። በተቃራኒው እንደ ዕንቁ አክብረንና ተንከባክበን ከተጠቀምንበት ዋጋው ከፍ ያለና ታሪክ ቀያሪ ዕድል ይሆናል። ልጆቻችንም "አባቶቻችን እንዲህ በማድረጋቸው አገራችን እዚህ ከፍታ ላይ ደረሰች" ብለው የሚያመሰግኑበትን አጋጣሚ ይፈጥራል።

አካታች ብሔራዊ ምክክሩ ስኬታማ እንዲሆን ሒደቱ ተቀባይነት ያለው ሆኖ መከናወን አለበት። ይኸም የሚሆነው ሁላችንም የምክክር ሂደቱን በበላይነት የሚመራውን የምክክር ኮሚሽን በተለያዩ መንገዶች መደገፍ፣ ማትጋትና ማጽናት ስንችል ነው። በዚህ ጉዳይ ዳር ቆሞ መገኘት በታሪክ ፊት የሚያስወቅስ ተግባር ነው። ሁሉም አካል በባለቤትነት ስሜት ለምክክር ሂደቱ አስተዋፅዖ በማድረግ ተሳትፎውን ያረጋግጣል እንጂ አንዱ ጋባዥ ሌላው ተጋባዥ እንደሆነ አድርጎ መቁጠር ከታሪክ ተጠያቂነት ነጻ አያደርግም።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳረጋገጡትም በመንግሥት በኩል እስከ ታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ድረስ የተቋቋመው የምክክር ኮሚሽን በቅልጥፍና መሥራት እንዲችል አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ከማድረግ ወደ ኋላ አይልም። የክልል መስተዳደሮች ቀናነት፣ ባለቤትነትና ታሪካዊ ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ለኮሚሽኑ ሥራ አስፈላጊ የሆነውን ግብዓት በማቅረብ ለሥራው ምቹ ሁኔታ ሊፈጥሩ ይገባል። ተፎካካሪ ፓርቲዎች በውይይቱ እንደሚሳተፉ ብቻ ሳይሆን እንደ ሂደቱ ባለቤት ለሂደቱ ቅልጥፍናና ስኬት አስፈላጊውን ሁሉ እንድታደርጉ በትኅትና እጠይቃለሁ ብለዋል።

ዶክተር አቢይ በመልዕክታቸውም የተለያዩ አካላት ለአገራዊ ምክክሩ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ጥሪ አቅርበዋል፤፤

ምሁራን ኮሚሽኑ አስተያየትና ምክረ ሐሳባችሁን በሚፈልግበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ ተነሳሽነት፤ የሂደቱ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የታሪካዊ ጉዟችን እና የዘመን አሻራችን ለሆነው ምክክር አስተዋፆዋችሁ የላቀ እንዲሆን እማጸናለሁ። የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች አገር ስምምነትን በምትፈልግበት በዚህ ወቅት አማካይ ሆናችሁ ሁሉን የማስማማት አደራ አለባችሁና የመቀራረቢያውን መድረክ በማገዝ አገራዊ ግዴታችሁን እንድትወጡ ከልብ በመነጨ ትኅትና እጠይቃለሁ።

የሁሉም ኃላፊትነት ተደምሮ የሚወድቀው በአገርና በሕዝብ ትከሻ ላይ ነው። ሁላችንም ልዩነቶቻችንን አቻችለን በኃላፊነት ስሜት መንቀሳቀስ አለብን። ሕዝብ ያላከበረው እና ሕዝብ ያልደገፈው እንቅስቃሴ ውጤቱ መና ነውና መላ ኢትዮጵያውያን ድጋፋችሁ፣ ተሳትፏችሁ፣ክብራችሁና ጸሎታችሁ ከኮሚሽኑ እንዳይለይ ከታላቅ አክብሮት ጋር እጠይቃለሁ ብለዋል።

የቀደሚ መጽሄት

# አገልግል



## «ሕወሓት ሕዝብና ሠራዊቱ እንዳይታረቅ አድርጎ ነበር ያጣሳው»

\- ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ጤናው (ቻቻው)
ወታደርና ደራሲ

ገጽ 6



## ‹‹ወጣቱ በህልምና በራዕይ መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል››

\- አቶ ዳዊት ሀይሉ

ገጽ 13



## የኩላሊትና አእምሮ ጤናን የሚጠብቁ ተፈጥሯዊ ምግቦች

ገጽ 8

የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን
HOUSING DEVELOPMENT CORPORATION

ከአ.አ ከተማ አስተዳደር ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቅድሚያ ክፍያና የማስተላለፊያ መጠን

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን በእጅጉ ከሚገዳደራቸው ዐበይት ችግሮች መካከል የመኖሪያ ቤት እጥረት አንዱ ነው። የከተማ አስተዳደሩም ይህን የኅብረተሰቡን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ በዘላቂነት ለመፍታትና ችግሩን ለመቅረፍ እንዲሁም የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ከዘረጋቸው የልማት ሜጋ ፕሮጀክቶች አንዱ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በተለያዩ ፕሮግራሞች አካቶ በመሥራት ቤቶቹን ለችግሩ ገፈት ቀማሾች ማስተላለፍ ከጀመረ ከአስርት ዓመታት በላይ ተቆጥሯል።

ይሁንና ከተለያዩ አካባቢዎች እየፈለሰ ወደ ከተማዋ በአራቱም አቅጣጫ የሚገባው የህብረተሰብ ክፍል ከጊዜ ወደ ጊዜ በእጅጉ እየጨመረ በመምጣቱ እና በልማት ከሚነሱ ነዋሪዎች ጋር ተያይዞ የከተማዋ ነዋሪዎችን የቤት ፍላጎት ዕርካታ መፍጠር ባለመቻሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታው በስፋት ቀጥሏል።

በዚህም በተሠራው ሰፊ ሥራ ለመምህራን የተሰጠውን አምስት ሺ ቤቶችን ጨምሮ በ10/90፣ በ20/80 እና በ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤቶች መርሐ-ግብር እስካሁን በጥቅሉ 256 ሺ 251 ቤቶችን የአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ሠርቶ በማጠናቀቅ ለባለ እድለኞች በማስረከብ ከአንድ ሚሊዮን 281 ሺ በላይ እማወራዎችን እና አባወራዎችን የቤት ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓል።

ኮርፖሬሽኑ በ10/90፣ በ20/80፣ በ40/60 እንዲሁም የኪራይ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ኅብረተሰቡ በአገሩ ላይ የኔ የሚለው መኖሪያ ቤት እንዲኖረው ያስቻለ ሲሆን፣ ከዚህ አኳያ የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቅድሚያ ክፍያና የማስተላለፊያ መጠን በተመለከተ የአከፋፈል ስርዓቱ ምን እንደሚመስል ከኮርፖሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት ጋር እንደሚከተለው ቆይታ አድርገናል።

**የጋራ መኖሪያ ቤቶች የቅድሚያ ክፍያ መጠን**

የቅድሚያ ክፍያ አከፋፈል ስርዓት ዝቅተኛው ቤት ገዢ ውል ከመፈረሙ በፊት የሚከፍለው ከቤቱ ጠቅላላ የማስተላለፊያ ዋጋ፡-

1. ለ10/90 የቤት ልማት ፕሮግራም 10 በመቶ ቅድመ ክፍያ፤
2. ለ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ለመኖሪያ 20 በመቶ ቅድመ ክፍያ፤
3. ለ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ለመኖሪያ 40 በመቶ ቅድመ ክፍያ፤
4. ለ20/80 እና 40/60 ንግድ ቤቶች 50 በመቶ ቅድመ ክፍያ የሚከፈል ሲሆን፣ እንደአስፈላጊነቱ ቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል፡፡
5. ለሌሎች የቤት ልማት ፕሮግራሞች በየወቅቱ በቦርድ የሚወሰን ይሆናል፡፡
6. የኪራይ ቤቶች ተመንን በተመለከተ ስቱዲዮ 350፣ ባለ1 መኝታ 671፣ እና ባለ2 መኝታ 851 ተመን እንደሚከፍሉ በቦርዱ ተወስኖ ተግባር ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡

**የቀሪ ክፍያና የችሮታ ጊዜ**

የቤቱን ማስተላለፊያ ዋጋ በተከፋፈለ ተከታታይ የረጅም ጊዜ ክፍያ ለመክፈል የብድር ውል ከተዋዋለበት ቀን በኋላ በባንክ የተሰጠው የችሮታ ጊዜ ከሚያበቃበት ቀን የሚቀጥለውን የስራ ቀን መነሻ በማድረግ በሚከተለው የጊዜ ወሰን መሠረት ይከፈላል፡-

1. ለ20/80 የቤት ልማት ፕሮግራም ለመኖሪያና ንግድ ቤት

| ዙር | እጣው የወጣበት ቀን | የቤት አይነት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ስቱዲዮ | ባለ አንድ መኝታ | ባለ ሁለት መኝታ | ባለ ሦስት መኝታ |
| 1ኛ | መስከረም 25/1998 | 665 | 665 | 950 | 1110 |
| 2ኛ | ሐምሌ 4/1999 | 665 | 665 | 950 | 1110 |
| 3ኛ | የካቲት 20/2000 | 665 | 665 | 950 | 1110 |
| 4ኛ | መስከረም 24/2001 | 1100 | 1414 | 1728 | 1807 |
| 5ኛ | ሚያዝያ20/2002 | 1450 | 1865 | 2280 | 2385 |
| 6ኛ | የካቲት 2/2003 | 1450 | 1865 | 2280 | 2385 |
| 7ኛ | ነሐሴ 19/2004 | 1481 | 1931 | 2523 | 2633 |
| 8ኛ | መጋቢት11/2005 | 1869 | 2491 | 3426 | 3581 |
| 9ኛ | ሚያዚያ 2/2005 | 1869 | 2491 | 4394 | 3581 |
| 10ኛ | መጋቢት 24/ 2007 | 2483 | 3438 | 4394 | 4776 |
| 11ኛ | ሐምሌ 30/ 2008 | 2483 | 3438 | 4394 | 4776 |
| 12ኛ | ሰኔ 2 / 2010 | 2483 | 3438 | 4394 | 4776 |
| 13ኛ | የካቲት 27 /2011 | 4511.27 | 4511.27 | 4511.27 | 4511.27 |

1.1. ለ10/90ና ለ20/80 ከስቱዲዮ እስከባለ ሶስት መኝታ ከ10-20 ዓመት፤

1.2. ለንግድ ቤት 5 ዓመት ይሆናል፡፡

2. ለ40/60 የቤት ልማት ፕሮግራም ለመኖሪያና ንግድ ቤት

2.1. 40/60 ከ10 -12 ዓመት

2.2. ለንግድ ቤት 5 ዓመት ይሆናል፡፡

የጋራ መኖሪያ ቤቶች የማስተላለፊያ ክፍያ መጠን

እስካሁን በተላለፉ ከ1ኛ እስከ 13ኛ ዙር የ20/80 የጋራ መኖሪያ ቤቶች የማስተላለፊያ የአንድ ካሬ ክፍያ መጠን እንደሚከተለው በሰንጠረዡ ላይ ሰፍሯል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# «ሕወሓት ሕዝብና ሠራዊቱ እንዳይታረቅ አድርጎ ነበር ያጣላው»

-ሃምሳ አለቃ ጋሻዬ ጤናው (ቻቻው)
ወታደርና ደራሲ

ማህሌት አብዱል

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን ወታደርና ደራሲ ወጣት ነው። የተወለደው ምሥራቅ ጎጃም ዞን ሞጣ ውሃ ገልጥ ቀበሌ ውስጥ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ውሃ ገልጥ እና አውጃ በተባሉ ትምህርት ቤቶች ተከታትሏል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በሞጣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተማረው። ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ተመድቦ በግብርና ትምህርት ክፍል በእንስሳት እርባታ ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። ይሁንና በተመረቀበት የትምህርት ዘርፍ ሥራ ማግኘት ባለመቻሉ መከላከያ ሚኒስቴር ባወጣው ማስታወቂያ ተወዳድሮ በማለፍ ሠራዊቱን ተቀላቀለ። ላለፉት 11 ዓመታት በእግረኛ ክፍል ውስጥ ተመድቦ አገሩን በማገልገል ላይ ይገኛል። ከዚሁ ጎን ለጎን የሥነ-ጽሑፍ ተሰጥኦውን በማሳደግ አንድ የግጥም መድብልና አንድ ልብ ወለድ መጽሐፎችን ለንባብ አብቅቷል። በሕወሓት ሠራዊት ጥቃት የደረሰበትን የሰሜን ዕዝ ግፍ የሚያትተውን €€የተከዳው የሰሜን ዕዝ« የተሰኘውን አዲሱን መጽሐፍ ደግሞ በዛሬው ዕለት በይፋ ያስመርቃል። በዚህ መጽሐፍና በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከመጽሐፉ ደራሲ ሃምሳአለቃ ጋሻዬ ጤናው ጋር ቆይታ አድርገናል። እንደሚከተለው ይቀርባል።**



ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

**አዲስ ዘመን፡- ሠራዊቱን የተቀላቀልክበትን አጋጣሚ አስታውሰንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**ሃምሳለቃ ጋሻዬ፡-** ገና የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለሁም አየር ኃይል ባወጣው ማስታወቂያ ተወዳድሬ በአብራሪነት ለመሰልጠን አልፌ ነበር። ግን ልጅነት ስለነበር ይከብደኛል በሚል ስጋት በሙያው ሳልቀጥል ቀረሁ። ከዩኒቨርሲቲ በተመረቅሁበት ወቅት ደግሞ በተማርኩበት ዘርፍ ሥራ አልነበረም። እንደአጋጣሚ መከላከያ ማስታወቂያ ሲያወጣ እኔ እንደአንድ የሙያ ዘርፍ ቆጥሬው ነው የተወዳደርኩት። ያም ቢሆን ሙያውን እወደው ነበር፤ በሂደት ደግሞ ለተቋሙም ሆነ ለሙያው ያለኝ ፍቅር እየጨመረ መጣ። በመሠረቱ እኔ ግብርና ትምህርት ክፍል የገባሁት በፍላጎቴ አልነበረም። ትምህርቱንም እስከምጨርሰው ድረስ ደስተኛ አልነበርኩም ነበር። በተለይ ለሥነ-ጽሑፍ ከፍተኛ ፍቅር ስለነበረኝ ሶሻል ትምህርት ዘርፍ ውስጥ የመግባት ፍላጎት ነበረኝ። በወቅቱ እንዲያውም በርካታ ግጥሞችና መጣጥፎችን እፅፍ ነበር። የሚገርምሽ የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ ጀምሮ ነው የመፃፍ ክህሎቴ እያደገ የመጣው። የምፅፋቸውን ግጥሞች የወላጆች ቀን ሲከበር በማንበብ ከፍተኛ እውቅና እና ሽልማት አግኝቼ ነበር። ዩኒቨርሲቲ ከገባሁም በኋላ በሥነጽሑፍ ክበብ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ከሚያደርጉ ተማሪዎች አንዱ ነበርኩ። የምማረው ግብርና ቢሆንም ሙሉ ትኩረቴን አደርግ የነበረው በኪነ-ጥበባዊ ሥራዎች ላይ ስለነበር እኔ ብቻ ሳልሆን መላው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያለመከሊትህ ነው የምትማረው ይሉኝ ነበር። ሠራዊቱንም ከተቀላቀልኩኝ በኋላ በርካታ ጽሑፎችን ጽፌያለሁ፤ መሠረታዊ የጋዜጠኝነት ስልጠና ወስጄ የመከላከያ ሪፖርተር ሆኜ ሠርቻለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ታዲያ ተሰጥኦና ዝንባሌ ስሥነ-ጽሑፍ ከሆነ ታዲያ በሚዲያ ተቋማት ላይ መሥራት አይቀልህም ነበር?**

**ሃምሳአለቃ ጋሻዬ፡-** ሁሉም ሰው በተጠራበት መክሊት ውስጥ ይሠራል ብዬ አላስብም። እኔም ምንም እንኳን ለሥነ-ጽሑፍና ለኪነ-ጥበብ ፍቅርና ዝንባሌ ቢኖረኝም ውትድርናንም በጣም የምወደውና የማከብረው ሙያ ነው። ደግሞም በሠራዊቱ ውስጥ የማገልገል ዕድሉን በማግኘቴ ራሴን እንደዕድለኛ ነው የምቆጥረው። ወታደር በመሆኔ ከምንም በላይ ነው የምኮራው። በተለይም ባለፈው አንድ አመት ተኩል ውስጥ መከላከያ በጣም የተከበረበት፤ የሠራዊቱ ዋጋ በሚገባው ልክ ዋጋ ያገኘበት ጊዜ ላይ ወታደር እንደመሆን ሌላ መታደል ያለ ያለ አይመስለኝም። እንዳልሽው የሚዲያ ተቋማት ውስጥ ብሆን የሥነ-ጽሑፍ ፍላጎቴን የበለጠ የማረከበት ዕድል አገኝ ነበር፤ ግን ደግሞ ሠራዊቱ ውስጥ ሆኜም ይህንን ዝንባሌዬን የማስተናግድበት ዕድል አላጣሁም። እንዲያውም የበለጠ ተሰጥኦዬን የማዳብርበት አጋጣሚ ነው ያገኘሁት።

መከላከያ ከገባሁ በኋላ በተለይ ከሁለት ዓመታት በፊት ጦርነት ስላልነበር ብዙ ጊዜ ስለነበር በርካታ ጽሑፎችን እፅፍ ነበር። በጣም ደስ የሚለው ነገር ደግሞ መከላከያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ተሰጥኦ ይስተናገዳል። አቅሙና ፍላጎቱ ካለሽ የምትሳዩባቸው ዕድሎች አሉ። ጫካ ውስጥ ሳይቀር ሆኜ አነብና እፅፍ ነበር። በነገራችን ላይ ዛሬ ከሚመረቀው «የተከዳው ሰሜን ዕዝ» መጽሐፌ በፊት «ውሽታም» የምትል አንድ የግጥም መድብልና «ኢትዮጵያ ትሙት» የሚል ልብወለድ መጽሐፍ ለንባብ አብቅቻለሁ። አዲሱ መጽሐፌ ሙሉ ለሙሉ በጁንታው ጥቃት በደረሰበት የሰሜን ዕዝ ላይ ያጠነጠነ እውነተኛ ታሪክ የሆነ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ከጥቅምት 24 እስከ ታኅሣሥ 9 ቀን 2013 ዓ.ም የነበረውን ሁኔታ ነው የሚሸፍነው። ይህም ማለት የመጀመሪያው የሰሜን ዕዝ ጥቃት ከተፈፀመበት ጦርነቱ አልቆ ተመልሰን የተደራጀንበትን ጊዜ ነው የሚዳስሰው። ይህም ቅፅ አንድ ነው፤ ከዚያ በኋላ ያለውን ታሪክ አያካትትም።

**አዲስ ዘመን፡- ይህንን ታሪክ ለመፃፍ የተለየ ምክንያት ነበረህ? እንዴትስ ፃፍከው?**

**ሃምሳለቃ ጋሻዬ፡-** በነገራችን ላይ እኔ ራሴ ከታፈኑት የሰሜን ዕዝ አባላት አንዱ ነበርኩኝ። የፃፍኩትም በራሴና በጓዶቼ ላይ የደረሰውን፤ በዓይኔ የተመለከትኩትን፤ የኖርኩትንና የሰማሁትን እውነተኛ ታሪክ ነው። እኔ 20ኛ ክፍለጦር ሆኜ አዲግራት ነሐሴ ወር ላይ በ2012 ዓ.ም ነው የተመደብኩት። ሁለት ወር ሳልቆይ ነው ይህ ጥቃት የተፈፀመው። ጥቃቱ በተፈፀመበት ወቅት ከታፈኑ ሠራዊት መካከል ነበርኩኝ። ለ25 ቀናት በአፈና እና በስቃይ ውስጥ ነበርኩኝ። እኔ ደግሞ በፊትም ቢሆን ከቦታ ቦታ ስንቀሳቀስ ማስታወሻ መፃፍ እወድ ነበር። የተለያዩ ነገሮች ይገጥሙሻል። ይሄ ነገር ሲከሰትም እያንዳንዱን ነገር ቦታውንና ጊዜውን ሳይቀር በመጥቀስ ወደ መፃፍ ነው የሄድኩት። በመጀመሪያ ላይ በርግጥ ጥቃቱ በዚህ ልክ ይፈፀማል፤ ጦርነቱም ይሰፋል ብዬ አልጠበኩም ነበር። ሆኖም እያንዳንዷን ክስተት እፅፍ ነበር። ዕለት ዕለት ግን ነገሮች እየባሱ ሄዱ። እኔም መፃፌን ቀጠልኩኝ። ጓደኞቼም እያንዳንዱን ክስተት እንድፅፍ ይገፋፉኝና ይደግፉኝ ነበር። የምፅፈውም በስልኬ ስለነበር፤ ስልኬ እንዳይወሰድብኝ ሁሉም ጓዶቼ ተከላክለውልኝ ነበር። የሚገርምሽ ይህች ታሪካዊ ስልክ አራት ጊዜ ከመቀማት ድናለች። እነሱ ቢያውቁ ኖሮ አይደለም ሞባይል እስኪሪብቶና ደብተር እንኳን ሳይቀር ነው የሚቀሙት። ምክንያቱም በየቀኑ ነበር እንፈተሽ የነበረው። በአፈና የቆየንባቸው እያንዳንዱ ቀናት የአመት ያህል የሚረዝምበት ሁኔታ ነበር ያሳለፍነው። በጣም ብዙ ስቃይ ነበር ያደርሱብን። በጓደኞቼ ድጋፍ ተደብቄ እፅፋለሁ፤ በድብቅ ፎቶ እናነሳም ነበር። እነዚህን ፎቶዎች በመጽሐፌ ውስጥ አካትቼያቸዋለሁ።

እንደዕድል ሆኖ ቀድመው ከተያዙ የሠራዊቱ አባላት አንዱ ስለነበርኩ አብዛኛው ሠራዊት ጫካ እያደረ እኔና ጥቂት ጓዶቼ ቤት ውስጥ የማደር ዕድሉ ገጥሞን ነበር። ልብስ ተሸፋፍኜ ነበር የምፅፈው። ያም ሆኖ ግን በከፍተኛ ደረጃ በርሃብ እንድንሰቃይ ያደርጉን ነበር። በርሃብ ብዛት የሞቱ ጓደኞቼም አሉ። ምክንያቱም በአራት ቀን የሚያመጡልን አንድ ዳቦ ነው፤ ውሃ ማግኘት አይቻልም ነበር። በዚያ ላይ በጣም ብዙ ሠራዊት ነው ያለው። ደግሞም እጅ ላለመስጠት በርካታ ቀናት በጦርነት ውስጥ ስለቆየን ብዙ ተጎድተን ነበር። ምግብ የጠየቁ ልጆች ዓይናችን እያየ ገድለዋቸዋል። ከዚያ በተቃራኒ ደግሞ ለእኛ የሚያለቅሱ፤ አፍነው ሲወስዱን የሚከራከሩልን ፤ ለእኛ ሲሉ የተገደሉ የክልሉ ተወላጅ የሠራዊቱ አባላትና ሲቪል ሰዎች ነበሩ። በዚህ አጋጣሚ ግን የትግራይ ተወላጅ የነበሩ ሁሉም አባላት ሠራዊቱን እንደከዱ ተደርጎ በሚቀርበው ሃሳብ እኔ አልስማማም። አንዳንድ የክልሉ ተወላጅ አባላት ከእኛ ሳይለዩ ስለእውነት ሲሉ የሞቱ እና ክቡር መስዋትነት የከፈሉ አሉ። ለእኛ የሚያለቅሱ እናቶችም ነበሩ። እነዚህን ነገሮች ስመለከት ወዲያውኑ የሚቀናኝ ማስታወሻዬ ላይ ማስፈር ነበር።

እንደሚታወቀው ደግሞ ትግራይ ውስጥ በጣም በርካታ ካምፕ ነው ያለው። ክልሉ በሙሉ ካምፕ ነው ማለት ይቻላል። በየካምፑ ብዙ ግፎች ተፈፅመዋል። ሠራዊቱ አንድ ላይ ስለተሰበሰበ በየካምፑ የተፈፀመውን ነገር የመስማት ዕድሉ ነበረኝ። የትኛው ካምፕ ላይ ምን እንደተፈፀመ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ለእኔ በጣም ቀላል ነበር። ከበደሉ ባሻገር የተደረጉ በጎ ተግባራትንም የማየት አጋጣሚው ነበረኝ። ከተጨፈጨፈውና ከተገደለው ባሻገር ጥቂት የማይባል ሠራዊት በሕይወት መትረፍ ችለዋል። ይህ እንዲሆን ደግሞ በጣም በርካታ የትግራይ ተወላጆች አስተዋፅኦ ነበራቸው። የክልሉ ልዩ ኃይልና ሚሊሻው ሳይቀር ግማሹ ሲተኩስብን ሌላው ይከላከልንን ነበር። ሲቪሉ ማህበረሰብ ራሱ የተከፋፈለ ነበር። የተወሰነው እነሱን ሲደግፍ፤ ሌላው በእኛ በኩል ሆኖ የሚዋጋ አለ፤ መሃል ላይ ቆሞ ግራ የተጋባና የተደናገጠ ሕዝብ ነበር። እነዚህ ሁሉ ነገሮች እውነተኛ ታሪክ ስለሆኑ በሁሉም ፈርጅ ያለውን ለማካተት ሞክሬያለሁኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙጊዜ ባለው ሂደት ታሪክ በአፍ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ በቆየ እውነታ ላይ ተመርክዞ ነው፤ ይህም ደግሞ ታሪኩ በራሶ ተዛብቶ የሚቀርበበት ሁኔታ እንደፈጠረ ይታመናል፤ ከዚህ አኳያ አንተ ራስህ የታሪኩ አካል ሆነህ መፃፋህ ምንዓይነት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለህ ታምናለህ?**

**ሃምሳአለቃ ጋሻዬ፡-** እንደሚታወቀው ይህንን መጽሐፍ የፃፍኩት በሕይወትና በሞት መካከል ሆኜ ነው። በመሆኑም እውነታውን ለሕዝብ ለማድረስ እንጂ እንዲህ በሕይወት ተርፌን በመፃፍ ደረጃ ለማሳተም እበቃለሁ ብዬ አልነበረም። ብዙዎቻችን ያጋጠመንን ችግር ለሕዝብ የሚያደርስ ሰው እንዲተርፍ ፈጣሪን እንማፀን ነበር። ምክንያቱም ያሳለፍነው ጊዜ በጣም ከባድ ነበር። ብዙዎቻችንም ከዚያ ሁሉ ስቃይ እንወጣለን ብለንም አናስብም ነበር። ግን እኛም በሕይወት ተርፈን የደረሰብንን በመጽሐፍ ለማሳተም መቻሌ ራሴን እንደዕድለኛ ነው የምቆጥረው። ከዚያ ባለፈ ግን እንዳልኩሽ የሆነውን ሁሉ አንድ በአንድ ሳልጨምር ሳልቀንስ ነው የፃፍኩት። በተቻለ መጠን በጣም ሚዛናዊ ለመሆን ሞክሬያለሁ። በተለይ ወታደር እንደመሆኔ የወታደር ወኔና ስሜታዊነት በመውጣት ለመፃፍ ጥረት አድርጌያለሁ። ምክንያቱም በውጊያ መንፈስ የምፅፈው ከሆነ ሚዛናዊ ላልሆን እችላለሁ የሚል ስጋት ስለነበረኝ በተቻለ መጠን ከወታደራዊ ስነልቦናዬ ለመላቀቅና ገለልተኛ ለመሆን ሞክሬያለሁ። በተለይ ደግሞ እኔ ራሴ የዚህ አካልና የታሪኩ ትክክለኛ ምንጭ በመሆኔ እውነታው ቀጥታ እንዲደርስ ያደርገዋል ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም በስማ በለው ከሚፃፈው ይልቅ የችግሩ ሰለባ የነበርኩት እኔ መፃፌ የበለጠ ተቀባይነት ይኖረዋል ብዬ ነው የምገነዘበው።

ከዚያ ባለፈ ሕዝቡ ይህንን መጽሐፍ እንዴት ይቀበለዋል? የሚለውን ነገር ለአንባቢ መተው ነው የሚሻለው። እኔ ግን በዚህ መጽሐፍ የተነሳ ምንም ነገር ቢመጣ አይቆጨኝም። እንዳልሽው ብዙ ሰዎች አስተያየት እየሰጡኝ ነው ያሉት። አንዳንዶቹ በሽፋኑ ብቻ ላይ በመሞርኮዝ «ከዚህ ቀደም በተዛባ ታሪክ መጣላታችን አልበቃ ብሎ አንተ ደግሞ ይህንን መጥፎ ታሪክ መፃፍ ቀጣዩ ትውልድ ላይ መጥፎ ጠባሳ ትጥላለህ» የሚሉኝ አሉ። እኔ ግን በእውነተኛ ታሪክ ላይ ከተፃፈ የምንጣላበት ምክንያት አለ ብዬ አላምንም። እውተኛ ታሪክ ሊያጣላን አይገባም። እንዲያውም ቀጣዩ ትውልድ ከዚህ ታሪክ ብዙ የሚማርበት ነው የሚሆነው። እንዲያውም በትክክለኛ አዕምሮ ለሚያስብ ሰው የተጣሉ ሰዎችን የሚያስታርቅ መጽሐፍ ነው። እኔም በዚያ ልክ ይሆናል ብዬ ነው የምጠብቀው። እኛ የኖርበት ስለሆነ ምንም ላይመስለን ይችል ይሆናል፤ በሩቅ ሆኖ ለሚያየው ሰው ግን ሲያነበው የከፈልነው ዋጋ ምን ያህል ከባድ እንደነበር የሚገነዘበው።

ይሁንና በእኛ አገር ታሪክ ሲፃፍ አንድ ፈረንጅ የፃፈውን እንደማጣቀሻ አድርጎ ካልተፃፈ በስተቀር ለመቀበል የሚቸገሩ ብዙ ሰዎች አሉ። እኔ ግን በዚህ ስለማላምን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ምንም ዓይነት ማጣቀሻ አልተጠቀምኩም። ሆን ብዬ ነው ያደረኩት። እኔ በሕይወት እያለሁ ያየሁትንና የኖርኩት ሰው ሌላ ማጣቀሻ መጽሐፍም ዋቢ የሚሆን ፈረንጅ አያስፈልገኝም። ይህ መጽሐፍ ራሱ ሌሎች ለመፃፍ መነሻና ማሻቀሻ የሚሆን ነው። ለምርምር ሥራ ጭምር የሚጠቅም ነው። ምክንያቱም በእኛ ላይ ብሎም በአገር ላይ የተፈፀመው ክህደት ለትውልዶች ታሪክ ሆኖ የሚቆይ ነው።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



**አዲስ ዘመን፡- የዚህ መጽሐፍ ርዕስ በሠራዊቱ ላይ ከደረሰው ጉዳት አንፃር ምን ያህል ይሸከመዋል ብለህ ታምናለህ?**

**ሃምሳስቃ ጋሻዬ፡-** በነገራችን ላይ በዚህ መጽሐፍ ርዕስን በሚመለከት ከአንዳንድ ሰዎች ጋር በጣም ተጨቃጭቀናል። እኔ ግን መቶ በመቶ አምኜበት ይመጥነዋል ብዬ ነው ያስቀመጥኩት። እንዳልኩሽ የሚያጠነጥነው የአንድ ወር ጊዜ እንደመሆኑ በዚያ ጊዜ ውስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሊገለፅ የሚችለው በክህደት ብቻ ስለሆነ ነው ርዕሱን የተካደው ሰሜን ዕዝ ብዬ የሰየምኩት። ምክንያቱም እኛ ትግራይ ውስጥ ስንኖር የማኅበረሰቡ አካል ሆነን ነው የኖርነው። እኔ ራሴ ለቦታው አዲስ ብሆንም የፊተኛውን መጽሐፌን ሽጬ ባገኘሁት ገቢ ለተማሪዎች ስጦታ ሰጥቼ ነበር። በተለይ አዲግራት አካባቢ ለሚኖሩ 200 ለሚሆኑ ሕፃናት ቢያንስ ለአንድ ዓመት የሚሆን የጽሕፈት መሣሪያ ለመስጠት ጥቅምት 17 ጀምረን አቅደን መንቀሳቀስ በጀመርንበት በሳምንቱ ነው ጥቃት ያደረሱብን። ከዚያ በፊት ደግሞ አምበጣ መጣና ያንን ለማባረርና የደረሰውን ሰብል በማጨድ ከአርሶ አደሩ እኩል ነበር የደከምነው። ያን ሁሉ ዋጋ እየከፈለ ለነበረው ያ ድንቅ ሠራዊት ላይ በምትኩ በሌሊት ጥይት ነው የዘነበበት። በተለይ እኔ በዋነኝነት እኔ ስለነበርኩኝ የእርዳታውን ሥራ የማስተባብረው ሙሉ ትኩረቴን እዚያ ላይ አድርጌ ስለነበር እንዲህ ዓይነት አሰቃቂ ግፍ ይፈፀምብናል ብዬ አላሰብኩም ነበር። ምንአልባት ለዚህ ተግባር ሌላ ቃል ስለሌለው እንጂ «ክህደት» ከሚለው በላይ ብገልፀው ደስ ባለኝ ነበር።

ብዙ ሰዎች እንደሚሉት በሠራዊቱ ላይ የተፈፀመው ድርጊት በዓለም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ነው። ምንአልባት ቢኖርም እንኳን የእኛን ያክል ይሆናል ብዬ አላስብም። ምክንያቱም የእኛ ሠራዊት ትግራይ ውስጥ 23 ዓመት ሲኖር ከእናትና አባት በላይ ማኅበረሰቡን ቀርቦ ነው የኖረው። ወልዶ የልጅ ልጅ ሁሉ ያየ አለ። በየትኛውም ዓለም ካለ ሠራዊት በላይ ከሕዝብ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ነበረን። ይህ በመሆኑም የየትኛው አገር ሠራዊት ቢካድ ህመሙን የኛን ያህል አይሆንም። ምንአልባት ከዚያ በኋላ የሆነውን ነገር በቅፅ ሁለት ሲፃፍ ይሄ ርዕስ ላይቀጥል ይችላል። ለዚህም ነው ይህንን መጽሐፍ አጠቃላይ የጦርነቱን ሂደት የሚያካትት አድርጎ መወሰድ የሌለበት።

**አዲስ ዘመን፡- አንተ እንደገለፅከው ከኅብረተሰቡ ጋር ያን ያህል ቅርበት ኖሯችሁ ሳለ ስለጥቃቱ እንዴት ቀድማችሁ ፍንጭ ማግኘት አልቻላችሁም?**

**ሃምሳአስቃ ጋሻዬ፡-** ይሄ ጉዳይ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ነው። እኔ እስከሚገባኝ እና እዚህ መጽሐፍ ላይም እንዳሰፈርኩት ከጥቅምት 24 በፊት በግልፅም፤ በሰውርም የሚደረግ ነገር ነበር። ለምሳሌ በቴሌቪዥን ልዩ ኃይላቸውን አሰልፈው ሲፎክሩ ያሳዩን ነበር፤ ፕሮፖጋንዳቸውም ከባድ ነበር። በመሠረቱ እኛ ነሐሴ ወር ላይ ወደ ትግራይ ስንገባ በጣም ከባድ ስቃይ ነው ያሳለፍነው። ከዚያ በፊት እኔ ባድመ ላይ ተመድቤ ስለነበር ትግራይን በደንብ አውቀዋለሁኝ። እንዳልኩሽ ከማኅበረሰቡም ጋር የተለየ ቅርበት ነበረን። ከዚህ አንፃር የሕወሓት ሰዎች በግልፅ የሚያሳዩን ነገር ነበር። ያንን ነገር እየታየን ቀደም ብሎ ጥንቃቄ ማድረግ አልተቻለም? ብለሽ ከጠየቅሽ ግን ትክክለኛውን ምላሽ ልሰጥሽ አልችልም። ምክንያቱም ከእኔ አቅም በላይ ነው። ግን ደግሞ ከኅብረተሰቡ የተለያዩ ጥቆማዎችን ይሰጡን ነበር። ደግሞም የትኛው ወታደር ከአንዱ ካምፕ ወደሌላው ካምፕ ለመሄድ መሣሪያ ይዞ መውጣት አይችልም። ሁሉም ነገር በእነሱ ቁጥጥር ውስጥ ነበር። የትኛውም የሠራዊቱ መኪና ከካምፕ ሲወጣ መሣሪያ ይዞ መውጣት አይችልም። መኪናው ራሱ መውጣት የሚችለው በእነሱ ፍቃድ ብቻ ነበር። በተጨማሪም የእኛን የወታደር ልጆች ሳይቀር ያሰለጥኗቸው ነበር። የትግራይ ተወላጆች የሆኑ አባላት በሙሉ ከሌላው ሠራዊት ተነጥለው እዚያው ካምፕ ውስጥ ስብሰባ ያደርጉ ነበር። መጽሐፍ ውስጥ እደገለፅኩትም አንዳንዶቹ በቀልድ አስመስለው አንዳንድ ፍንጮችን ይጠቁሙን ነበር።

ለአብነት ያህል የቤተሰብ ፍቃድ ስንጠይቅ «ምንፍቃድ አስጠየቀህ? መከላከያን ማፍረሳችን ስለማይቀር ያኔ ጠቅልለህ ትሄዳለህ» ይሉን ነበር። የደመወዝ ጉዳይ ሲናነሳ ደግሞ «አይደለም የደመወዝ ጉዳይ ልታነሳ ትጥቅ መፍታትም አለ» የሚል ሃሳብ ያነሳሉ። አየሽ ይህንን ያክል ነበር የሚነግሩን! ፤ ግን ደግሞ ወታደር እንደመሆናችን ትዕዛዝና መመሪያ ትጠብቂያለሽ። ይህ አሠራር በመኖሩ ማንም ሰው የሚናገረውን ሰምተን እርምጃ መውሰድ አንችልም ነበር። ግን ይህ ጥያቄ የእኛም ስለነበር መጽሐፉ ውስጥም የተካተተው በጥያቄ ነው። በተለይ እነሱ ያንን ያክል ዝግጅት ሲያደርጉ ለምን ምላሽ መስጠት አልተቻለም? የሚለው ነገር አሁንም ለእኔም ሆነ ለሌላው ምላሽ ያላገኘ ጉዳይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ጥቃቱ ካደረሰው ጉዳት ባሻገር ግን ሕዝቡን በአንድነት የአገሩን ህልውና ለማስቀጠል እንዲነሳ ከማድረግ አኳያ የነበረው ፋይዳ እንዴት ይገለፃል?**

**ሃምሳስቃ ጋሻዬ፡-**አንዳንድ ጊዜ አየሽ እንዲህ ያሉ ድንገተኛ ጥቃቶች በጣም በጣም ብዙ ጉዳት ይዘው በሚመጡበት ጊዜ ከችግሩ ባሻገር መልካም ነገርም ይዘው ይመጣሉ። በእርግጥ ጦርነት ባይመረጥም የራሱ ጠቀሜታም ነበረው። የማልክደው ነገር ይህ ጦርነት የብዙ ወገኖቻችንን ሕይወት ነጥቋል፤ የሠራዊቱን ሕይወት አመሰቃቅሏል፤ ልጅ ከወላጁ ተለይቷል፤ ቤተሰብ ተበትኗል፤ ሚስት ባሏን ያስገደለችበት፤ ልጅ አባቷን ከዳ አሳልፋ የሰጠችበት ለመቀበል የሚከብድ ሁኔታ ተፈጥሯል። እንዳልሽው ከለውጡ በፊት ሕዝቡና ሠራዊቱ ሆድና ጀርባ ነበር። እንደአጋጣሚ ከለውጡ በፊት ጎንደር አካባቢ ነበርኩኝ፤ በወቅቱ ከነኮሎኔል ደመቀ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ አመፅ ሲቀሰቀስ ብዙ ጓዶቼን አጥቻለሁ። በጣም ከባድ ሁኔታዎችን አይተናል። ያ የሆነው ከዚህ ቀደም በነበረው ሥርዓት ነው። ሕወሓት ሕዝብና ሠራዊቱ እንዳይታረቅ አድርጎ ነበር ያጣላው። የዚህ ጦርነትም ውጤት ያ ነው። እንዳይታረቅ አድርጎ ያጣላውን ሠራዊት በገዛ እጁ በቀሰቀሰው ጦርነት እንዳይጣላ አድርጎ ሠራዊቱን ከሕዝብ ጋር አስታርቆታል ባይ ነኝ። ይህንን በአገርና በሠራዊት የተፈፀመ ክህደት ስትመለከቺ በቁጭት በኅብረት እንድትነሺ ነው የሚያደርግሽ። ብዙ ጉዳት ቢመጣብም ይህች አገር በሕዝቦቿ ኅብረት እንድትቀጥል አድርጓል።

በነገራችን ላይ እነሱ ሠራዊቱን ከሕዝቡ ጋር ብቻ ሳይሆን ተለያይቶ እንዲኖር ያደረጉት እርስበርሱ እንዳይጋባባ አድርገው ነበር የቀረፁት። በተለይ በጎሳ በመከፋፈል ሁሉም በየጎጡ እንዲቧደን በማድረግ ከሌላው ጋር ተስማምቶ እንዳይኖር ያልቆፈሩት ጉድጓድ የለም። ሲጀመር ምዝገባው ራሱ በጎሳ የተከፋፋለ ነበር። ይህንን ስልሽ አሁን ድረስ የትግራይ ተወላጆች ሆነው በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩና ከሁሉም ጋር በፍቅር መኖሩን የሚመርጡ የሠራዊቱ አባላት አልነበሩም ማለቴ አይደለም። ከአመራር እስከ ተራ ወታደር ድረስ ከእኛ ጋር አብረው የተሰቃዩ አሉ። አብዛኛዎቹ እኛን ክደው ሲሄዱ ከእኛ ጋር የነበሩት ጥቂቶቹ ግን ብዙ ፍዳቸውን አይተዋል። ሠራዊቱ ግን ለመከፋፈል የተደረገውን ጥረት አልቀበልም ብሎ አንድ ሆነ፤ ይልቁንም ሊከፋፍሉት የመጡትን አሳፍሮ ነው የመለሳቸው። በተለይ ከጥቃቱ ቀን ጀምሮ እነሱ በጎሳ ከፋፍለነዋል፤ አይግባባም ብለው ያሰቡት ይህ ሠራዊት እንደአንድ ሕዝብ ሆኖ ነበር ሲታገላቸው የነበረው። በአጠቃላይ ጥቃቱ ሠራዊታችንን በጣም ጎድቷል፤ በሌላ በኩል ግን ኅብረቱ የተጠናከረ ሠራዊት አድርጎታል። የእሱ ውጤትም ነው እንድናሸንፍ ያደረገን። እንደሥራቸው ቢሆንማ ኖሮ አይደለም ሠራዊቱ ኢትዮጵያ ራሱ እስከዛሬ አትሰነብትም ነበር። እንደአጀማመራቸውና እንደእነሱ እቅድ ቢሆን ኖሮ ከዚህ በከፋ ችግር ውስጥ በገባን ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- እንዲህ ዓይነቱ ነገር ለቀጣይ ምን አሰርተምሮ አልፏል ብለህ ታምናለህ?**

**ሃምሳ አስቃ ጋሻዬ፡-** በሠራዊቱ ላይ የተፈፀመው ይህ ድንገታዊ ጥቃት ከመጀመሪያው እንዲህ ይሆናል ብለን ባንጠብቅም ከአገር ውስጥ እስከ ውጭ ታላላቅ መንግሥታት ሳይቀር ነው የተሳተፉበት። በእኔ እምነት ኢትዮጵያ በዚህ ጦርነት ምክንያት የማይገባትን ዋጋ ከፍላለች። ይህንን ዋጋ የከፈለችው ደግሞ በራሷ ልጆች በጣም የሚያሳዝን እና የሚያስቆጭ ነው። ምክንያቱም እኛ ወታደሮች የአገራችን ሉዓላዊነት የምንጠብቀው ከውጭ ከመጣ ወራሪ ነው። አሁን እኛ እያደረግን ያለነው የህልውና ዘመቻ ነው። ህልውና ከሉዓላዊነትም በላይ ከባድ ነው። ምክንያቱም የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው። የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ጉዳይ ነው። ከሉዓላዊነትም በላይ የመጠቀ ነው። የእያንዳንዱን ቤት የሚያንኳኳም ነው። ይህ መሆኑ ነው የቆየንበትን ሁኔታ ከባድ ያደረገው። እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ለጦርነት አዲስ አይደለችም፤ ብርቋም አይደለም። እንዳካሄደችው ጦርነት ብዛት እስካሁን እንደአገር መቀጠሏ ራሱ አስገራሚነው። እኛ የአባቶቻችን ልጆች ነን፤ እነሱ ኢትዮጵያን አቆይተውልናል፤ እኛም እናስቀጥላታለን። ሆኖም የተፈፀመው ክህደት በሕዝቦች መካከል የማያባራ ፀብ የሚፈጥር መርዝ ነው የሚሆንብን ብዬ እሰጋለሁ። በዚህ አጋጣሚ ግን ባንዳ የሆኑ ሰዎችን ለመመንጠር አስችሎናል። ከዚህ በኋላም ነገሮችን በጥንቃቄ ለመያዝ ትምህርት የሰጠ ነው ብዬ ነው የማምነው። በተጨማሪም ለአገሩ፣ ለሕዝቡ ለሰንደቅ ዓላማው ክብርና ፍቅር ያለው ሠራዊት እንዲፈጠር ያደርጋል። እውነትን ብቻ ይዞ የሚሄድ፤ በትክክለኛ መንገድ ግዳጁን የሚወጣ ሠራዊት በደንብ እንዲፈተሽ ያደርጋል። ምክንያቱም በጦርነት ቀልድ የለም፤ ትንሽ ስህተት መሥራት ከፍተኛ ዋጋ ነው የሚያስከፍለው። እንዲህ ዓይነት መጽሐፍም የሚፃፈው እንድንማርበት ነው። ይህ ጦርነት የሠራዊቱን የቀድሞ ስም የቀየረም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ሠራዊቱ ዳግም ሪፎርም መደረጉ የኢትዮጵያዊነት ቁመና ያለው ተቋም ለመፍጠር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?**

**ሃምሳ አስቃ ጋሻዬ፡-** እኔ መከላከያ ከገባሁበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ብሔር የበላይነት ጉዳይ ውስጥ ለውስጥ በደንብ ሲወራ የነበረ ነው። ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በደንብ ገንፍሎ በገሃድ የታየው የእርሱ ውጤት ነው። ከአዲስ አበባ ሄዶ ነው መገናኛ ኃላፊው የሰሜን ዕዝን የሬዲዮ ፕሮግራም ሲስተም የቀየረው፤ ይህ ሰው የትግራይ ተወላጅ ነው። አዲስ አበባ ሄዶ የአንድን ግዙፍ ዕዝ የሬዲዮ መገናኛ ሲስተምን ሲቀይር ማንም አላወቀም። ይህም ውስጥ ለውስጥ ምን ያህል እንደሚሠሩ ነው። የሚገርምሽ ሰውየው ሲመጣ የእኛ ሠራዊት ሰንጋ ጥሎ በክብር ነበር የተቀበለው። እሱ ግን እንዲህ ላደረገለት ሠራዊት መሞቻውን ነው አዘጋጅቶለት የሄደው። ውጭ አገር ሱዳን ሰላም ማስከበር የሄዱ ጀነራሎች መጥተው ተልዕኮ ተሰጥቷቸዋል። በደንብ ስለሠሩበት፣ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ስለያዙ ነው ያደረጉትም። በወቅቱ የነበረውን እኛ በግልጽ መናገር አንችልም ነበር። ውስጥ ለውስጥ ከምትመሳሰይው ሰው ጋር የምታወሪው ነበር። መከላከያ ውስጥ በፌዴራል ቋንቋ ብቻ ነው የሚሠራው። ነገር ግን አንድ እስታፍ በትግርኛ ብቻ ስብሰባ የሚደረግበት ነበር። በብዛት ዋና ክፍል፣ አስተዳደሩ፣ ስልጠና ክፍሉ፣ አዛዥነት ደረጃ ላይ ያሉ እነርሱ ነበሩ። ሌላው ተዋጊ ነበር። አማርኛ፣ ኦሮሚኛ፣ አፋርኛ፣ ሱማሊኛ ወይም ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ በመካከላቸው አልነበረም። በሙሉ አንድ ብሔር ብቻ ነበሩ። የትምህርት ዕድል ሲሰጥ፣ ሰላም አስከባሪ የሚላከው በብሔር ተጠራርተው ነው። በአጠቃላይ በአንድ ብሔር የበላይነት ነው ይህንን ችግር ያመጣው።

ለውጡን ተከትሎ በተደረገው ሪፎርም በጣም ትልቅ ነገር ተደርጓል። በእኔ እምነት የመከላከያ ሠራዊት ሪፎርሙ ባይደረግ ኖሮ ጥቅምት 24 ቀን የሰሜን ዕዝ ላይ የተፈጸመው ጥቃት ቤተ መንግሥትም ይደገም ነበር። ሪፎርም በመደረጉም ነው ኢትዮጵያን እንደአገር እንዲያስቀጥል የመከላከያ ሠራዊት እንዲቆይ የተደረገው። ከእዚያ በፊት እኮ የመምሪያ ኃላፊ፣ ክፍለ ጦር አዛዥ፣ ዕዝ አዛዥ የብሔር ምጥጥን ባይደረግ ኖሮ በአንድ ቀን ኢትዮጵያ ትፈርስ ነበር። ግን ያም ሆኖ በደንብ ስለሠሩበት እና እስከ ታች ድረስ ለማስተካከል ብዙ ጊዜ ይጠይቅ ነበር። ምክንያቱም ሙያ ነው፣ መሪነት ነው። እየዳበረ የሚመጣ ነው፣ በትምህርት፣ በጊዜ ቆይታ የሚመጣ ነው። ማንንም አንስተሽ ጀኔራል ልታደርጊው አትችይም። ታች ያለው የሰለጠነና የበቃ ሰው ስላልነበር አምጥቶ ለመተካትም አስቸጋሪ ነበር። ሪፎርሙ ሠራዊቱ ላይ የደረሰውን ጥቃት፣ አገር እና መንግሥት ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ጥቃት በእጅጉ ቀንሷል። ያ ጥቃት በሰሜን ዕዝ እንዲደርስ ያደረገው ደግሞ በፊት ይሠሩበት የነበረው መረቡ በጣም ብዙ ጊዜ ይፈጅ ስለነበር ሠራዊቱ ሙሉ ለሙሉ እንዳይፈራርስ ሪፎርሙ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው።

**አዲስ ዘመን፡- ዓለም አቀፍ መስፈርቱን ያሟላ ሠራዊት ለመፍጠር ስነ-ምግባሩ በምን መልኩ መቀረፅ ይገባዋል ብለህ ታምናለህ?**

**ሃምሳ አስቃ ጋሻዬ፡-** ወታደር ፖለቲካ፣ የፖለቲካ ፓርቲ፣ ሃይማኖት፣ ብሔር አይመለከተውም። ሰው መብቴ ነው ብሎ የሚተገበራቸው አብዛኞቹ ነገሮች አይመለከቱትም። እርሱ የሚመለከተው ሕገ-መንግሥት ነው። ሕገ-መንግሥት ማለት ኢትዮጵያ የምትተዳደርበት፣ ሕዝብ የሚመራበት ነው። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ከጎጥ ወይም ከዘረኝነት የፀዳ ሠራዊት ለመገንባት ሰፊ ጊዜ ያስፈልገዋል። አሁንም ሠራዊቱን ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ከብሔር ጋር ያገናኙታል። የአገሪቱ ፖለቲካ የታመመ ነው። በዚህ በታመመ ሂደት ጤናማ ሠራዊት ይኖራል ብሎ ማሰብ አይቻልም። ፖለቲካው፣ የሕዝቡ ኑሮ፣ ሰላምና ፀጥታው ሲስተካከል ነው ሠራዊቱ በአግባቡ ሊገነባ የሚችለው። ሰላም በሌለበት ሠራዊት ግንባታ የለም። አሁን ሠራዊት የምትገነባው ለጦርነት ነው። መሠረታዊ፣ ብቁ፣ በአስተሳሰቡ የበቃ፣ ሕገ-መንግሥቱን የሚጠብቅ፣ ለሰንደቅ ዓላማው የሚሞት፣ ለማንም ፖለቲካ ተላላኪ የማይሆን፣ በሃይማኖት፣ በብሔር፣ በዘርና በጎጥ የማያምን ሠራዊት ለመገንባት ፖለቲካው መስተካከል አለበት።


**አዲስ ዘመን፡- ለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቼና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ ሳመሰግን እወዳለሁ።**

**ሃምሳአስቃ ጋሻዬ፡-** እንግዳችሁ ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## የኩላሊትና አእምሮ ጤናን የሚጠብቁ ተፈጥሯዊ ምግቦች

**አስናቀ ፀጋዬ**



እንደኩላሊት ታታሪ የሆነ የሰውነት ክፍል የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም ኩላሊት በሰውነት ውስጥ ያሉ ቆሻሻዎችንና ተጨማሪ ፈሳሾችን አጣርቶ በሽንት መልክ ስለሚያስወግድ ነው። ኩላሊት በሰውነት ሴሎች የሚመረቱ አሲዶችን በማስወገድ በሰውነት ውስጥ የተመጣጠነ ውሃ፣ ጨውና ሶዲየም፣ ካልሺየም፣ ፎስፈረስና ፖታሺየም የመሳሰሉ ሚኒራሎች እንዲኖሩም ያስችላል።

በሌላ በኩል ደግሞ አእምሮ የተወሳሰበ የሰውነት ክፍል ሲሆን አስተሳሰብን፣ የማስታወስ ችሎታን፣ ስሜትን፣ ንክኪን፣ የሰውነት ጡንቻ የመንቀሳቀስ ችሎታን፣ ራዕይን፣ መተንፈስን፣ ሙቀትን፣ ረሃብን እና ሌሎች የሰውነት እንቅስቃሴ ሂደቶችን ይቆጣጠራል። ከዚህ አንፃር አእምሮ ወሳኝ የሰውነት ክፍል ሆኖ ይቆጠራል።

ሆኖም በዓለም አቀፍ ዙሪያ በርካቶች የኩላሊትና የአእምሮ ጤና ችግር አጋጠመን ሲሉ ይደመጣሉ። እነዚህ ሁለት ወሳኝ የሰውነት ክፍሎች በአግባቡ ሥራቸውን እንዲከውኑና ከበሽታም እንዲጠበቁ ለእነሱ የሚስማሙ ምግቦችን መመገብ ይጠይቃል።

በተለይ ደግሞ ተፈጥሯዊ ምግቦችን መመገብ የኩላሊትና የአእምሮ ጤናን በመጠበቅ ረገድ ጉልህ ሚና እንደሚጫወት የሥነ- ምግብ ባለሞያዎች ይናገራሉ። ፈሊክሎድድ /fleekloadede.com/ ያወጣው መረጃ ደግሞ ከታች የተዘረዘሩት ሦስት ተፈጥሯዊ ምግቦች ለኩላሊትና አእምሮ ጤና ፍቱን መድኃኒት ናቸው ይላል።

**1ኛ፡- ቱና እና ሳለሞን ዓሣዎች**

እነዚህ የዓሣ ዝርያዎች በበርካታ ማዕድናት በተለይ ደግሞ የደም ግፊትን ለመቀነስ በሚረዱ ኦሜጋ-3 የበለፀጉ በመሆናቸው የኩላሊትዎንና የአእምሮውን ጤና መጠበቅ ከፈለጉ የዘወትር ምግብዎ ያድርጓቸው። ምን አልባት እንደነዚህ ዓይነት የዓሣ ዝርያዎችን ላያገኙ ቢችሉ እንኳን እዚሁ አገርዎ ያለውን ዓሣ የመመገብ ባህሉን ካዳበሩ የኩላሊትና የአእምሮ ጤናዎን በቀላሉ መጠበቅ ይችላሉ። በተለይ ደግሞ የደም ግፊትዎ ከፍተኛ ከሆነ የኩላሊት ህመም ሊኖርብዎት ስለሚችል ዓሣን አዘውትረው እንዲመገቡ በጤና ባለሞያዎች ይመከራሉ።

**2ኛ፡- እንጆሪ**

የኩላሊትዎንና የአእምሮዎን ጤንነት ለመጠበቅ መመገብ ካለብዎ ምግቦች ውስጥ ሌላኛው የእንጆሪ ፍሬ ነው። እንጆሪ ሲባል ታዲያ የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን ሁሉንም የእንጆሪ ዓይነቶች ያካትታል። የእንጆሪ ፍሬ በአንቲኦክሲደንት የበለፀገ በመሆኑ በተለይ የኩላሊትዎን ጤና በመጠበቅ ረገድ ቁልፍ ሚና ስለሚጫወት ይህን ፍሬ አዘውትረው እንዲመገቡ ይመከራሉ።

**3ኛ፡- ለውዝ**

የአእምሮዎን ጤንነት ከሚጠብቁ ምግቦች ውስጥ አንዱ ለውዝ ነው። ለውዝ በአንቲኦክሲደንት በተለይ ደግሞ በቫይታሚን ኢ የበለፀገ በመሆኑ በአእምሮ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ህመሞችን በመከላከል ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። እርስዎም ለውዝ ለማግኘት እምብዛም ስለማይቸገሩ የዘወትር ምግብዎ ቢያደርጉት ያተርፋሉ እንጂ አይከስሩም።

# ለጤንነትዎ

## ጤና መድህን በሸዋሮቢት

**አስናቀ ፀጋዬ**

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን መጠነ ሰፊ ውድመት ካደረሰባቸው አካባቢዎች አንዱ ሸዋሮቢት ሲሆን፤ ከመሠረተ ልማት ተቋማት ውስጥ ደግሞ የህክምና አገልግሎት መስጫዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ። ቡድኑ በወረራ በያዛቸው የአማራና የአፋር ክልል አካባቢዎች የሚገኙ በርካታ የጤና ተቋማትን አውድሟል፤ የህክምና መገልገያ መሣሪያዎችንና መድኃኒቶችንም ዘርፏል። በዚህም በሁለቱም ክልሎች በርካታ ሕዝብ ከህክምና አገልግሎት ተቆራርጧል።

ሆኖም አሸባሪ ቡድኑ በመከላከያ ሠራዊቱ፣ በአማራና አፋር ልዩ ኃይል፣ ሚሊሻና ፋኖ በተወሰደበት እርምጃ ከሁለቱ ክልሎች ተጠራርጎ ከወጣ በኋላ በመንግሥትና በተለያዩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች ድጋፍ የወደሙ ጤና ተቋማትን መልሶ የመገንባት ሥራዎች በስፋት ሲከናወኑ ቆይተዋል። በዚህም በተለይ መሠረታዊ የሚባሉ የህክምና አገልግሎቶችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለዜጎች ማቅረብ ተችሏል።

በዚሁ ጦርነት ምክንያት ከተቆራረጡ አገልግሎቶች ውስጥ ታዲያ አንዱ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አገልግሎት ሲሆን አንዳንድ ጤና ጣቢያዎች ከጦርነቱ በኋላ ዳግም አገግመው አገልግሎቱን በማስጀመር ለሌሎች አርአያ መሆን ችለዋል። ከነዚህ ውስጥም አንዱ በአማራ ክልል፣ ሰሜን ሸዋ ዞን፣ ቀወት ወረዳ፣ ሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኘው የሸዋሮቢት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ነው።



አቶ አስማረ ዘነበ፤



ወይዘሮ ወርቋ ንጉሴ፤



ወይዘሮ ቦጋለች ሽመልስ፤

ፎቶ - አስናቀ ፀጋዬ

ወይዘሮ ወርቋ ንጉሴ በሸዋሮቤት ከተማ ልዩ ስሙ ዜሮ ሁለት ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ነዋሪ ናት። የሦስት ልጆች እናት ስትሆን የዕለት ጉርሷን የምታገኘው ጉልት ውስጥ በከሰል ንግድ ነው። ሆኖም ያጋጠማት የልብ፣ ጉበትና የሳምባ ህመም ሥራዋን እንደልብ ሊያሠራት አልቻለም። የልብ ህመሟ እስካሁን ባይሻላትም ታዲያ ከዛሬ ስድስት አመት በፊት የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አባል በመሆኗ ካጋጠማት የጉበትና የሳምባ ህመም መዳን ችላለች።

‹‹የጤና መደህን አባል ባልሆን ኖሮ እነዚህ ሁሉ በሽታዎች ተደራርበውብኝ በሕይወት የመቆየት ዕድሌ እጅግ ዝቅተኛ ነበር›› የምትለው ወይዘሮ ወርቋ የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አባል መሆን ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነው ትላለች። በየዓመቱ በማዋጣው ገንዘብ ሳልሳቀቅ በፈለኩት ጊዜ የፈለኩትን የህክምና አገልግሎት እንዳገኝ ዕድል ሰጥቶኛልም ትላለች።

እስካሁን እንኳን ለህክምናዋ ከ400ሺህ ብር በላይ ወጪ መደረጉንና ይህም የተሸፈነው በጤና መድህን አባልነት መሆኑንም ትጠቁማለች። ከዚህ አንፃር ሰዎች የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አባል ቢሆኑ ካላስፈላጊ የህክምና ወጪ እንደሚድኑና ገንዘብ ሳይኖራቸው በአነስተኛ መዋጮ ብቻ የህክምና አገልግሎት ስለሚያገኙ ዛሬ ነገ ሳይሉ አባል ሁኑ ስትልም ወይዘሮ ወርቋ ትመክራለች።

ወይዘሮ ቦጋለች ሽመልስም በተመሳሳይ የሸዋሮቢት ከተማ፣ ዜሮ ሁለት ቀበሌ ነዋሪ ስትሆን በአነስተኛና ጥቃቅን የሻይ ዳቦ ንግድ ትተዳደራለች። የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አባል በመሆኗ ከምትኖርበት ሸዋሮቢት ከተማ እስከ አዲስ አበባ ድረስ በመሄድ የመጀመሪያ ልጇን የማሳከም ዕድል እንዳገኘች ትገልፃለች። አሁንም ሁለተኛ ልጇ ታሞ ለማሳከም ወደ ሸዋሮቢት ጤና ጣቢያ እንደመጣችና የጤና መድህን አባል ከሆነች ሁለት አመት እንደሆናት ትናገራለች።

‹‹ጤና መድህን ለእኛ የቁም እድራችን ነው›› የምትለው ወይዘሮ ቦጋለች እርሷን ጨምሮ መላው ቤተሰቧ የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ በመሆኑ እፎይታን እንዳገኘች ትገልፃለች። ሌሎችም የማኅበረሰብ አቀፍ ጤና መድህን አባል ቢሆኑ ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ እንደማይሆኑ ትመክራለች።

የሸዋሮቢት ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ኃላፊ አቶ አስማረ ዘበነ እንደሚሉት ተቋሙ በወረራው ወቅት ኢላማ ከተደረጉትና ዝርፊያና ውድመት ከደረሰባቸው ውስጥ አንዱ ነበር። ሆኖም ወረራው ከተቀለበሰ በኋላ በመንግሥት፣ በተለያዩ አጋር ድርጅቶች፣ ግለሰቦችና ዳያስፖራዎች ድጋፍ የተለያዩ መድኃኒቶችንና የህክምና መሣሪያዎችን ለተቋሙ ማሟላት ተችሏል። በዚህም ተቋሙ አገግሞ የጤና መድህን አገልግሎትን ጨምሮ ሌሎች የህክምና አገልግሎቶችን መስጠት ጀምሯል።

በዚህም ከሸዋሮቢት ከተማ በዘንድሮው ሁለት ሩብ አመታት ውስጥ 15ሺህ 372 ታካሚዎች ወደ ጤና ተቋሙ መጥተው በጤና መድህን ተገልግለዋል። ከቀወት ወረዳ 1ሺህ 572፣ ከጣርማ በር ወረዳ 260 ታካሚዎች እንዲሁም ከኤፍራታ ግድም 568 ታካሚዎች በጤና መድህን የህክምና አገልግሎት በጤና ተቋሙ አግኝተዋል።

ይህ አገልግሎት በገንዘብ ሲተመን ደግሞ ከሸዋሮቢት ከተማ አስተዳደር በዚህ ሁለት ሩብ ዓመት 937ሺህ 209 ብር በጤና መድህን ተጠቅመዋል። ከቀወት 900ሺህ 300 ብር፣ ከጣርማ በር 16ሺህ 67 ብር፤ እንዲሁም፣ ከኤፍራታ 27ሺህ 17 ብር በሁለቱ ሩብ አመታት በጤና መድህን የህክምና አገልግሎት ተጠቅመዋል።

በጣቢያው ከመድኃኒት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ እጥረት ይታያል። 30 ከመቶ የሚሆኑ የመድኃኒት ዓይነቶችም በጤና ተቋሙ የሉም። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅርቦት አገልግሎት መድኃኒቶችን ማግኘት አለመቻልና በውጪ የሚሸጡ መድኃኒቶች ውድ መሆናቸው ነው። ይሁንና በተቻለ አቅም ሁሉንም ዓይነት ጥረቶችን በመጠቀም መድኃኒቶችን ለማቅረብ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)

gechoseni@gmail.com

> የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# እንደ ነዋሪ መሥራት፤ እንደ ሟች መኖር

**ቀዳሚ መንደርደሪያ፤**

ግፈኞች ለበደል የሚፈጥኑት ሟች መሆናቸውን ስለማያስቡ ብቻም አይደለም። ሟችነታቸው ባይጠፋቸውም የግፋቸውን ጥም ለማርካት ሲሉ በደላቸውን እንደ ውሃ ስለሚጎነጩ ለፀፀት ጊዜ አይኖራቸውም። የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን የሚለየው በጋራ በጸደቀ ሕግ መመራቱ ብቻ ሳይሆን በህሊና ዳኝነትና አመዛዛኝነት ጭምር ራሱን ስለሚገዛ ነው። ክፉና ደጉን ለይቶ ራሱን ለመግራትም ሆነ ለመምራት ፈጣሪ የተለየ ዕውቀት አድሎታል። እውነታው ይህ ቢሆንም ሰብዓዊ ፍጡር በአብዛኛው ነገን የሚናፍቀው «ስኬት» በማለት ከሚያልመው «ጫፍ» ላይ ለመድረስ እንጂ ከአፈር ጋር የሚዳበል ሟች መሆኑን ለማሰላሰልና ለማሰብ እጅግም ሲተጋ አይስተዋልም። የሩጫውን ልጓም እየገታም ቆም ብሎ ተሰባሪ መሆኑን ለመፈተሽ ጊዜ አይሰጥም።

ደራሲ ማሞ ውድነህ በአንድ መጽሐፋቸው መግቢያ ላይ እንዲህ የሚል ሃሳብ አስፍረዋል፡-«አንዳንዶች… ከትቢያ እየተነሱ ለታላቅ ኃላፊነት ከደረሱ በኋላ የማሰብና የማስተዋል ብርታታቸው እየደከመ [እንደ ዘለዓለም ነዋሪ ራሳቸውን እየቆጠሩ]፣ የሰው ዘር እልቂትና የአገር ውድመት የየዕለቱ ደስታቸው እየሆነ…ሥራቸው ወጥመድ…ፍጻሜያቸው አሰቃቂ ሆኖ ያለፉ ብዙዎች ናቸው።» በማለት ከገለጹ በኋላ፤ አንድ የአገራችንን መራር ታሪክ በማስታወስ እንዲህ ጽፈዋል።

«…ያለ ርህራሄ ተደበደቡ። በተገኘው መሣሪያ ሁሉ ኢትዮጵያውያን ተፈጁ። ቤት እየተዘጋባቸው ተቃጠሉ። በተወለዱበት አገራቸው፣ በአደሩበት አልዋሉም። በዋሉበት አላደሩም። በሀብታቸው አላዘዙበትም። የበደሉት ነገር አልነበረም… የፍርድ መሻት ጩኸታቸውም መልስ አላገኘም።…ፀጋ ከአገሪቱ መሬት ተገፈፈ…ቀኑም ሌሊቱም አንድ ነበር። ይህን ሁሉ ግፍ ያስፈጸሙት….» እያሉ ይቀጥላሉ።

ደራሲው «ይህንን ሁሉ ግፍ ያስፈጸሙት…» በማለት የሚወቅሱትን አካል ማንነት በሚገባ ገልጸውታል። ስለማን እንደሚናገሩ ባናውቅ ኖሮ ይህንን በእንጥልጥል የተተወ ድርጊት በቀጥታ የምናመሳስለው ከአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ስለመሆኑ አስረግጦ መናገር ይቻላል። ለመሆኑ ከላይ ከተዘረዘሩት አሰቃቂ ሁኔታዎች ዛሬ በዐይናችን ፊት ያልተፈጸመ ምን ነገር አለ? እንዲያውም ባይከፋ? ለማንኛውም ነፍሰ ሄሩ አንጋፋው ደራሲያችን በመጽሐፋቸው ውስጥ የተረኩት የፋሽስቶቹ መሪ የቬኒቶ ሞሶሎኒ ወራሪዎች በአገራችን የፈጸሙትን ግፍ ነበር። ለነገሩ የሩቁን ታሪክ ወደ ኋላ ዞረን ለመመልከት ምን አታከተን። የእኛዎቹ አሸባሪ ጉዶች የፈጸሟቸውና እየፈጸሟቸው ያሉት የክፋት ጥግ ግፎች ከዚህ በምን ይለያሉ። ደግሞስ ባይበልጡ!

ይህ ጸሐፊ «ልጄ ሆይ እንደምትኖር ሆነህ ሥራ፤ እንደምትሞት ሆነህ ኑር» የሚለውን ልብ ጠለቅ የጠቢብ ምክር ለመስማት የታደለው ገና በታዳጊነት ዕድሜው ላይ እያለ ነበር። ዓመታት ያላደበዘዙት ይህ ድንቅ አባባል ዛሬም ሆነ በወደፊት ቀሪ ሕይወቱ በፍጹም ወይቦ ወይንም ነትቦ ሊጠፋ እንዳይችል ሆኖ በአእምሮው ውስጥ ታትሞ ቀርቷል።

አገሬን በየዘመናቱ የገጠሟት የውስጥ ችግሮች በሙሉ መንስዔያቸው በአግባቡ ቢጠና ውጤቱ የሚመራን እንደ ዘለዓለማዊ ነዋሪ ቁምነገር ሠርተው፤ እንደ ሟች ደግሞ በህልፈት ሊሰናበቱ መቻላቸውን ማሰብ የማይፈልጉ ጨካኞች በሚፈጥሯቸው ችግሮች ምክንያት እንደሆነ በቀላሉ ማረጋገጥ ይቻላል።

በተለይም እየኖርንበት ባለነው በዚህ የዕለት ጀንበራችን እየተፈጸሙ ያሉ መከራዎቻችንና አበሳዎቻችን የሚመነጩትና የሚረጩት እንደ «ቋሚ ነዋሪ» በራሳቸው ዙፋን ላይ በነገሡ ዜጎችና ሹመኞች አማካይነት መሆኑ ምስክር አያስፈልገውም። «ግፈኛ የሠይጣን መልዕክተኛ» መባሉስ ስለዚሁም አይደል።

**አገሬን ሌሎች እንደምን ይገልጧታል?**

«ግምገማ» የአገሪቱ ቋሚ ባህል እስኪመስል ድረስ መሠረቱ የተተከለው እጅግ ጠልቆ ነው። መገማገሙ ባይከፋም ከመጯጯኹ በኋላ የተገማገሙበት ጉዳይ ፍሬ አልባ፤ የተገመገመው ግለሰብም ቂመኛ ከመሆን ውጪ አንዳችም ትርፍ ስለማስገኘቱ «አትርፈንበታል» የሚሉት ይነግሩን ካልሆነ በስተቀር እኛ የታዘብነው ውጤቱ «የደመና ክምር» ሆኖ ሲበንና ሲበን ነው።

ለነገሩ ዓላማ ያለው ግምገማና ለማቅናት የሚደረግ መፈታተሽ ሁሉ እርባና ቢስ ነው ብሎ መጠቅለል እንዳልሆነም አጽንኦት ሰጥቶ ማስታወስ ያስፈልጋል። የመደበኛ የሥራ ውጤት በሥራ መሪ እንደሚገመገም፣ የፖለቲከኞች ስምሪትም (ብዙ ጊዜ «ለጥሎ ማለፍ» ሽኩቻ ጥሩ ሜዳ መሆኑ ሳይዘነጋ)፤ «ምን ሠርተህ/ሽ ከረምክ/ሽ፣ ምንስ ልትከውን/ልትከውኚ ጨከንክ/ሽ እንደሚባባሉ የሹሞችን ፊት አይተው የሚያድሩት ሚዲያዎቻችን ዕለት በዕለት ግብሩን ሳይሆን ቃሉን ሳያሰሙን ጀንበር ጠብታ አትመሽም።

ለማንኛውም አሰልችቶን ኖሮ እያሰለቸን ያለውን «የግምገማ ባህል» በወፍ በረር ግምገማ ከገመገምነው ዘንዳ ወደ መነሻ ሃሳባችን አቅንተን እንደተለመደው «መስሚያ ጆሮ» ይኖራቸው ከሆነ «ለሚመለከተው ሁሉ!» በማለት ትዝብታችንን እንዘረግፋለን።

ለመሆኑ አቻ አገራት አገሬን ይገምግሙና ሪፖርቱን ይግለጡልን ብንል የግምገማቸው ውጤት ምን ሊሆን ይችላል? ከትናንት ይልቅ ዛሬ በዚህ ጉዳይ ላይ ቀልብያችንና ነፍሳችንን ሰብሰብ አድርግን «እህ» ብለን ብናደምጣቸው አንዳች ቁምነገር አናገኝም ይሆን?

የግምገማውን ውጤት ከመተንበያችን አስቀድሞ የዚህን ጸሐፊ አንድ መራራ ገጠመኝ ማስታወሱ ቦታው ሳይሆን እንደማይቀር በመገመት በአጭሩ እንዲህ እናስታውስ። ይህ ጸሐፊ ከጥቂት ዓመታት በፊት ታላቅ የተሰኘ ስልጠና ለመሳተፍ «የበቃሁና የነቃሁ ነኝ» በሚል አንድ አገር ተገኝቶ ነበር። ከስልጠናው መርሃ ግብሮች መካከል አንዱ እያንዳንዱ ሰልጣኝ በስልጠናው መስጫ ኢንስቲትዩት አካባቢ በሚገኙ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እየተገኘ ስለ አገሩ የማስተዋወቂያ ንግግር እንዲያደርግ ይጠበቅበት ነበር።

ይህ ጸሐፊም በተመደበበት ት/ቤት ተገኝቶ ስለ አገሩ ስለ ኢትዮጵያ መሠረታዊ ናቸው የሚላቸውን ማሞካሻዎችና «መኩሪያ ባህሎች» በመዘርዘር ከተረከ በኋላ ተማሪዎቹ ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ ዕድል ሰጣቸው። «ጥያቄ ያለው?» ብሎ ገና ቃላት ከአፉ ከማውጣቱ እነዚያ ታዳጊ ወጣቶች ለጥያቄ እጃቸውን እንደ ችቦ በመቀሰር ቅድሚያ ለማግኘት ተሽቀዳደሙ።

የመጀመሪያው ተማሪ፡- «ለምን ጦርነት ወዳድ ሆናችሁ?» በማለት የጥያቄ ቋጥኝ ወርውሮ ራሱን መቀመጫው ላይ ወረወረ። ሁለተኛው ተማሪ ቀጠለ፡- «እንዴት ርሃብን ለማሸነፍ አቃታችሁ?» እርሱ በፈገግታ ተጠያቂው ፊቱን አጨፍግጎ «የተወነጨፈበት የዳዊት ጠጠር» በብዙ ኅሊያዶች ፊት እንዳይዘርረው በመስጋት ውስጡን ብርድ ብርድ እንዳለው በጠያቂዎቹ ተከታታይ የጥያቄ ማዕበል ወረደበት። «ለምን አትሰለጥኑም?» የከፋው ጥያቄ ይህ ነበር። እነዚህ ለናሙናነት የተመረጡት ጥያቄዎች ለጊዜው ስለሚበቁ በተከታዩ ክስተት ማጠቃለል ይበጅ ይመስለናል።

ለካንስ እነዚያ ገና «ነፍስ ለማወቅ ድክ ድክ የሚሉት

> **እውነት ነው! የችግሮቻችን ዋናው ምክንያት «እንደሚኖሩ ሆነው የሚሠሩ፤ እንደሚሞቱ ሆነው የሚኖሩ ሹማምንት ስላጣን፣ ህሊና አደር ፖለቲከኞች ስለጠፉብን፣ ታማኝ ነጋዴዎች እንደ ሸቀጦቻቸው ስለተወደዱብን፣ ሆደ ባሻ ምሁራን የሩቅ ተመልካቾች ስለሆኑብን፣ መከራ የተሸከመው ሕዝብ በተስፋ መቁረጥ ስለተሞላ፣ ሥራ ጠልነት ባህላችን ስለሆነ፣ ሁሉም አውቃለሁ እንጂ ልወቅ ለማለት ልቡን ስላደነደነ ወዘተ.» የሚሉትን ሃሳቦች ፈነጣጥቆና እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደሩ ከሁሉም የተሻለ መልስ ነው**

ታዳጊዎች» ጥያቄው ተመጥኖና ተቀነባብሮ የተሰጣቸው በመምህራኖቻቸው አማካይነት ነበር። «እንዳያልፉት የለም…» አለ በረኸኛው አዝማሪ፤ እንኳንም አለፈ እንጂ ያንን ቀን ይህ ጸሐፊ በፍጹም አይዘነጋውም። እንኳን ሊዘነጋው ቀርቶ ትዝ ባለው ቁጥር እነዚያ ትንታግ ነበልባል ልጆች በመራር ትዝታ ግዘፍ ነስተው ብቅ ጥልቅ እያሉ እንደሚያባንኑት የሚገልጸው በኑዛዜ ያህል ነው። መቼም «ምን መልስ ሰጠሃቸው?» ብሎ አንባቢው ሌላ ሙግት ውስጥ እንደማይገባ በማመን ወደ ሌላው ጉዳይ እንሸጋገር።

ዛሬ «ታናናሽም» ይሁኑ «ታላላቅ» የምናላቸው ሉዓላዊ አገራት ጓደኞቻቸውን ኢትዮጵያን የግመገማ ጥያቄ እንዲጠይቋት ቢፈቀድላቸው ከታዳጊዎቹ ሕፃናት የተለየ ምን ጥያቄ ሊጠይቁ ይችላሉ ብለን እንጠረጥራለን? የጸሐፊው መልስ ልዩነት አይኖረውም የሚል ነው። «መቼ ነው ከርሃብ ባርነት ነፃ የምትወጡት? ለምን በመወያየት አታምኑም? ለምን እርስ በእርስ ትጠፋፋላችሁ? ለምን ግትርነታችሁን አታስወግዱም? ለምን ጦራችሁን ወደ ማረሻ አትለውጡም? ለምን እርዳታ በቃንን አታውቁም?» ይህቺ ምስኪን ገመምተኛ አገር ሌላም ብዙ ብዙ ጥያቄዎችን ልትጠየቅ እንደምትችል ብንገምትም ቁስሎቿን ላለመደነቋቆል ስንል በዚሁ እናቁም።

እንደ ጸሐፊው እምነት ለሁሉም ጥያቄዎች ሊሰጥ የሚገባው አጠቃላይና «ማስተር» መልስ የሚከተለው ቢሆን ከክርክር ብቻም ሳይሆን ከራሳችን የሽንገላ ቅንብርም የሚታደገን ይመስላል። እውነት ነው! የችግሮቻችን ዋናው ምክንያት «እንደሚኖሩ ሆነው የሚሠሩ፤ እንደሚሞቱ ሆነው የሚኖሩ ሹማምንት ስላጣን፣ ህሊና አደር ፖለቲከኞች ስለጠፉብን፣ ታማኝ ነጋዴዎች እንደ ሸቀጦቻቸው ስለተወደዱብን፣ ሆደ ባሻ ምሁራን የሩቅ ተመልካቾች ስለሆኑብን፣ መከራ የተሸከመው ሕዝብ በተስፋ መቁረጥ ስለተሞላ፣ ሥራ ጠልነት ባህላችን ስለሆነ፣ ሁሉም አውቃለሁ እንጂ ልወቅ ለማለት ልቡን ስላደነደነ ወዘተ.» የሚሉትን ሃሳቦች ፈነጣጥቆና እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደሩ ከሁሉም የተሻለ መልስ ነው።

መቼም ራሳችንን ለማየት «ህሊናችንና ድርጊታችን የዐይንና የቅንድብን» ጉርብትና ቢያስታውሰንም ሰከን ብለን እንደ አገርና ባለ አገሮች አቋማችንን ብንፈትሽ እውነታው ከላይ ከተዘረዘሩት መልሶች ውጪ ይሆናል ተብሎ አይገመትም። እስከ መቼ በአፍቅሮተ ራስ እንደናወዝን እንኑር? እስከ መቼስ ከችግር ጋር ተላምደንና ተዳብለን ዕድሜያችንን እንፍጅ? እኮ እስከ መቼ ለመደጋገፍ ሳይሆን ለመጠፋፋት አመጽን በደቦ ስንፈጽም እንኖራለን። ዘመን ሲነጉድ እኛ ግን በዚያው በተቀመጥንበት ቦታ ማኅላጀጃ ምን ረባን፤ ምን ጠቀመን። እስከ መቼስ «ሃሳብ እሹሩሩን» እንደ ብሔራዊ መዝሙራችን እያንጎራጎርን ዕድሜያችንን እንገፋለን? በዚሁ በእኛው ዕድሜና በእኛው ጀንበር በኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያልተፈጸመ የግፍ ዓይነት ይኖራል? እኛ ያልሞከርነው ወይንም ያልተሞካከርንበት የእኩይ ድርጊትስ ይኖር ይሆን?»

መታወቂያ ግብሩን ያዋሰን አያ ሰይጣን እርሱ ከተካነበት ክፋት በተሻለ ሁኔታ ስንለማመድ ቢያየን ምን ይለን ይሆን፡- «እናንት ብርቱ ባሪያዎቼ እነሆ ወደ አዘጋጀሁላችሁ ስፍራ ተሰብሰቡ» ሳይለን ይቀራል። ርሃብ ሰለቸን፣ ሞት መረረን፣ መጠፋፋት አንገሸገሸን፣ መዘላለፍ እጅ እጅ አለን፣ ተንኮልና ሴራ አጥወለወለን። ስለዚህ እንደ አገርና እንደ ዜጎች ጨክነን ልንፈወስበት ለምንችለው ለዚህ መርህ አጥብቀን እንገዛ፡- «እንደምንኖር ሆነን እንሥራ፤ እንደምንሞት ሆነን እንኑር።» ይሄው ነው። ሰላም ይሁን!!

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተናጋሪው ዶሴ

# ሩቅ አሳሚው እንግዳ ...

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

የቤቱ አባወራ ትጉህና ጠንካራ አባት ነው። ቤተሰቦቹን ለማኖር ቤቱን በወጉ ይመራል፤ ሚስቱን አክባሪ ልጆቹን ወዳድ ስለመሆኑም አገር ጎረቤት ይመሰክራል። አመታትን የዘለቀበት ትዳር ለበርካቶች ምሳሌና አርአያ እንደሆነ ዘልቋል።

ከፋ ዞን ቦንጋ ከተማ ። አቶ ሲሳይ ዲዳና ከትዳር አጋሩ ስምንት ልጆችን አፍርቷል። ተግባቢና ቅን አሳቢ ነው። ባለቤቱን ጨምሮ ለሚያስተዳድረው በርከት ያሉ ቤተሰብ ሌት ተቀን ይለፋል። . ሲሳይ የመንግስት ሰራተኛ እንደመሆኑ ተቀጥሮ አመታትን ባገለገለበት የመንገድ ስራ ከባልደረቦቹ ጋር ተግባብቶ በመስራት ይታወቃል።

መልካም ምግባሩን የሚያውቁ ሁሉ ስለእሱ ያላቸው ምስክርነት ከአክብሮት ጋር ነው። የመስሪያ ቤቱ አለቆች በሲሳይ ጉብዝና ይተማመናሉ ። ሁሌም ጠንከር ያለ ስራን ከኃላፊነት ጋር ያስረክቡታል ። ብርቱው ባለሙያ ለስራ ካሉት ቀልድ አያውቅም። ግዳጁን በታላቅ ውጤት አጠናቆ ለቀጣዩ ተግባር ይዘጋጃል። አቶ ሲሳይ ጥርሱን በነቀለበት ሙያው ታምቶ አያውቅም ። ለስራው ተገዢና ሟች ነው ።

አንዳንዴ አቶ ሲሳይ ከዋና መስሪያ ቤቱ የሚያርቅ ስራ ያጋጥመዋል። ይህ አይነቱ የመስክ ቆይታ ቀናትና ሳምንታትን አልያም ወራትን ሊፈጅ ይችላል። በእንዲህ አይነቱ ግዴታ ስራውን በብቃት የሚወጣው ሲሳይ ከስራው መልስ ከኃላፊዎቹ አድናቆትን ይቸራል፣፤

የሲሳይ አለቆች ሁሌም በጠንካራው ሰራተኛቸው ብቃት ይተማመናሉ። እንዲህ መሆኑ ሲሳይን ወደተለያዩ ወረዳዎች ያመላልሰዋል። ትዕዛዝ አክባሪው ሰው ለተሰማራበት የመንገድ ስራ ሁሌም ዝግጁ እንደሆነ ነው። በየደረሰበት የተጠቃሚውን ችግር ለመፍታት ከልቡ ይተጋል። ይህ ትጋቱ ሁሌም በውጤት ያሳጅበዋል፣፤ በመልካምነት ያስጠራዋል።

የመንገድ ባለሙያው ክረምት ከበጋ በማይቋረጥ ግንባታ ላይ ይሰማራል። እሱ በሚሳተፍባቸው የገጠር አካባቢዎች ከፍተኛ ድልድዮችና የመንገድ ግንባታዎች ይሰራሉ። እሱ ችግር አለባቸው በተባሉ ስፍራዎች አስቀድሞ ይገኛል ። ለሲሳይ የአናጺነትና የግንበኝነት ፣ ሙያዎች ከእጁ የራቁ አይደሉም። አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ተገኝቶ ስራውን ይመራል፣ይቆጣጠራል። አንዳንዴ በእጁ ያለውን ስራ ትቶ ወደሌላ ቦታ እንዲሄድ ይገደዳል። ለመስሪያ ቤቱ ወሳኝና አስፈላጊ ነውና በእንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ተከፍቶ አያውቅም። የተሰጠውን ሊፈጽም ፣በቀና ልቦና ወደተባለው ቦታ ይሄዳል።

የሲሳይ ቤተሰቦች የስራ ባህርይውን ጠንቅቅው ያውቃሉ። ወደ መስክ ሲወጣ በወጉ ይሸኑታል። ሲመለስ ጠብቀው በደስታ ይቀበሉታል። ባለቤቷን የምታከብረው ወይዘሮ የአባወራዋን በሰላም ወጥቶ መግባት ትመኛለች። በስስት የሚያዩት ስምንት ልጆችም ስለአባታቸው የተለየ ቦታ አላቸው። አባታቸው ለእነሱ አባት ብቻ አይደለም። የጓደኛ ያህል ነው ። በተለየ ፍቅር ይቀርባቸዋል።

ሲሳይ ወደመስክ በወጣ ጊዜ የእጅ ስልኩ አያርፍም። ለቤተሰቦቹ ይደውላል። ለባለቤቱ ሁኔታውን ያስረዳል። ለአለቆቹ ስለስራው ሪፖርት ያደርጋል። ሚስቱና ልጆቹ ከመነሻው ጀምሮ እስከሚያርፍበት ድረስ ደህንነቱን ያረጋግጣሉ። ለእነሱ በሰላም መድረሱ እፎይታቸው ነው።

አንዳንዴ አቶ ሲሳይ የሚሄድበት ስራ ሊያቆይ፣ሊያከርመው ይችላል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ሆቴል ከማረፍ ቤት መከራየትን ይመርጣል። ቆይቶ በሚሰራበት አካባቢ ከምግብ ቤቶች ከፍሎ ይመገባል። ስራውን ሲጨርስም ወደመጣበት ይመለሳል። የስራ ባህርይው ሆኖ የመንገድ ግንባታው ከሌሎች ጋር ያገናኘዋል። ከስራ ባልደረቦቹ፣ከአካባቢው ነዋሪና ከሌሎች ጋር በሰላም ውሎ መለያየት ልማዱ ነው።

ሲሳይን የሚቀርቡት ስለመልካምነቱ ተናግረው አይጨርሱም። የዋህና ቅን መሆኑን፣ ለብቻው መብላት፣ መዝናናት ያለመውደዱን ይመሰክራሉ። ታታሪው አባወራ ከመስክ ስራ መልስ ደከመኝን አያውቅም። ሚስትና ልጆቹን ለማስደሰት ከቤት ደርሶ የቻለውን ያደርጋል። ይህ ልማዱ ለመላው ቤተሰብ አይረሴ ትዝታ ነው።

ሲሳይ ለጎረቤቶቹና ለአካባቢው ነዋሪ ታዛዥና ቅን አሳቢ ነው። በታቻለው ሁሉ ከሁሉም ጋር በሰላም መኖርን ይሻል። ይህን ባህርይ የሚያውቁለት ስለእሱ ከበሬታና ፍቅር አላቸው። ትዳሩን አክባሪ ቤተሰቡን ወዳድ በመሆኑ ለብዙዎች መልካም ምሳሌ ሆኖ ይጠቀሳል።



**ታህሳስ 3 ቀን 2010 ዓም...**

ሲሳይ በማለዳ ከቤት የወጣበት ስራው ላይ አርፍዷል ። ከመስሪያ ቤቱ ደርሶ የዕለት ግዴታውን ሲወጣም ውሏል። ከምሳ በኋላ በነበረው ጊዜ ከቅርብ አለቆቹ የስራ ትዕዛዝ ደረሰው። እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ለታታሪው ሰራተኛ አዲስ አይደለም። የተሰጠው ስራ ከቢሮው ተቀምጦ የሚሰራው አይደለም። ከቆይታ በኋላ በሚጓዝበት ወረዳ ጊዜያትን ፈጅቶ የሚቆይበት ስራ እንዳለ ከቀናት በፊት ተነግሮታል።

ሲሳይ የስራ ስምሪቱን እንዳወቀ የሚጓዝበት መኪና ተመደበለት። ለወጪው የሚያስፈልገው ውሎ አበል፣ ለስራው የሚያግዙት ቁሳቁሶችና ሌሎችም ዝግጁ ሆኑለት። ለስራው ጓዙን የሸከፈበት አካባቢ ከመኖሪያው ይርቃል። ለስራ ትዕዛዝ የተቀበለበት የአዲዮ ወረዳና ነዋሪው በክረምረቱ ቆይታ በመንገድ ጉዳይ ሲቸገር ቆይቷል። ለችግሩ አስቸኳይ መፍትሄ ለመስጠት ከተመረጡት ባለሙያዎች አንዱ አቶ ሲሳይ ሆኗል።

አባወራው ከቤቱ ደርሶ ስለሚሄድበት ስራ ከቤተሰቡ አወጋ። ጊዜ በሚፈጀው የመንገድ ስራ መመለስ የሚታሰብ አይደለም። ለዚህ መፍትሄ ስራው እስኪጠናቀቅ በከተማው ቤት ይከራያል። ከቆይታ በኋላ ሻንጣውን ይዞ ሚስትና ልጆቹን ተሰናብቶ ከቤት ወጣ። ሁሉም በፍቅር ዓይን እያዩ ከደጅ ወጥተው ተሰናበቱት።

ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን ባለሙያዎቹን የጫነው የመስሪያ ቤቱ መኪና ግቢውን ለቆ ወጣ። ሰራተኞቹ ቦንጋንና አካባቢውን ርቀው ኪሎ ሜትሮችን ተሻገሩ። ሁሉም በየድርሻቸው የተመደቡበት የሙያ ዘርፍ ተሰጥቷቸዋል። ሲሳይ ከመስሪያ ቤቱ የጀመረው የማስፋፊያ ስራ ቢኖርም አንገብጋቢ ነው ወደተባለው ቦታ ሊሄድ ግድ ብሏል።

አቶ ሲሳይ በጉዞ ላይ ሳለ የእጅ ስልኩን አነሳ። ለባለቤቱ መንገድ መጀመሩን አሳውቆ ጥቂት አወራት። የትዳር አጋሩ በቸር ደርሶ እንዲመጣ ተመኘችለት። ከታሰበው ለመድረስ የመኪና ፍጥነት ቀጥሏል። መንገዱ ወጣ ገባ የገጠር ጎዳና ነው። ለስራ የሚሄድበት አዲዮ ወረዳ ደግሞ ከዚህ የባሰ ውጣውረድ ይቆየዋል። በሀሳብ እየተብሰለሰለ መነሻውን ወደ ኋላ ትቶ ወደፊት ተጓዘ።

ሰአቱ ለዓይን መያዝ እንደጀመረ የመኪናው ተጓዦች ካሰቡት ወረዳ ደረሱ። አቶ ሲሳይን ጨምሮ ሌሎች ሻንጣቸውን አውርደው ማደሪያቸውን አሰቡ። ሲሳይ ለስራ እንደሚዘልቅ በማወቁ የኪራይ ቤት አዘጋጅቷል። ጓዙን ይዞ ወደማረፊያው አቀና። ቤቱ ደርሶ ጥቂት ከማረፉ የእጅ ስልኩ አቃጨለ። የቤተሰቡ ጥሪ ነው ።

በሰላም መግባቱን ጠየቁት። ሁሉም ሰላም መሆኑንና ነገ ስራውን እንደሚጀምር አሳወቃቸው። ከቤተሰቡ ተደጋጋሚ የስልክ ጥሪዎችን ተቀበለ። ሁሉንም በምስጋና አሰናብቶ ሞባይሉን ተጫኔና ሰአቱን ተመለከተ። ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ከሰላሳ ይላል። ወደከተማ ዘልቆ እራት መብላትና ጓደኞቹን ማግኘት እንዳለበት አሰበ። ጊዜ አልፈጀም። ከእጁ ያለውን አስቀምጦ ጃኬቱን ደረበና ወደባልንጀሮቹ መገኛ አመራ።

ጊዜው እየመሸ ነው። ሲሳይ ለአካባቢው አዲስ ቢሆንም እንግድነት አልተሰማውም። ባልንጀሮቹ ያሉበትን ሆቴል ነግረውታል። ጥቂት ተራምዶ እነሱ ካሉበት ደረሰ። ጠረጴዛ ከበው ተቀምጠዋል። ሰላም አላቸውና ወንበር ስቦ እነሱን መሰለ። ሁሉም የአንድ ድርጅት ባልደረቦች ናቸው። ሲገናኙ ጨዋታው ደራ። ስለስራ ፣እያነሱ፣ ስለህይወት እያወጉ ቆዩ።

ከምሽቱ አንድ ሰአት ከሰላሳ ከማለቱ የሲሳይ የእጅ ስልክ አቃጨለ። ሴት ልጁ ነች። ስለመንገዱ ጠየቀችው ። በሰላም መግባቱን መለሰላት። ጥቂት ቆይቶ ከሚጠጣው እንዲጨመር ታዘዘ ። ባልንጀሮቹ እየተጫወቱ ከመጠጡ ደጋገሙ። ሲሳይ የጓደኞቹን ሂሳብ ለመዝጋት ፈልጓል። በኪሱ ያለውን ሂሰብ አሰበው። ሙሉን ወጪ የሚሸፍን አይደለም። ቤት ደርሶ አሟልቶ ለመክፈልና እራቱን ጭምር ለመብላት ፈለገ። ይህን ለማድረግ ተመልሶ ከተከራየው ቤት መሄድ አለበት።

ሲሳይ ቤት ገብቶ ያሰበውን ይዞ ሲመለስ ከምሽቱ ሁለት ሰአት አልፎ ነበር። ገንዘብ ተቀባይዋ ዘንድ ደርሶ ሂሳቡን ዘጋና ወንበር ስቦ ተቀመጠ ። የቤቱ ባለቤት በክፉ ዓይኖቹ አተኩሮ እያየው ነው። ጸጉረ ልውጥ መሆኑና ተመልሶ መምጣቱ የተመቸው አይመስልም። ሰውዬው እንግዳውን በግልምጫ እያነሳ ወደ ገንዘብ ተቀባይዋ ተጠግቶ ስለ ማንነቱ ጠየቃት።

ገንዘብ ተቀባይዋ ሂሳብ ለመዝጋት ተመልሶ መምጣቱንና አሁንም እየተስተናገደ መሆኑን ተረጋግታ መለሰችለት። የሆቴሉ ባለቤት የሲሳይን ድርጊት በበጎ አላየውም። እንደተናደደ እጁን ጨብጦ ከፊት ለፊቱ ተገተረ። ሲሳይ ሁኔታው ቢያስደንቀው ምክንያቱን ለመጠየቅ ሞከረ። ሰውዬው ለምላሹ ጊዜ አልነበረውም። ዓይኑን አፍጥጦ፣ ጥርሱን አግጥጦ አንገቱን ለማነቅ ተንደረደረ ። አንዳች ትንፍሽ ያላለው እንግዳው ሲሳይ የእጁን ብርጭቆ አስቀምጦ ወደውጭ ለመውጣት ተነሳ። ይህን ያስተዋለው የሰውዬው የቅርብ ጓደኛ ከወደኋሮ ብቅ ብሎ እንዳይንቀሳቀስ አገደው። ሌሎች ሁለት ሰዎች ተጨምረውም ራሱን እንዳይከላከል እጆቹን አጥብቀው ያዙ።

ሲሳይ ወጥቶ ከመሄዱ በፊት ድንገት በተነሳው አለመግባባትና ግጭት የቤቱ ሁኔታ ተረበሸ ። ገላጋይ መሳዮቹ ሰዎች ሲሳይን እያንገላቱ ለቤቱ ባለቤት አሳልፈው ሰጡት። ግርግር፣ ጩኸትና ወከባው አየለ። በዚህ መሀል ሲሳይ በአንዳች ነገር ጀርባው ጠልቆ ሲወጋ ተሰማው። ስቃዩን ችሎ ራሱን ለማስለቀቅ ታገለ። ብዙ አልቆየም ። በቀኝ ጭንቅላቱ በኩል ተመሳሳይ ጥቃት ሲያርፍበት ራሱን ስቶ ተዘረረ።

**ታህሳስ 5 ቀን 2010 ዓም...**

ማለዳ ከዕንቅልፏ የተነሳችው ወይዘሮ እንደወትሮዋ የዕለት ስራዋን ልትከውን ጥድፊያውን ይዛለች። በዚህ ሰዓት ከቤት ወደየጉዳዮቻቸው ለመውጣት ለሚዘጋጁ ልጆቿ ቁርስ ለማድረስ ትባትላለች። በሌሊት ልብሷ ነች። ድንገት በሩን ከፍታ ወደውጭ አስተዋለች። አካባቢው ባልተለመደ ሁኔታ በሰዎች ተጨናንቋል። በሁሉም ፊት ላይ ሀዘንና ጭንቀት እየተነበበ መሆኑ ቢገባት ክፉኛ ደነገጠች ። በቦታው ምን እንደተፈጠረ እስኪታውቅ እግሯቿ ብርክ ያዛቸው። የምታያቸው ሁሉ ወደእሷ ቤት እየተመለከቱ ነው። ውስጧ በፍርሀት ራደ፣ተንቀጠቀጠች።

ተመልሳ ወደቤት ገባችና ሴት ልጇ ለወንድሞቿ እንድትደውል አጣደፈቻት። ልጅቷ ቀድማ ለአባቷ ደወለች። ስልኩ አይመልስም። እየተጣደፈች አንደኛው ወንድሟ ዘንድ ደወለችና የሚያውቁት ነገር እንዳለ ጠየቀች። በቂ ምላሽ አላገኘችም። ቤት የነበረው ወንድሟ ከሌላው ወንድሙ ጋር በስልክ እያወራ ከቤት ወጣ። ክፉኛ ተረብሸዋል።

የአባቱ መስመር ባለመስራቱ የተጨነቀው ወጣት ድንገት ከአንድ ሰው የደረሰው የስልክ መልዕክት ይበልጥ አስደንግጦታል። ደዋዩ የአባቱ የስራ ባልደረባ ነው። ለማንም ሳይናገር መስሪያ ቤት እንዲመጣ ነግሮታል። ወጣቱ ሌሎች ሰዎችን አስከትሎ ከተባለው ስፍራ ደረሰ። ለጉዞ የተዘጋጁ መኪኖች እነሱንና ጥቂት ባልደረቦችን ይዞ ወደ አዲዮ ወረዳ አቅጣጫ ተፈተለከ ።

የአቶ ሲሳይ ልጆች ካሰቡት ደርሰው አባታቸውን ሊያገኙ ቸኩለዋል። በድንገት መጠራታቸው ብዙ እያሳሰባቸው ነው። ሲሳይ ለስራ ከወጣ ገና አንደኛ ቀኑ ነው። ከማንም እንደማይጋጭ፣ እንደማይጣላ ያውቃሉ። ምንአልባት ትንሽ አሞት ሊሆን ይችላል። ታዲያ ስልኩ ለምን አይሰራም?ለምንስ አላወራቸውም ? ክፉኛ ተጨንቀዋል።

**በአዲዮ ወረዳ - ከፖሊስ ጋር**

ከቦንጋ የተነሳው የድርጅቱ መኪና አዲዮ ወረዳ ሲደርስ የአካባቢው ፖሊሶች ተቀበሏቸው። ልጆቹና አብረዋቸው ያሉት ፊትና ኋላ ሆነው ፖሊሶቹን ተከተሉ። ሁሉም በቅርብ ርቀት በርከት ያሉ ሰዎች መኖራቸውን አስተውለዋል። ፡የልጆቹ ዓይኖች እነሱን አሻግሮ ሌላውን ተመለከተ። አባታቸው ከአንድ ቦይ ላይ በጀርባው ተንጋሎ ወድቋል ። እየተጣደፉ አጠገቡ ደረሱ። ደግመው ፣ደጋግመው አዩት፣አላያቸውም። እየጮሁ፣እያለቀሱ ወዘወዙት፣ ጠሩት ፤አልሰማቸውም።

**ትናንትና ምሽት..**

ለሆቴሉ ባለቤት አግዘው ሲሳይን ለጥቃት የሰጡት ሰዎች ለአገሩ እንግዳ የሆነውን ሰው ተባብረው በስለት ወግተውታል። ሁኔታውን ያስተዋሉ ጥቂቶች ለመገላገል ዕድል አላገኙም። ህይወቱ ማለፉን የተረዱት ግለሰቦች በድኑን ከስፍራው ለማሸሽ የአካባቢው መብራት ዕንቅፋት ሆኗቸዋል። አስከሬኑንም ለሰአታት በኮሪደሩ አቆይተው ከመንገድ ለመጣል በመስማማት እንዳሰቡት አድርገዋል።

ሌቱ ነግቶ ጸሀይ መውጣት ስትጀምር በከተማው የታየው እውነት ብዙዎችን አስደነገጠ። ለነዋሪው በስለት ተወግቶ ከጎዳና የተጣለውን ሰው መለየት ቀለል አልሆነም። እንግዳው የመንገድ ሰራተኛ ህይወቱን የተነጠቀው ከተከራየበት ቤት ለአንድም ቀን ሳያድርና የመጣበትን ሥራ በወጉ ሳይጀምር ነበር ።

የአካባቢው የጸጥታ አካላት የሟችን ማንነትና የድርጊቱን ፈጻሚዎች ለማወቅ ጊዜ አልፈጀባቸውም። ተጠርጣሪዎቹን በህግ ቁጥጥር ስር አዋሏቸው። የወረዳው መርማሪ ፖሊስ ረዳት ሳጂን በላቸው በዛብህ የሁለቱን ሰዎች ቃል ለመቀበል ከፊታቸው ቀረበ። ተጠርጣሪዎቹ የፈጸሙትን የነፍስ ግድያ ወንጀል አልካዱም። ለስራ ጉዳይ በወረዳው የተገኘውን የመንገድ ስራ ባለሙያ ተባብረው በግፍ መግደላቸውን አመኑ። መርማሪው ቃላቸውን በበቂ ማስረጃዎች አስደግፎ ለቀጣዩ የክስ ሂደት መዝገቡን ለዓቃቤህግ አስተላለፈ።

## ውሳኔ...

የካቲት 2 ቀን 2010 ዓ.ም በችሎቱ የተሰየመው የከፋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በነፍስ ማጥፋት ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው የተባሉትን ሰዎች ክስ ሲከታተል ቆይቷል። ፍርድ ቤቱ በተለያዩ መረጃና ማስረጃዎች ተጠናክሮ የቀረበለትን መዝገብ ካየ በኋለ በሰጠው ውሳኔም አንደኛ ተከሳሽ በ23 ዓመት ጽኑ እስራት፣ ሁለተኛው ተከሳሻ ደግሞ በ19 ዓመት ጽኑ እስራት ይቀጡልኝ ሲል ብይን ሰጥቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ከዓባይ ጋር ምናባዊ ቃለ ምልልስ

**ዋለልኝ አየለ**

ዛሬ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት 11ኛ ዓመት ነው። ቀኑን ለየት የሚያደርገው ደግሞ የመሠረት ድንጋይ የተጣለበት ዕለት ልክ እንደ ዛሬው ቅዳሜ ነበር። ሌላ ለየት የሚያደርገው ደግሞ በዚህ ዓመት የመሠረት ድንጋይ የተጣለበትን ቀን የምናከብረው ኃይል የማመንጨት ሥራውን በጀመረበት ዓመት መሆኑ ነው።

ስለ ዓባይ በሰፋፊና ጥልቅ ትንታኔዎች፣ በቃለ መጠይቆች፣ በዜናዎች በብዙ ተብሏል። እስኪ በዚህ ዓምድ ደግሞ ከጠንካራ ሀሳቦች (Hard Issue) ወጣ እንበልና ዓባይን ምናባዊ ቃለ መጠይቅ እናድርግለት።

ግድቡ በተገባደደበትና በዚህ ኃይል ማመንጨት በጀመረበት ዓመት ዓባይ ከሰው ጋር ቢያወራ ምን ይል ይሆን? ብለን አሰብን። ምናባዊ ቃለ ምልልስ እናድርግለት። የህዳሴው ግድብ የሚገነባበትን ቦታ ታሳቢ በማድረግ የዚህ ምናባዊ ቃለ ምልልስ አድራጊ ጋዜጣ ጉባ ተብሎ ተሰይሟል። የጉባ ጋዜጣ ጋዜጠኛ ዓባይነህ ከዓባይ ጋር ቆይታ አድርጓል፤ መልካም ንባብ።

**ጉባ፡- እስኪ በመጀመሪያ ራስህን አስተዋውቅ?**

**ዓባይ፡-** ዓባይ እባላለሁ።

**ጉባ፡- ሰፋ አድርገህ አስተዋውቅ፤ ዓባይ የሚባል እኮ ብዙ ሰው አለ፤ ሰው ብቻ ሳይሆን ዓባይ እየተባለ የተሰየመ ስንትና ስንት ነገር አለ። የትኛው ዓባይ ነህ?**

**ዓባይ፡-** አሁንማ በቃ ተደፋፈርከኝ አይደል? እኔ ዓባይ ወንዙ ነኝ ብዬ ልንገርህ? መቼም አታፍርም ዓባይ ማለት ወንዝ መሆኑን የማያውቅ ይኖራል ትለኝ ይሆናል እኮ።

**ጉባ፡- ይሄ ትውልድ የአገር ፍቅር የለውም፣ ታሪኩን የዘነጋ ነው እየተባለ ይታማል፤ ታዲያ ይሄ ትውልድ የተምታታበት ከሆነ ዓባይ ወንዝ መሆኑን የማያውቅ ይኖራል ብዬ ብሰጋ ምን ችግር አለው?**

**ዓባይ፡-** የተምታታብህ ራስህ ነህ ባክህ! ይሄ ትውልድ የአገር ፍቅር የሌለው ሳይሆን ያለው ነው። ለዘመናት በአይነኬነት ስመለክ የኖርኩትን አግዶ ያስቀረኝ ታዲያ ይሄ ትውልድ ነው እንጂ ሌላ ማነው?

**ጉባ፡- ስለዚህ የዚህ ትውልድ አድናቂ ነህ ማለት ነው?**

**ዓባይ፡-** አንተ ማድነቅ አለብህ ማለቴ ነው እንጂ፤ እኔማ ምኑን አደንቀዋለሁ። ስንት ሺ ዘመን ተፈርቼና ተከብሬ፣ አገር ምድሩን አቋርጬ እስከ ሜዲትራኒያን ባህር ድረስ እንዳላጓራሁበት ሁሉ አንድ ቦታ አግዶ ሲያስቀረኝ እንዴት ላደንቀው እችላለሁ? በእርግጥ ድፍረቱን አደንቃለሁ!

**ጉባ፡- አግዶ እንዳስቀረህ አመንክ ማለት እኮ ያው አደነቅከው ማለት ነው። ስመሆኑ የድሮ ጀግንነትህ ምን ነበር?**

**ዓባይ፡-** ወይ! መደፋፈር፤ እውነት አሁን የድሮ ዝናዬን ስተኸው ነው? እንደተገደብኩ አይተህ ነው እንጂ አንተስ ካጠገቤ ዝር ትል ነበር? አላውቅህም እንዴ አፉፍ ላይ ቆመህ «ዓባይ ጉደል ብለው አለኝ በታህሳስ፤ የማን ሆድ ይቆያል እስከዚያ ድረስ» እያልክ ትዘፍን እንደነበር።

**ጉባ፡-እረ ዓባይ ወደ ዋናው ቃለ ምልልስ ከመግባታችን በፊት ስለውልደትህና አስተዳደግህ ትንሽ እናውራ።**

**ዓባይ፡-** ጀምስ ብሩስን ጠይቀው፤ ከአጠገብህ ተነስቼ የዓለም አገራትን አቆራርጬ ስጓዝ የዓለም ተመራማሪዎች ስለእኔ ብዙ ሲጽፉ የት ነበርክ? ጭራሽ የት ተወለድክ ትለኛለህ እንዴ?

**ጉባ፡- ስለሽ ደምሴ(ጋሼ አበራ ሞላ) እንደዘፈነው ከሆነ አባትህ ደጄን እናትህ ጣና ናቸው ማለት ነው?**

**ዓባይ፡-** ሂድና ራሱን ጠይቀው።

**ጉባ፡- ቆይ ግን ምንድነው እንዲህ የሚያነጫንጭህ? ዛሬም እንደ ድሮው የምፈራህ መሰለህ እንዴ! ከፈለክ አሁንም ሌላ ቦታ እንዳልገድብህ።**

**ዓባይ፡-** ሆሆሆሆሆ! ወደው አይስቁ አሉ። እሱማ እኮ የጀግኖች ነው። ምንህ እንዳሳቀኝ ታውቃለህ? አንተ ለአንባቢዎችህም ብለህ ይሆናል፤ ግን እኔን የት ተወለድክ? የት አደክ? ብለህ ስጠይቅ አንባቢም ይስቅብሃል። ከዚያ አልፈህ ደግሞ እገድብሃለሁ ትላለህ። እኔን የገደቡ እኮ ስለማንነቴ አንጠርጥረው የሚያውቁ፤ ከየት ተነስቼ የት እንደምሄድ የገባቸው ናቸው። ዝም ብለህ ምንም ሳታውቅ አፍህ እንዳመጣ እገድብሃለሁ እያልክ አታስፈራራ። ደግሞ ከአሁን በኋላ የምፈራ እንዳይመስልህ! ሜዲትራኒያ ማደሪያዬ እንደነበር ሁሉ ጉባም ማደሪያዬ ይሆናል።

**ጉባ፡- ግንድ ይዘህ ከመዞር በስተቀር ማደሪያ የለህም አልተባለም ነበር እንዴ?**

**ዓባይ፡-** እሱማ ተረት ሆነ እኮ። አሁን ግንድ ይዘህ የምትዞር ራስህ ነህ።

**ጉባ፡- ደግሞ እኔ የምን ግንድ ነው ይዤ የምዞር?**

**ዓባይ፡-** ብትፈልግ የዋርካ፣ ብትፈልግ የዋንዛ(ሃሃሃሃ) ያው መቼም መብራት ለማስገባት በየገጠሩ እየዞራችሁ የመብራት እንጨት መትከላችሁ አይቀርም ብዬ ነዋ!

**ጉባ፡- እስኪ ለሰዎች ጥቅም መስጠትህን ካነሳኸው አይቀር ከጥንት እስከ ዛሬ ምን ጥቅም ሰጥቻለሁ ብለህ ታስባለህ?**

**ዓባይ፡-** በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው። እንግዲህ እስከዛሬ የሰጠሁትን ጥቅም በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን።

**ጉባ፡- ደግሞ አንተም እንደ ምሁራን ‹‹በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን›› እያልክ ማብራራት ጀመርክ? እስኪ ምን ምን ናቸው?**

**ዓባይ፡-** ደግሞ አትዘባርቅ! ዝም ብለህ አዳምጠኝ። በሁለት መከፈል ያለበት ነገር ካለ ይከፈላል። ለምሳሌ እኔ በሁለት ይከፈላል ያልኩህ ድሮ የምሰጠውን ጥቅምና አሁን የምሰጠውን ጥቅም ነው።

**ጉባ፡- እስኪ ድሮ ምን ነበር? አሁንስ ምንድነው?**

**ዓባይ፡-** ድሮ ድሮ ጥቅም የምሰጠው ለቅኔ፣ ለፉከራና ለቀረርቶ ነበር። ብዙነትን፣ ኃይለኝነትን፣ ተጓዥነትን... ለመግለጽ፣ በሌላ በኩል የአባባሎች ምንጭ ነበርኩ። በየጎራው እየወጣህ «እንዴት አምሮበታል ጭስ ዓባይ ዘንድሮ» እያልክ ታቅራራብኝ ነበር። እኔ አትገናኙ ያልኩ ይመስል «ከዓባይ ማዶ ሆነሽብኝ» እያለ እየየውን ያንጎራጉርብኛል።

**ጉባ፡- ዓባይ እዚህ ላይ ላቋርጥህና እኔ አትገናኙ ያልኩ ይመስል ያልካት ነገር አልተዋጠችልኝም። ለምሳሌ ድልድይ ከመኖሩ በፊት ከአንተ ማዶና ማዶ ያሉ ተፋቃሪዎች እንዴት ይገናኙ ነበር? የበጋ ወቅትን ጠብቀህ ጎደል ስትል ዘመድ አዝማድ ይጠያየቃል። በዚያው ደግሞ ከአንተ ማዶ ፍቅር ይዞት ይመጣል። ግራ ቢገባው እኮ ነው «አንቺ ወዲያ ማዶ እኔ ወዲህ ማዶ፤ አንገናኝም ወይ ተራራው ተንዶ!» ብሎ የዘፈነው።**

**ዓባይ፡-** ሃሃሃሃ! አንዳንድ ዘፈኖቻችሁ ደግሞ ያስቁኛል። ተራራ ነው እንዴ ያለያየው እኔ ነኝ እንጂ። እስኪ አሁን ማን ይሙት የውሃ መጉደልን ከተራራ መናድ ጋር ምን አገናኘው?

**ጉባ፡- ዓባይ ስለቅኔ እናውራ ከተባለ ከባድ ነው። ይህኔ እኮ ተራራ የተባለው ነገር አንተ ልትሆን ትችላለህ። ተራራው ይናድ የተባለው አንተን ጉደል እንደማለት ሲሆን ይችላል። ግጥም ደግሞ ብቻውን እንደማይፈታ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ቆይ ግን ድሮ ለቅኔና ለቀረርቶ ይጠቀሙብኝ ነበር አልክ። አሁን በአንተ ላይ መቀኘትና ማቅራራት አይቻልም እንዴ?**

**ዓባይ፡-** አይ! እንደ ድሮው አይደለም። በዚያ ላይ ደግሞ የአሁኑና የድሮው በጣም የተለያየ ነው። ድሮ አይነኬው፣ ጀግናው..... የሚሉ ነገሮች ናቸው የሚበዙት። አሁን ግን ቅኔውም ፉከራውም እኔን ስለማሸነፍ ነው።

**ጉባ፡- ቆይ አንተ ግን አሥር ጊዜ ተሸነፍኩ ተሸነፍኩ የምትል ምን ጎድሎብህ ነው? ሜዲትራኒያም ገባህ፣ ጉባም ታገድክ ለአንተ ምን ልዩነት አለው?**

**ዓባይ፡-** ኧረ እባክህ! እዚያ ስሄድ እኮ የዓለም አገራትን እያቆራረጥኩ ነው። ለም አፈርን እየጠራረኩ እየበላሁ ነው። መታገዴ ሳያንስ አሁን ደግሞ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ በማለት አፈርም እንዳላገኝ አደረጋችሁኝ። ታዲያ ለምን ተደፈርኩ አልል ጉባ?

**ጉባ፡- ነገርህ ሁሉ ዓባይን በጭልፋ እየሆነብኝ ነው።**

**ዓባይ፡-** እንዴት?

**ጉባ፡- ስለአንተ ብዙ ነገር ማውራት ይቻላል። ግን ከምን ጀምሬ በምን እንደምጨርሰው ግራ ገባኝ። እንግዲህ ልንሰነባበት ነውና ዝም ብዬ ዕድል ልስጥህ። እስኪ በመጨረሻ ምን ታስተላልፋለህ?**

**ዓባይ፡-** በመጨረሻ የማስተላልፈው ኤሌክትሪክ ነው።

ጉባ፡- ሃሃሃሃ! በእውነት ይህን ቀልድ ልጅ ያሬድ ከቀለደው በላይ ያሳቀኝ ዛሬ ነው። በዚህ ቀልድህ ላይ ምንም ነገር ሳልደርብበት ሰላም ሁን! መልካም ኤሌክትሪክ ማስተላለፍ!

# ዓለም አቀፍ



## የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል እንዲጠናከር ጥሪ ቀረበ

አዲስ አበባ፡- የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል በአካባቢው ያለውን የሠላምና ደህንነት የሚመጥን ወቅታዊ አቅም ሊኖረው እንደሚገባ ተገለጸ።

የኢፌዴሪ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹምና የምሥራቅ አፍሪካ የጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹሞች ኮሚቴ ሊቀመንበር ፊልድማርሻል ብርሃኑ ጁላ ናይሮቢ ውስጥ ባደረጉት ንግግር፣ ተጠባባቂ ኃይሉ በአካባቢው ካለው የሠላምና የፀጥታ ሁኔታ ጋር የሚመጥን ቁመናና ዝግጅት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የተጠባባቂ ኃይሉ የያዝነው ዓመት የሁለት ሳምንት ስልጠና ትናንት በናይሮቢ ተካሂዷል።

ኢትዮጵያ ለምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይሉ ጥንካሬ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደምታደርግ ገልጸው፣ አባል አገራት የፖለቲካ ቁርጠኝነታቸውንና የሚሰጡትን ድጋፍ እንዲያሳድጉም ጥሪ አቅርበዋል።

የተቋሙ አባል አገራት ሰልጣኞችን በማሰማራት ላደረጉት አስተዋጽኦ ፊልድማርሻል ብርሃኑ ምስጋና አቅርበዋል።

የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ብርጋዴር ጄኔራል ጌታቸው ሽፈራው በበኩላቸው፣ በስልጠናው የተገኘው ልምድ ተጠንቅቆ ኃይሉ ቀደም ሲል የነበረውን አቅም ለማሳደግ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

በዚሁ የኮማንድ ፖስት ስልጠና ላይ የኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሱዳን፣ ዩጋንዳ፣ ርዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ሲሸልስ፣ ኮሞሮስ፣ የአገር መከላከያ፣ የፖሊስ እና የሲቪል አካላት ተሳታፊ መሆናቸውን ተቋሙ ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት በላከው መግለጫ አመላክቷል።

ኤታማዦር ሹሙ ቀደም ሲል ከኬንያ የመከላከያ ሚኒስትር ዩጂን ዋማሉዋ እና ሮበርት ኪቢቾ ጋር በነበራቸው ውይይት ተቋሙን በማጠናከር ረገድ ኢትዮጵያና ኬንያ የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ መግባባት ላይ መድረሳቸው ይታወቃል።

ኢትዮጵያና ኬንያ በመልካም ብቻ ሳይሆን በአስቸጋሪ ወቅቶችም ጠንካራ ወዳጆች ናቸው ያሉት የኬንያ የመከላከያ ሚኒስትር ዩጂን ዋማሉዋ የአሁኑ ትውልድም ይህን ከፍ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

## የዩናይትድ ስቴትሱ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አሜሪካ ለችግር ጊዜ በሚል ካከማቸችው ነዳጅ በገፍ እንዲቀዳ አዘዙ

የዩናይትድ ስቴትሱ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን አሜሪካ ለችግር ጊዜ በሚል ካከማቸችው ነዳጅ በገፍ እንዲቀዳ አዘዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ ይህን ትዕዛዝ ያስተላለፉት እየናረ የመጣውን የነዳጅ ዋጋ ለመዋጋት ነው።

ባይደን እንዲወጣ ያዘዙት 180 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ በማከማቻው ታሪክ ትልቁ ነው።

ዩክሬን ባለው ጦርነት ምክንያት ጣራ እየነካ የነበረው የነዳጅ ዋጋ ከባይደን ትዕዛዝ በኋላ ትንሽ ረገብ ብሏል።

ነገር ግን አሜሪካ በየቀኑ ለመከራ ጊዜ ካስቀመጠችው ነዳጅ አንድ ሚሊዮን በርሜል ብትቀዳም ችግሩን ሙሉ በሙሉ አይቀርፈውም ይላሉ የዘርፉ ሰዎች።

ባይደን፤ ከማከማቻው እንዲቀዳ የታዘዘው ነዳጅ አሜሪካ «የራሷን የነዳጅ ምርት እስከታሳልጥ ድረስ» እንዲያግዝ በሚል ነው ብለዋል።

ፕሬዚዳንቱ ኩባንያዎች ነዳጅን ከመንግሥት መውሰድ የመጨረሻ አማራጭ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

ባይደን አረንጓዴ የኃይል ምንጭ የሚከተሉ ኩባንያዎች እንዲበረታቱ መክረዋል።

በሚቀጥለው ኅዳር የግማሽ ዓመት ምርጫ ለማካሄድ ደፋ ቀና እያለች ያለችው አሜሪካን ጨምሮ የዓለም አገራት የኑሮ መወደድ እያማረራቸው ነው።

ባይደን፤ ስትራቴጂክ ፔትሮሊዬም ሪዘርቭ ከተሰኘው የችግር ቀን ገንዳ ነዳጅ ለመቅዳት የወሰንነው «ያለዕቅዳችን» ነው ብለዋል።

ይህ ግዙፍ የነዳጅ ማከማቻ ገንዳ የተመሠረተው በፈረንጆቹ 1974 ነው።

ማከማቻው ቴክሳስና ሉዊዚያና መካከል በሚገኘው የገልፍ ኮስት ላይ በተንጣለለው የጨው ክምር አካባቢ ይገኛል።

ይህ ገንዳ በፈረንጆቹ 2009 700 ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ አቅፎ ነበር። ባለፈው መጋቢት ሲለካ ግን የነዳጅ ክምችቱ ወደ 568 ሚሊዮን በርሜል ወርዷል።

አሜሪካ ከሳዑዲ ቀጥሎ ሁለተኛዋ ግዙፍ የነዳጅ አምራች ከሆነችው ሩሲያ ነዳጅ አልገዛም ካለች ወዲህ የነዳጅ እጥረት እያንገላታት ይመስላል።

የነዳጅ ዋጋ መለኪያ የሆነው ብሬንት ክሩድ ባለፈው የፈረንጆቹ ወር መጀመሪያ ዋጋ አሜሪካና አጋሮቿ ሩሲያ ላይ ማዕቀብ ከጣሉ በኋላ አሻቅቧል።

ምንም እንኳ የኃይል ዋጋ ቀስ በቀስ ቢወርድም ነዳጅ ግን ከባለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር ዋጋው 70 በመቶ ጨምሯል።

አሜሪካ ውስጥ እየናረ የመጣው ኑሮ ሪፐብሊካን ጮቤ እንዲረግጡ እያደረጋቸው ነው። የባይደን ተቃዋሚዎች የኑሮ ውድነቱን በባይደን አስተዳደር አላከዋል።

አሁን ደግሞ ነዳጅ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ዋጋው ሲያሻቅብ የባይደን አስተዳደርን ከድጡ ወደ ማጡ መርቷቸዋል።

ባለፈው ሐሙስ ሩሲያን ጨምሮ የነዳጅ አምራች አገራት ማህበሩ ኦፔክ አባላት የነዳጅ ምርታቸውን ለመጨመር ተስማምተዋል።

የኃይል ዋጋ ከዩክሬን ጦርነት በፊትም ቢሆን የዓለም ምጣኔ ሀብትን ሊፈታተነው እንደሚችል ግምት ነበር።

ምንጭ ቢቢሲ

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

## መከዳትን መክዳት

በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ

አምቡላንሱ በሚያሰማው ጩኸት መኪኖች መንገድ እንዲለቁለት እየጠየቀ በቻለው ፍጥነት እየከነፈ ነው። እያንዳንዱ ሴኮንድ በአምቡላንሱ ውስጥ ላለችው ከሞት ጋር ትግል ውስጥ ለገባችው ወጣት ትርጉም አለው። ሞትን ማስቀረት ወይንም ልጃቸውን ከማጣት ውጪ ሌላ አማራጭ የሌላቸው የቤተሰብ አባላት በተለያየ መንገድ የአምቡላንሱ መዳረሻ ወደሆነው ሆስፒታል እያመሩ ነው፤ ድንገተኛ አደጋ፤ በመከዳት ውስጥ የተወለደ፤ ከሞት ጋር ፊትለፊት ያገናኘ።

ወጣቷ ራሷን ስታ እንድትወድቅ ያደረጋት የመከዳት መዝገብ ፍንትው ሲል በእጇ የነበረው ሃብት ሁሉ ወደ ሌላ ሰው ዞሮ ያገኘችበት ቅጽበት። ነገሮች ያለቁ ሆነው በተሳለላት ጊዜ ህይወቷን ለማጥፋት የወሰደችው እርምጃ በቤተሰብ አባላት ጣልቃ ገብነት የተጨናገፈ ሆኖ ህይወት በማለሚያ ሙጣጭ ውስጥ ትገኛለች። አንዳች ተስፋ፤ ከአምቡላንሷ ጩኸትና ከሚረጨው እምባ ውስጥ።

በሌላው ጎራ ከወጣቷ ጀርባ ሲያደባ የነበረው በፍቅር ቃላት ቀርቦ በልቧ በር በኩል ሰተት ብሎ ገብቶ ያላትን ሲያራቁት፣ ሁሉ ነገሯን ለእርሱ ሰጥታ የተደላደለችበት ሰው። “ጨዋታው አለቀ/game over” በሚል በክፋት ጥግ አመታትን በወሰደበት ፕሮጀክት በድል መጠናቀቅ ምክንያት ሊጠጣው የቀረበው መጠጥ ጥንካሬውን ከፍ ያለ አድርጎታል። ተሸንፈው ሳሉ ራስን አሸናፊ አድርጎ የማቅረብ ውድቀት።

ጨዋታውን ፈጻሚ ግለሰብ የፖሊስ የምርመራ መዝገቦች ውስጥ የሚሰሙ ዘግናኝ ታሪኮች ጀርባ ያለው የጭካኔ ጥግ በወረሰው ማንነቱ ውስጥ ሆኖ ራሱ ፈጥሮ፤ ራሱ ተውኖ፤ ራሱን ተመልካች አድርጎ በሰራው ተውኔት ውስጥ ይገኛል። የሲኒማው አዳራሽ ወንበሮች በሙሉ በእርሱ መክዳትን ልብሱ ባደረገው ግለሰብ ተሞልተዋል። በስክሪን ላይ በሚታየው ፊልም ውስጥ ግን ንጹህ ልብ፤ የተከዳው ልብ፤ ህያውነት በሙላት የነበረበት ልብ፤ እንዴት ሲማረክ እንዴትም የራሱ ሲያደርግ እንዴትም ሲሰብረው እንዴትም ወደ ሞት እንዳደረሰው ይመለከታል፤ ጨዋታው አልቋልና “ተፈጸመ” እያለ ይመለከታል። በክፋት ጥግ በሰሩት የጭካኔ ተግባር ከመጸጸት ይልቅ፤ ክፋቱን መላልሶ እንደ ፊልም ተመልክቶ ራስን አሸናፊ አድርጎ ከማቅረብ በላይ ምን አይነት ውድቀት አንድ በህይወቱ ያለ ሰው ሊወድቅ ይችላል?

ልብስን አውልቆ ጥሎ ሌላኛውን ልብስ ለብሶ በአዲስ የፊልም ታሪክ፤ በአዲስ አቅርቦ የመግደል ታሪክ ውስጥ መሪ ተዋናይ አድርጎ ራስን ማቅረብ። ከተሳካ እስከ ጫፍ ድረስ መሄድ፤ ካልተሳካ በየመንገዱ ባለው ቅንጭብጫቢ ተደስቶ መራመድ። ህይወትን በማጨንገፍ ውስጥ ህይወትን ለመኖር በመሞከር ራስን አትራፊ መስሎ ማቅረብ።

ወደ ሞት ከሚደረግ ጉዞ ለመዘግየት የሚደረገው ግብግብ ቀጥሎ አምቡላንሷ ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ደረሰች። ተስፋን ሊመልሱ ነጩን ጋውን የለበሱ የህክምና ባለሙያዎቹ ያላቸውን ሊሰጡ ሩጫው ውስጥ ገቡ። ከቅርብ እርቀት ሲከተል የነበረው የሞት ኮቴ በህይወት ምስቅልቅል ውስጥ ባለች ነፍስ ውስጥ ሊነግስ እየፈጠነ ስለ ሰው ቃለመሃላ የፈጸሙት ስለ አንዳች መፍትሔ እየደከሙ ነው። ለሌሎች ለመኖር እጃቸውን አንስተው ቃል የገቡት ሐኪሞች በበዛው ትጋታቸው፤ በፈጣሪም ጣልቃ ገብነት የሞቱ ኮቴ ባለበት ቆመ። ደቂቃዎች እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር የሞት ኮቴው እየራቀም ሄደ፤ መዳረሻው መሸነፍ ሆነ። ወጣቷ ከአካላዊ ጉዳቷ ዳነች።

የወጣቷ አካላዊ መዳን የፈጠረው የቤተሰብ ፌሽታ ግን የተከዳውን ንጹህ ልብ በቀደመ ውበቱ ዳግም ማግኘት በሚያስችል ሁኔታ አልነበረም። እናትም አባትም ሌላውም ሁሉ በጥርጣሬ ቀለበት ውስጥ እየተቆጠረ የሚኖር አዲስ ህይወት በወጣቷ ልጃቸው ልብ ውስጥ እየተወለደ መሆኑን ለመረዳት ጊዜ ወሰደባቸው። የመከዳት ውጤት ከራስ የህይወት መዝገብ ላይ ታትሞ ሲገኝ ይህ ሆነ። በየጓዳው ያለ ስብራት፤ በአግባቡ ባለመያዙ ምክንያት እያመረቀዘ ደጋግሞ የሚጎዳ፤ መከዳት!

በመከዳት ስሜት ውስጥ ያለፉ ሰዎች ስሜቱን በቃላት መግለጽ ሲቸገሩ ይስተዋላል። መከዳት ታላቅ የልብ ስብራትን ፈጥሮ የሚያልፍ መሆኑን ከተደረጉ በርካታ ጥናቶች እንረዳለን። በመከዳት ውስጥ ተስፋ ደብዝዞ፤ ከሰዎች ጋር የሚኖር የህይወት መስተጋብር ትርጉም ባለው ሁኔታ ተጎድቶ፤ ፍርሃት ነግሶ፤ ነጻነት ተገርስሶ ይታያል። አንዳች መፍትሔ እስካልተገኘ ድረስ። እነሆ “መከዳት ሲደርስብን” ብለን እንቀጥል።

### መከዳት ሲደርስብን

መከዳትን ተከትሎ የሚመጣው የሥነ-ልቦና ቀውስ ቀላል አለመሆኑን ለመረዳት የግድ በህመሙ ውስጥ ማለፍን አይጠይቅም። መከዳትን ውስብስብ የሚያደርገው በአብዛኛው ሳይጠበቅ የሚደርስ፤ ካልተጠበቀ ሰው የሚመጣ በመሆኑ ነው። ሰው መከዳትን እያሰበ ግንኙነት ሊመሰረት አይችልምና። የትኛውም በመተማመን መንገድ ላይ ያለ ግንኙነት በሂደት ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላኛው ደረጃ በሚያድግበት ጊዜ ከመከዳት እየራቀ እየመጣ መሆኑን ውስጣችን ይቀበላል። በተቃራኒው መከዳት በሚሆንበት ጊዜ ጉዳቱ ቀላል የማይባል ሊሆን ይችላል። ልብን የሚሰብር ጉዳት፤ በወጌሻ ታክሞ ሊድን የማይችል ስብራት።

መከዳት በፍቅር ግንኙነት ውስጥ፤ መከዳት በቤተሰብ ውስጥ፤ መከዳት በንግድ ሥራ ውስጥ፤ መከዳት በፖለቲካ፤ መከዳት በሌሎችም ዘርፎች ውስጥ ሊፈጠር ይችላል። ‘እከሌ ሊከዳኝ ይችላል’ ብሎ አስቦ ግንኙነት ውስጥ መሆን ግንኙነቱ ማደግ በሚችልበት ደረጃ እንዳያድግ ማድረግ መሆኑ ግልጽ ነው። ነገርግን በህይወታቸው ውስጥ መከዳት የደረሰባቸው ሰዎች መኖራቸው መከዳት ሲደርስብን እንዴት ማስተናገድ እንዳለብን ዛሬ ላይ ሆነን ከማሰብ ሊከለክለን አይችልም።

መከዳት ሲደርስ ራስን በመጣል፤ ራስን ለጉዳት በመዳረግ በሰፊው የምንመለከተው ምላሽ ነው። እንደ ግለሰብ የምንሰጠው ምላሽ ቤተሰባችንን እንዲሁም ሌሎች ለእኛ ትልቅ ቦታ ያላቸው ሰዎች አላስፈላጊ ዋጋ እንዲከፍሉ የሚያደርግም ሊሆን ይችላል። ከሁሉም በላይ ግን እነርሱንም በጥርጣሬ እንድናይ የምንገደድበት ሁኔታ የመፈጠሩ ሃቅ ጎልቶ የሚታይ ነው።

በችግር ጊዜ የቤተሰብ አባላት አብረው ከመቆም ይልቅ መራቅን ሲመርጡ፤ አሉልን ከጎናችን ናቸው ያልናቸው በቦታቸው ሳይገኙ ሲቀሩ፤ የሚፈጠረው ስሜት እንኳን ጉዳቱ ከፍተኛ ነው። በዚህ ስሜት ውስጥ የተገኙ ሰዎች ዋናው መከዳት ሲደርስባቸው እንዴት ሊቀበሉት እንደሚከብዳቸው ቢያስቡ ሊገርመን አይገባም። ይህም ሰዎች ምን ያህል እርስበእርሳችን ባለው ግንኙነታችን ውስጥ ህይወታችን የተሳሰረች መሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል።

አንባቢው ምናልባት በህይወቱ ውስጥ የገጠመውን መከዳት እያሰበ እያነበበ ይሆናል። ምናልባትም በህይወቱ ቀጣይ ምእራፍ ሊያጋጥመው የሚችል ሆኖ ሊመጣም ይችላል። ምናልባትም በመከዳት ውስጥ ያለን የሚያውቀውን አንድ ሰው እያሰበም ይገኛል። ምናልባትም ራሱን ለመከዳትም እያዘጋጀ ወይንም በመከዳት ህይወት ውስጥ አልፎ ከህሊናው ጋር ጸብ ውስጥ የሚገኝ ሊሆን ይችላል።

በዋናነት መከዳት ሲደርስብን እንዴት በመከዳት ስሜት ሳንጎዳ የህይወታችንን አቅጣጫ ማስተካከል እንዳለብን ግንዛቤን የሚሰጡ ነጥቦችን በቀጣይ እናነሳለን። መከዳት ሲደርስ ፈራርሶ ከመቀመጥ ዛሬ ላይ ራስን ማዘጋጀት ተገቢ መሆኑን ጸሐፊው ያምናል። በተቃራኒው ደግሞ መከዳት ሊደርስ ይችላል ብሎ የግንኙነትን እድገት መወሰን ውስጥ እንዳንገባ ማሰብም ተገቢ ሆኖ ይገኛል። ጠንካራን ግንኙነት እየፈጠሩ ነገርግን መከዳት ሲያጋጥም መልሶ በእግር እየሄዱ ህይወትን ለመቀጠል በሚረዳ ሚዛን ውስጥ። ከጥበብ በሚገኝ ሚዛን መካድን በመቀበል የመፍትሔውን ሃሳብ እናስቀምጥ።

### ከመካድ መቀበል

መከዳት ሲያጋጥመን እውነታውን ለመካድ ከመሞከር መቀበል የተሻለው የመፍትሔ መንገድ መሆኑን የሚያስረዳ ነጥብ ነው። በህይወታችን ውስጥ እንዳይሆኑ የምንፈልጋቸው ነገሮች አሉ። ምናልባትም ሰዎች እንዳያውቁብን የምንፈልጋቸው። ነገርግን ሁሉም በእኛ ቁጥጥር ውስጥ ያለ ባለመሆኑ፤ በተጨባጭ መከዳት በሚፈጠርበት ጊዜ ላለመቀበል ብዙ እርቀት ከመሄድ እውነታውን በቁመናው ልክ መቀበል ተገቢነት ይኖረዋል።

የከዳንን ሰው እኛም በተመሳሳይ መንገድ በመከዳት ሂደት ውስጥ ከመግባት እውነታውን ተቀብሎ የመፍትሄ መንገዶችን መፈለጉ በባለሙያዎች የሚሰጠው ቀዳሚ ምክር ነው። በህጻናት አስተዳደግ ውስጥ የመከዳት ትርጉም ቦታን ይዞ እናገኛለን፤ እንዴት የሚለውን ስናነሳ መከዳት በሰዎች ህይወት ውስጥ ተዋህዶ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል እንድንረዳ ያደርገናል። መከዳትን ተቀብሎ ለመፍትሔው ከመስራት ይልቅ፤ አቅልሎ የማየት አስተሳሰብን እንድንፈጥር የሚያደርግ።

መከዳት ከመጠበቅ የሚወጣ በመሆኑ ህጻናት በተፈጥሯቸው ከቤተሰባቸው የሚጠብቁ ናቸው። ከቤተሰብ የሚጠብቁት ከመሰረታዊ ፍላጎታቸው ውጪ ፍቅርንና እንክብካቤን ተቀባይነትን ወዘተ የመሰሉ ቁሳዊ ከሆኑ ፍላጎቶች ውጭ የሆኑትንም ነው። ህጻናቱ እነኚህን የሚጠብቁትን በሚያጡበት ጊዜ በውስጣቸው እያደገ የሚሔድ ቤተሰባቸውን ያለመቀበልና በስተመጨረሻ በቤተሰብ ውስጥ ጤናማ የመቀባበል ስሜት እንዳይኖር ያደርጋል። አለመቀባበሉ በሂደት አድጎ በአዋቂ እድሜ ውስጥም ሆነ በመከዳዳት ውስጥ ሊያልፉ ይችላሉ።

የመከዳት ስሜት አብሮን እያደገ የሚመጣ በሚሆንበት ጊዜ ችግሩን እንደ ችግር ሲያጋጥም ተቀብሎ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ‘መከዳትም ሆነ መክዳት ያለ ነው’ ብሎ ተቀብሎ ለተወሳሰበ ችግር ራስን ማጋለጫ ምክንያት ሊሆን ይችላል። መከዳትንም የምንቀበልበት መንገድ ወደ ተሻለ የህይወት አቅጣጫ የሚመራ ከመከዳት ወይንም መክዳት ህይወት መውጣት የሚያስችል ሳይሆን መከዳዳት እየሰፋ እንዲሔድ የሚያደርግ ይሆናል።

ከትናንት ከረጅሙ የአስተዳደግ ጉዞ ውስጥ የተፈጠረ መከዳዳትን አቅልሎ የሚያይ አተያይ ውስጥ ካለን እንዴት ልንወጣ እንደምንችል ስናስብ መፍትሔው በትናንትናችን ውስጥ የሆነውን መርምሮ መቀበል ሆኖ እናገኘዋለን። ስለሆነም መከዳት የህይወትን አቅጣጫ በተሳከረ መንገድ እንደሚመራ፤ መከዳት በአግባቡ ካልታከመ ጉዳቱ እየተባዛ እንደሚሔድ፤ መከዳዳት ህይወትን በሙላት ከመኖር የሚያግድ መሆኑን ማሰብ ያስፈልጋል።

ከትናንት ተጉዞ የመጣም ይሁን አዲስ የተከሰተ የመከዳትም ሆነ የመክዳት እውነት በህይወታችን ውስጥ ካለ ችግሩን እንደ ችግር መቀበል ችግሩን ክዶ ከመቀመጥ የተሻለ ነው። ላለመቀበል የምናደርገው ትግል በበሽታው ውስጥ አብረን እንድንቆይ ሊያደርግ ይችል ይሆናል እንጂ ወደ መፍትሔው ሊያደርሰን የሚችል ባለመሆኑ።

### የስሜት ቀውስን ምላሽ መለማመድ

በመከዳት ውስጥ የሚፈጠረው የስሜት ቀውስን በየአይነቱ ለይቶ ስሜቱ ሲፈጠር ልንሰጥ የሚገባውን ግብረ-መልስ መለማመድ ሌላው የመፍትሔ መንገዱ ቁልፍ ነጥብ ነው። መከዳትን ተከትተሎ ንዴት፤ ቁጣ፤ ህመም፤ እፍረት ወዘተ የስሜት አይነቶች ይፈራረቃሉ። እያንዳንዱ የስሜት ቀውስ የራሱ የሆነ መገለጫና ባህሪ አለው። ለእያንዳንዱ የምንሰጠው ትርጉምና በሚሰማን ጊዜ ልናደርግ የምንፈልገውን ለይተን ማወቅ አለብን። ከልየታው በኋላ በእያንዳንዱ ስሜት ውስጥ ራሳችንን እየጨመርን በተጨባጭ ስሜቱ ሲፈራረቅብን ራሳችንን እንዴት እየገዛን ልናልፈው እንደሚገባ ትምህርት እንወስዳለን።

ለምሳሌ፣ በተፈጠረብን መከዳት ስሜት ውስጥ ሆነን መከዳታችንን የሚያውቁ ሰዎች በሚያገኙን ጊዜ እንዴት ምላሽ እንደምንሰጥ ማወቅ በተጨባጭ የእፍረት ስሜቱ ሲያጋጥመን ከምናደርገው ያልተዘጋጀንበት ምላሽ የተሻለ ነው። ሰዎች የሚወዱትን ሰው በሞት ተነጥቀው በሃዘን ላይ ሆነው ሌላ ሟችን በጋራ የሚያውቁትን ሰው ሲያገኙ ስለሟች እያነሱ ማውራት እንዲሁም አብረውም ማልቀስ ባህላችን ነው። በሂደቱም ስሜትን መጋራትና መጽናናት ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ ከምናልፍበት የመከዳት ስሜት አንጻር ከሰዎች ጋር ስንገናኝ የሚገጥመን የስሜት ጎርፍ አለ። ይህን የስሜት ጎርፍ እንዴት አድርገን ማስተናገድ እንደሚገባን አስቀድሞ ማወቁን ነው እያነሳን ያለው። ይህ ማለት ስላለንበት ስሜት ድብቅ እንሁን ማለት አይደለም፤ ማንን ስናገኝ ምን ሊሰማን ይችላል የሚለውን ካወቅን በኋላ ስሜታችንን በጤናማነት እንዴት መግራት እንዳለብን ማሰብ መቻል ነው። የከዳንን ሰው የቅርብ ቤተሰብ ስናገኝ እንዴት እንመለከታለን? ያንን ስሜት ዛሬ ላይ መለማመድ። የእኛን መጎዳት የማይፈልግ የልብ የምንለው ሰው ሲገጥመን ምን ሊሰማን ይችላል? አሁንም ያንን ስሜት ዛሬ ላይ መለማመድና ስሜቱ ሲገለጥ በአግባቡና ወደ ተሻለ መፍትሔ ሊያደርሰን መንገድ ውስጥ ማረቅ መቻል ማለት ነው።

### ለእርዳታ መቅረብ

ሰው በመሆናችን ውስጥ ያለው አንዱ በረከት አንዳችን ለሌላችን ያለን ቦታ ነው። በህይወታችን ውስጥ ልዩ ቦታ የምንሰጣቸው ሰዎች አሉ። ቤተሰብ እና ጓደኞች ልዩን ቦታ ከሚይዙት መካከል ቀዳሚዎች ናቸው።



በማንኛውም የስሜት መዋዠቅ ውስጥ ስንሆን እጅግ ቅርብ ከምንለው ሰው ጋር ካልሆነ በስተቀር ከሌሎች ሰዎች ልንርቅ እንችላለን። ከሁሉም ሰው መራቅ ደግሞ አደገኛ ነው። ያለንበትን የስሜት መዋዠቅ ተለማመድን ሰው ጠሊታ ሆነን ራሳችንን እንድናገኝ ሊያደርገን ይችላል። የቅርብ የምንለው ሰው ግን ስሜታችንን እንዲያውቅና ካለንበት ነገር ለመውጣት በምናደርገው ሂደት ውስጥ እንዲያግዘን ማድረግ አለብን። ይህ ራሳችንን ለሌሎች እርዳታ የማቅረብ ምእራፍ ነው።

የመከዳት ስሜት ወደ በቀል፤ የመከዳት ስሜት ራሳችንን ምሽግ ውስጥ እንድንደብቅ እንዲሁም ህይወትን በፍርሃት የምንከተል እንዳያደርገን ከፈለግን የመውጫ መንገዱ ላይ መግባትን ይፈልጋል። እርዳታ ለሚያደርጉልን ሰዎች ራሳችንን ማቅረብ ከመውጫ መንገዱ ላይ የሚገኝ አንዱ የመፍትሔ ሃሳብ ነው።

በቅርባችን ያሉ ሰዎች በምንሆነው ሁናቴ እንዲሁ ከሚጨነቁ እውነታውን ተረድተው በምክርም፤ በተግሳጽም እንዲሁም በእንክብካቤም እንዲረዱን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ውድ የምንላቸው ሰዎች በተጨባጭ ውድ መሆናቸው የሚገባን እንዲህ ባለወቅት ነውና።

### በምንፈልገው ነገር ላይ ትኩረት ማድረግ

በፍቅር ግንኙነት ውስጥ የተፈጠረ መከዳት እምነትን መልሶ ሊቀጥል የሚችልበት መንገድ ላይ መግባት ስለመቻሉ በጥቅሉ መናገር ባይቻልም እድል ሊኖረው ይችል ይሆናል። በመከዳት ጊዜ ግን የምንፈልገው ነገር እስከምን ድረስ መሆኑን ግብ ማድረግ ያስፈልጋል። ከዳን የምንለው ሰው የከዳን በምን ምክንያት ነው ብለን በእርሱ ጫማ ሆነን በእውነተኛ ይቅርታ ከተመለሰ አብረን ህይወትን ለመቀጠል ወይንም መለየታችን እርግጥ ሆኖ የራሳችንን አቅጣጫ ለማስተካከል ብሎ ትኩረት መደረግ የሚገባውን ነገር መለየት ያስፈልጋል።

ትኩረት ያደረግነው ላይ ለመድረስ የሚወስደው ጊዜ መኖሩ እሙን ነው። በጊዜ ውስጥ የሚሰራውን ስራ ማወቅም እንዲሁ ተገቢነት አለው። ልብ አንጠልጣይ ፊልም በማየት ራሳችንን ለአፍታም ቢሆን በመርሳት ከአዲሱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለመግባባት ማድረግ ብቻም ሳይሆን ተጨማሪ ልማዶችን ወደ ህይወታችን በመጨመር ትኩረት ያደረግነው እንዲሳካ ማድረግ ያስፈልገናል። በጸሎት፤ በቅዱሳት መጽሐፍት ንባብ፤ አዳዲስ ልማዶችን (ሆቢዎችን) በመተግበር ወዘተ ውስጥ ትኩረት ወዳደረግነው የመፍትሔ አቅጣጫ ላይ መድረስ እንችላለን።

ማጠቃለያችን መከዳት የሚያመጣውን አሉታዊ ተጽእኖ እንዴት ተቋቁመን የህይወታችንን አቅጣጫ አስተካክለን መራመድ እንደምንችል እንድናስብ። ወጣቷን ለማዳን የተደረገው እርብርብ አካላዊውን ችግር ለመፍታት የቻለ ቢሆንም ከውስጥ የሚወጣው የመከዳት መራር ስሜት ግን በጥንቃቄ መታከምን ይፈልጋል። በተለይም የጉዳዩ ባለቤት ችግሩን በመቀበል፤ የስሜት መዋዠቆቹን በመለማመድ፤ እርዳታ ሊያደርጉለት ከሚገቡ አካላት እርዳታን በመቀበል እና ትኩረት መደረግ ባለበት ላይ ትኩረት በማድረግ ስለ ሰዎች መልካም ሆኖ መኖር!

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ‹‹ወጣቱ በህልምና በራዕይ መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል››

- አቶ ዳዊት ሀይሉ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ኢትዮጵያዊ ትህትና፣ አክብሮት፣ ኩራትና ፍቅርን የተጎናጸፉ መልከ ቀና ሰው ናቸው። ስብዕናቸውም ቢሆን ከጥንቱ ኢትዮጵያዊ የባህል ቱባ የተመዘዘ ለመሆኑ ነገረ ሥራቸው ሁሉ ይመሰክራል። ከደንበኞቻቸውና ከሠራተኞቻቸው ጋር ያላቸው ቀረቤታም እንዲሁ ቤተሰባዊ የሆነ ጥብቅ ትስስር ያለው ለመሆኑ በነበረኝ ቆይታ መገንዘብ ችያለሁ። ልጆች መልካም ስብዕናን ይዘው ለማደጋቸው ትልቅ ድርሻ ካለው ቤተሰብ ፍቅርን፣ መልካምነትን፣ አክብሮትንና ለሌሎች መትረፍን በብዙ ተምረዋል። ለትውልድ የሚተርፍ መልካም ሥራን መሥራት የሰብዓዊነት ጥግ ስለመሆኑም ኖረውት አድገዋል።

በመልካም ስብዕና ለማደጋቸው ቀዳሚ ተምሳሌት ቤተሰቦቻቸው እንደሆኑ ይናገራሉ። በተለይም ከወላጅ እናታቸው የወረሱት መልካምነት ፍሬ አፍርቶ ዛሬ በብዙ እጥፍ እየመነዘሩት እንደሆነ የሚነግሩን የዕለቱ እንግዳችን በጤና፣ በትምህርትና በምግብ ኢንዱስትሪ ተሰማርተው ትርጉም ያለው ሥራ እየሠሩ ለብዙዎች በርካታ የሥራ ዕድል የፈጠሩ ባለሀብት ናቸው - አቶ ዳዊት ኃይሉ። በእንቅስቃሴያቸው ሁሉ ለገጠሟቸው ደንቃራዎች እጅ ሳይሰጡ ለስኬት በቅተዋል። ታዲያ ስኬት ማለት ለእርሳቸው ሰዎች ያቀዱትን ማንኛውንም ነገር ለሚገጥማቸው እንቅፋት ሳይበገሩ ማሳካት መቻል ነው ብለው ያምናሉ።

ወላጅ እናታቸው በሕይወት ባይኖሩም በልጆቻቸው ላይ የዘሩት መልካም ፍሬ ግን በእጥፍ ያፈራ ስለመሆኑ የሚናገሩት የዕለቱ እንግዳችን አቶ ዳዊት ተወልደው ያደጉት አዲስ አበባ መሀል ፒያሳ ላይ ነው። የአካውንቲንግና የሶሾሎጂ ትምህርታቸውን ተከታትለው በአሁኑ ወቅት በንግዱ ዘርፍ ተሰማርተዋል። አሁን ላይ በጤና፣ በትምህርትና በምግብ ዘርፍ ሦስት ድርጅቶችን ቢመሩም መነሻቸው የባህል አልባሳት መሸጥ እንደነበር አጫውተውናል።

በተማሩት ትምህርትም ሆነ በሌላ ተቀጥረው ያልሠሩት አቶ ዳዊት፤ ከሠርጋቸው በተረፈ ገንዘብ በቀዳሚነት በባለቤታቸው ስም ውዳሴ የባህል ዕቃዎች መሸጫን ከፍተው ነበር። ወደ ንግዱ የገቡበት አጋጣሚም ሠርጋቸውን እጅግ መጠነኛ በሆነ ድግስ በቀበሌ አዳራሽ ውስጥ ከማድረጋቸው ባለፈ የመጠነኛ ድግሱ ወጪም ቢሆን በዘመድ አዝማድ መሸፈን በመቻሉ ወደ ንግዱ እንዲገቡ ዕድል ፈጥሮላቸዋል። ባገኙት አጋጣሚ የባሕል ዕቃዎች መሸጫን ከአንድ ወደ ሁለት ከሁለት ወደ ሦስት ቅርንጫፍ በማሳደግ፣ በማምረትና ወደ ውጭ በመላክ በዘርፉ ውጤታማ መሆን ችለዋል።

ተጨማሪ ሥራን ሲያስቡ ታዲያ በወቅቱ በጤናው ዘርፍ ያለውን ክፍተት በማጥናት የሲቲ ስካን አገልግሎት በአገሪቱ አለመኖሩን በመገንዘብ ውዳሴ ዲያግኖስቲክ ማዕከልን አቋቋሙ። ቀጥለውም ቢሾፍቱ ከተማ ላይ ከኬጂ እስከ ስምንተኛ ክፍል ያለውና አንድ ሺ ተማሪዎችን የመቀበል አቅም ያለው ጆርጎ ትምህርትን ከፍተዋል። ጆርጎ የቅድመ አያታቸው ስም መሆኑን እና የኦሮሚኛ ቃል እንደሆነ የገለጹት አቶ ዳዊት፤ ትርጉሙም ትልቅ ፍሬው የከበደው ዛፍ ማለት ነው። ስለዚህ እነርሱም እንደ ጆርጎ ዛፍ ፍሬያቸው በዝቶ ለሌሎች ጥላ ለአገር መከታ ለመሆን ካላቸው ፍላጎት የተነሳ ትምህርት ቤቱን ጆርጎ አካዳሚ ብለው እንደሰየሙ አጫውተውናል።

በተጨማሪም ቴክኖሎጂ ላይ የሚሠራ ፍቱን ከቴክኖሎጂ እንዲሁም የሕክምና መሣሪያዎችን የሚያቀርብ ኤልስ ሜድ የተባለ ድርጅትን በመክፈት የንግድ ሥራቸውን ማቀላጠፍ የቻሉት አቶ ዳዊት፤ አሁን ደግሞ በምግብ ኢንዱስትሪው በስፋት እየታወቁ መጥተዋል።

በአሁኑ ወቅት በስፋት እየታወቁበት ያለው አኮ ቡና ሲሆን ‹‹አኮ ›› የወላጅ እናታቸው መጠሪያ ስም ነው። አኮ ቡናም ወላጅ እናታቸውን ይበልጥ የሚያስታውሱበት እንደሆነ ይናገራሉ። አኮ ቡናን ጨምሮ የተለያዩ ምግቦችን በጥራት የሚያቀርብና በተለያዩ አካባቢዎች ሦስት ቅርንጫፎች ያሉት በቅርቡም አራተኛውን ቅርንጫፍ ለመክፈት በዝግጅት ላይ ሲሆኑ በእህት ኩባንያዎቻቸው በጠቅላላ አንድ ሺ ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

በሕይወት ጉዟቸው ሁሉ ውጤታማ የመሆናቸው ምስጢር ከወላጅ እናታቸው የተገኘ ስለመሆኑ ሲናገሩ እናታቸው የብዙዎች እናት አልባሽና አጉራሽም ነበሩ። ይህን መልካምነት እየተመለከቱ ያደጉት አቶ ዳዊት፤ ዛሬ የእናታቸውን ፈለግ መከተል አላዳገታቸውምና በሚያስተዳድሯቸው ድርጅቶች ሁሉ የወላጅ እናታቸውን መርሆ በመከተል እንግዳ ተቀባይ ሆነው ደንበኞችን እንደየፍላጎታቸው ያስተናግዳሉ።

‹‹አኮ የልጅ ልጆቿ ሲመጡ የማይሆን ነገር አታቀርብም፤ ምርጥ የተባለውን ሁሉ ታቀርባለች›› የሚሉት አቶ ዳዊት እርሳቸውም ለደንበኞቻቸው የማይሆን ነገር እንደማያቀርቡ እና ደንበኞች አኮ ቡና ገብተው ምንም የሚያጡት ነገር እንደሌለም ይናገራሉ። አገልግሎታቸው ለ24 ሰዓታት የሚቋረጥ አይደለም ለዚህም ወላጅ እናታቸው በሕይወት በነበሩ ጊዜ እርሳቸው ጋር ገብቶ ሳይበላ ሳይጠጣ የሚወጣ ሰው እንደሌለና ምግብ ባይበላ እንኳ እንግዳ ሆነው የገቡ ሴቶች ሽቶ ተቀብቶ ይመለሱ እንደነበርም ለአብነት አንስተዋል።

ስኬት ማለት ሰዎች የተፈጠሩለትን ዓላማ ፈልገው ሲያገኙ፣ ሲያሳኩና ለዚያ ዓላማም መኖር ሲችሉ ነው



የተጀመረ ነገር ፍጻሜ እንዲኖረው እናታቸው የሚመክሩትን ምክር ሁሌም በማስታወስና ተግባር ላይ ለማዋል ከሚያደርጉት ጥረት ባለፈ ‹‹ልጆቼ አንድን ነገር ከመጀመር ይልቅ መፈጸም መልካም ነውና የጀመራችሁትን ነገር ፈጽሙት›› የሚለውን ንግግር በድርጅታቸው ግርግዳ ላይ ከፍ አድርገው አስቀምጠዋል። ከንግግራቸው ባለፈም ሙሉ የቤተሰቡን አባላት የያዘው ፎቶግራፍ አይን የሚይዝ ቦታ ላይ መሰቀሉም አኮ ቡናን ለየት ያደርገዋል።

አኮ ቡና ውስጥ ታዲያ እናታቸው የሚታወሱባቸው በርካታ ድርጊቶችና ምስሎች መኖራቸው በዋናነት ለማስታወስ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ዳዊት፤ ከሌሎቹ ድርጅቶች በተለየ አኮ ቡና የወላጅ እናታቸውን መልካም ባህሪና ማንነት ሊያንጸባርቅ የመጣ ድርጅት እንደሆነም ይናገራሉ። በአኮ መሶብ ውስጥ ምንም የሚታጣ ነገር አልነበረምና ፍራፍሬን ጨምሮ ዳቦ፣ ጭኮ፣ ቆሪና ሌሎችም ባህላዊ ምግቦች ሁሌም አሉ። ይህን መነሻ በማድረግም በአኮ ቡና ባህላዊ የሆኑ ምግቦችን ጨምሮ የጾምና የፍስክ፣ ቡና በዓይነት በዓይነቱ፣ ጣፋጭ ኬኮችና የተሟላ የምግብ አገልግሎት እየሰጠ ያለ ድርጅት ነው።

ሦስት ዓመታትን ያስቆጠረው አኮ ቡና ቅርንጫፍ ሲከፈት ለሰዎች በጎ ነገሮችን እያስተማረ መሆኑን አቶ ዳዊት ይናገራሉ። ሁለተኛው ቅርንጫፍ ሲከፈት ድርጅቱን የመረቁት የመቄዶንያ ሰዎች ሲሆኑ በፕሮግራሙም አረጋውያኑን በአክብሮትና በትህትና ዝቅ በማለት እግራቸውን አጥበውና ስመው ተቀብለዋል። ቀጥለውም አረጋውያኑን ጋቢ አልብሰው ምግብ በጋራ በልተው የአረጋውያኑን ምርቃት ተቀብለው ፍጹም ኢትዮጵያዊ በሆነ ባህል ድርጅቱን መርቀው ከፍተዋል።

ይህ ለድርጅቱ ትልቅ ትርጉም አለው የሚሉት አቶ ዳዊት፤ ከዚያም ባለፈ እንግዳ ተቀባይነት የኢትዮጵያውያን መገለጫ በመሆኑ ነው። እግር ማጠብ ትህትና በመሆኑ ትህትና የሌለው ሥራ ደግሞ ውጤታማ አይሆንም። ስለዚህ የአረጋውያኑን እግር በማጠብ የትህትናን ጥግ እግር በመሳም ደግሞ የፍቅርን ጥግ ማሳየት በመቻላቸው ልጆቻቸውን ጨምሮ ለሠራተኞቻቸውም አርአያ መሆን ችለዋል።

ሦስተኛውን አኮ ቡና በከፈቱበት ወቅት ደግሞ 150 የሚደርሱ ማየት የተሳናቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከየአቅጣጫው በማሰባሰብ የምሳ ግብዣ በማድረግ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ዳዊት፤ ማየት የተሳናቸውን የመረጡበት ምክንያትም ከማኅበረሰቡ የተገፉና የተረሱ በመሆናቸው ለማስታወስ ነው ይላሉ። ሌላው ቀርቶ እነሱን መጋበዝ ቀላል ሥራ እንዳልሆነና ለእነሱ አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ እንደሚገባ ለማስታወስ ጭምር መሆኑን ይናገራሉ።

ቤት መመረቅ እርዳታ መሰብሰቢያ መሆን የለበት የሚል ዕምነት ያላቸው በመሆኑ ከተለመደው የሆቴል ምርቃት ወጣ በማለት በረከትና ምርቃት ከሚገኝባቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ኢትዮጵያዊ በሆነ ባህል መገናኘቱ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ልምድ በማድረጋቸው ተጠቃሚ እንደሆኑና ሥራቸው እንደሚባረክም ያምናሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ማኅበራዊ ኃላፊነትን ከመወጣት አንጻር የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሲሆን ለአብነትም በውዳሴ ዲያጎንስቲክ ማዕከል በየዓመቱ ጳጉሜ ከአምስት እስከ ስድስት ቀናት ነፃ ሲቲ ስካንን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ማናቸውንም ሕክምና ማድረግ የሚችሉበትን ዕድል አመቻችተዋል። በማንኛውም ጊዜም የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሰዎች ነፃ አገልግሎት ይሰጣሉ። በአጠቃላይ በ12 ዓመት የሕክምና ጉዟቸውም 50 ሺ ለሚደርሱ አቅመ ደካሞች የነፃ አገልግሎት ሰጥተዋል።

ሁሉም እህት ድርጅቶች እርስ በእርስ ተደጋግፈው የሚጓዙ ስለመሆናቸው ያነሱት አቶ ዳዊት፤ ድርጅቶቹ የተሟላ አገልግሎት ምክንያታዊ በሆነ ዋጋ ያቀርባሉ። የሚሰጧቸው አገልግሎቶችም ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን በመላበስ በፍጹም ትህትናና አክብሮት እንደሆነ ይጠቅሳሉ። እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረሳቸውም ከቤተሰብ የወረሱት ኢትዮጵያዊ ጨዋነትን ጨምሮ ባለቤታቸው ትልቅ ድርሻ ያላቸው መሆኑን በማንሳት በዋናነት ግን ‹‹እኔ ማነኝ የተፈጠርኩለት ዓላማ ምንድነው ›› ብለው እራሳቸውን ጠይቀው ለጥያቄያቸውም መልስ በመሻታቸው መሆኑን ያስረዳሉ።

‹‹ገንዘብ ያላቸውና ካፒታላቸውን ማሳደግ የቻሉ ሁሉ ስኬታማ ናቸው ማለት አይቻልም። ስኬት ማለት ሰዎች የተፈጠሩለትን ዓላማ ፈልገው ሲያገኙ፣ ሲያሳኩና ለዚያ ዓላማም መኖር ሲችሉ ነው›› የሚሉት አቶ ዳዊት፤ በተሰማሩባቸው የሥራ ዘርፎች ሁሉ ውጤታማ ለመሆን በሚያደርጉት ጥረት ልክ ስኬታማነታቸው የሚለካ እንደሆነና ሥራቸው ፍሬ አፍርቶ ለሌሎች መትረፍ ሲችሉ እንዲሁም ተጨማሪ የሥራ ዕድል በመፍጠር ለአገርና ለወገን መከታ መሆን እያሳኩት ያለ የተፈጠሩበት ዓላማ እንደሆነ ይናገራሉ።

በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ከአስር ዓመት በላይ የተጓዙት አቶ ዳዊት በጉዟቸው ሁሉ የተለያዩ መሰናክሎች ይገጥሟቸው እንደነበር፣ አሁንም ችግሮች እንዳሉና ወደፊትም ሊገጥማቸው የሚችል እንደሆነ በማመን ነገር ግን ማንኛውንም ችግር በጥረት ማለፍ ይቻላል ይላሉ። በቀጣይም የሚገጥማቸውን ፈተናዎች ሁሉ በመቋቋም በተለይም ድርጅቶቻቸውን በማጠናከርና ሌሎች ቅርንጫፎችን በመክፈት ተደራሽነታቸውን የማስፋት ዕቅድ አላቸው።

ጆርጎ አካዳሚንም እንዲሁ የማስፋፋት ዕቅድ ያላቸው ሲሆን የውዳሴ ዲያጎንስቲክ ማዕከል አገልግሎትን በክልል ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ ጅማ ከተማን ቀዳሚ በማድረግ እየተንቀሳቀሱ የሚገኙ ሲሆን በፈረንጆቹ 2025 ለአራት ሺ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠርም አቅደው እየሠሩ ነው።

‹‹ወጣቱ በህልምና በራዕይ መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል›› የሚሉት አቶ ዳዊት፤ ህልም ዓይን ተጨፍኖ የሚታይና ሥራ የማይፈልግ በመሆኑ ወጣቶች ሥራ የሚፈልገውን ራዕይ ዕውን ማድረግ እንዲችሉ ዓይናቸውን ገልጠው ማሰብ፣ ማሰላሰልና ሀሳባቸውን ወደ ተግባር ለመቀየር ጠንክረው መሥራት እንዳለባቸው ይመክራሉ። እኛም አስተማሪ ታሪክ ካላቸው እንግዳችን ወጣቶች ብዙ እንደሚያተርፉ በማመን ከህልም ዓለም በመውጣት ባለራዕይ እንሁን በማለት አበቃን ሰላም!

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ለፍጻሜው የሚንደረደረው ታላቁ የህዳሴ ግድብ

**መሳኩ ኤሮሴ**

ኢትዮጵያውያን ድህነትን እንዲያሸንፉ የሚያስችላቸውን የታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ መሠረተ ድንጋይ ካስቀመጡ እነሆ 11 ዓመታት ተቆጠሩ። ኢትዮጵያውያን ሀብታቸውን፣ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና እውቀታቸውን በማዋጣት እየገነቡት ያለ ታሪካዊ አሻራ ነው። የፕሮጀክቱ 84 በመቶ ለፍጻሜ የደረሰው ይህ ፕሮጀክት ቀሪ ሥራዎቹም በኢትዮጵያውያን ሀብትና ጉልበት የሚጠናቀቅ ይሆናል። ለዚህም ኅብረተሰቡ ከፍተኛ ድጋፍ እያደረገና ተነሳሽነቱንም እያሳየ ይገኛል። የዚህ ፕሮጀክት ግንባታ መሠረተ ድንጋይ የተቀመጠበት ቀን ላለፉት 11 ዓመታት በየዓመቱ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር የቆየ ሲሆን፤ ዘንድሮም «ግድባችን የአንድነታችን ብርሃን» በሚል መሪ ቃል ነው እየተከበረ ያለው።

የዘንድሮ በዓል ግድቡ የሁለተኛ ዙር የውሃ ሙሌት እና ከ13ቱ የግድቡ ተርባይኖች አንዱ 375 ሜጋ ዋት ኃይል ማመንጨት የጀመረበት ዓመት እንደመሆኑ ከዚህ በፊት ከነበሩት ክብረ በዓላት ልዩ ያደርገዋል። ግድቡ አሁን የደረሰበት ደረጃ ትልቅ ምዕራፍ ተብሎ የሚወሰድ ነው። በርካታ ውጣ ውረዶችን አልፎ ግድቡ ኃይል ማመንጨት በጀመረበት ዓመት የሚከበረው ይህ የዘንድሮው ክብረ በዓል ለኢትዮጵያውያን ልዩ ትርጉም አለው። ኢትዮጵያውያን የደከሙበትን እና ዋጋ የከፈሉበትን ግድብ ፍሬ ማጣጣም በጀመሩበት ማግስት የሚከበር ከመሆኑም ባሻገር ኢትዮጵያውያን በጫናዎች ሳይበገሩ ያሰቡትን ማሳካት እንደሚችሉ ለዓለም ያስመሰከሩበት ነው።

የዚህ ታላቅ ፕሮጀክት ግንባታ ይፋ ሲደረግ በርካታ ወዳጅ አገራት ጭምር ኢትዮጵያ እንዲህ ያለ የባለ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ወጪንና የካበተ ልምድን የሚጠይቅ ፕሮጀክት ልትሠራው አትችልም የሚል ግንዛቤ ነበራቸው። የግድቡ ግንባታ ተጀምሮ ይቆማል የሚል እሳቤ ነበራቸው። እርግጥ እነዚህ አገራት እንዲህ ያለ አመለካከት ቢኖራቸው የሚገርም አልነበረም። ምክንያቱም ይህ ግድብ ከመጀመሩ ጥቂት አስርት ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ትታወቅ የነበረው በጦርነት፣ በረሃብና በድርቅ እንጂ በመልካም ጎኗ አልነበረም። በኦክስፎርድ መዝገበ ቃላት ረሃብ ለሚለው ቃል፣ ምሳሌው ኢትዮጵያ ነበረች። ከረሃብ እና ከድርቅ ጋር ስሟ ሲነሳ የቆየች አገር ያለ ውጭ አገራት ድጋፍ እንዲህ ዓይነት ፕሮጀክት ልገንባ ብላ ስትነሳ ግራ መጋባታቸው የሚደንቅ ሊሆን አይችልም።

የግድቡ ግንባታ መሠረተ ድንጋይ የተጣለበት 11ኛው ክብረ በዓል በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች በተለያዩ ዝግጅቶች ሲከበር በመድረኮቹ ላይ የተገኙት የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ግድቡ ኢትዮጵያውያን ገንዘብ፣ ጉልበት እና እውቀት ሳይሰስቱ በማዋጣት አሁን የደረሰበት ደረጃ መድረሱን ጠቁመው፤ ግድቡ ተጠናቆ በተሟላ አቅሙ ኃይል እስኪያመነጭ ድረስ ሕዝቡ ለግድቡ ግንባታ የሚያደርገውን የነቃ ተሳትፎ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ጠይቀዋል።

ይሄ የመንግሥት ጥሪ ተገቢነት ያለው ነው። የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በእውቀታቸው፣ በገንዘባቸው፣ በጉልበታቸውና በቁሳቁስ አቅርቦት ከመንግሥት ጎን በመቆም ያለ አንዳች ውጭ እርዳታና ድጋፍ ያገባደዱትን ግድብ ሙሉ በሙሉ እስኪጠናቀቅ ድረስ ከመንግሥት ጎን መቆም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው። ኢትዮጵያውያን የ«አይቻልም» መንፈስን የሰበረ፣ የሕዝቦች የትብብርና የአንድነት መንፈስ ያጎለበተ ተምሳሌታዊ ፕሮጀክት እስኪጠናቀቅ ድረስ ሕዝባዊ ድጋፉ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

11ኛው ክብረ በዓል ከመከበሩ ጎን ለጎን፤ በመጀመሪያ ምዕራፍ ቅድመ ኃይል ማመንጨቱን ተከትሎ አገር አቀፍ የቦንድ ሽያጭ ሳምንት ይፋ ተደርጓል። የቦንድ ሽያጭ ሳምንቱ ከመጋቢት 20 እስከ ሚያዝያ 05/2014 ዓ.ም ይቆያል ተብሏል። በተለያዩ አካባቢዎች ሕዝቡ ለግድቡ ግንባታ የቦንድ ግዥ ፈጽሟል። በአንዳንድ አካባቢዎች እስከ ስምንተኛ ዙር የቦንድ ግዥ ተፈጽሟል።

ሕዝቡ ከዚህ ቀደም ከዕለት ጉርሱ ቀንሶ ለግድቡ ግንባታ የሚውል ገንዘብ በቦንድ ግዥና በሌሎች የገቢ ማሰባሰቢያ ሥርዓቶች ሲያካሂድ የቆየ ሲሆን በተለያየ መልኩ ከ16 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርጓል። አሁንም ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠሉ ሕዝቡ ዛሬም ግድቡ ተጠናቆ ለማየት ያለውን ጉጉት አመላካች ነው። ግድብ አጠቃላይ የግንባታ ሥራው 84 በመቶ መድረሱ የተገለጸ ሲሆን እስካሁን ለግድቡ ግንባታ ከኅብረተሰቡ አርሶ አደሩ ደግሞ በጉልበቱ የተፋሰስ ሥራዎችን በመሥራት 100 ቢሊዮን ብር የሚገመት አስተዋጽኦ ማበርከቱም ተጠቅሷል።

በ2003 ዓ.ም በቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ አማካኝነት የመሠረተ ድንጋይ የተቀመጠለት ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አገሪቱ ከገነባቻቸው እና እየገነባቻቸው ካሉ ትልልቅ የአገሪቱ ፕሮጀክቶች መካከል ግንባር ቀደሙ ነው። ለግድቡ በሚወጣው ወጪ መጠን፣ በሚያመነጨው የኃይል መጠን፣ ባለው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከአገሪቱ ፕሮጀክቶች አውራ ነው።

ኢትዮጵያ ለጀመረቻቸውና የምጣኔ ሀብታዊ እድገት ያመጣሉ ላለቻቸው ፕሮጀክቶች ያለባትን የኃይል አቅርቦት እጥረት ለመፍታት የግድቡ መጠናቀቅ እና ወደ ሥራ መግባት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይጠበቃል። የፕሮጀክቱ መጠናቀቅ በተለይም በአሁኑ ወቅት በኃይል እጥረት እየተፈተ ያለው እና የአቅማቸውን ያህል ማምረት ያልቻሉ በአገሪቱ የተገነቡ ትላልቅ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሀይል ችግር ለመቅረፍ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ። አዲስ ወደ ስራ የሚገቡ ሌሎች መለስተኛ እና ትልልቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ያልተቆራረጠ ኃይል እንዲያገኙ የዚህ ግድብ መጠናቀቅ ፋይዳው የላቀ ነው። በመሆኑም የውጭ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ውስጥ መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ እንዲበረታቱ የሚያደርግ ነው።

የማምረቻ ዘርፍ ራስ ምታት የሆነውን የኃይል እጥረት ችግር ለመቀነስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችለው ይህ ፕሮጀክት አገሪቱ ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መሪ ኢኮኖሚ ለመሸጋገር ለምታደርገው ጥረት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ፕሮጀክቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የተለያየ አቋም በመያዝ የሚታወቁ ሰዎችን ጭምር ተመሳሳይ አቋም የያዙበት መሆኑ ልዩ ቦታ የሚሰጠው ፕሮጀክት ነው። እንደ «ዓድዋ ድል» ሁሉ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን በአንድ ጥላ ስር ማሰባሰብ የቻለ፣ የመላ ኢትዮጵያውያንን ቀልብ የገዛና የሁሉም ዜጎች አሻራ ያረፈበት ነው። በመሆኑም ግድቡ ከኃይል ማመንጫነቱ ባሻገር ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ፣ ከደቡብ እስከ ሰሜን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የአንድነታቸውና የትብብራቸው ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ግድብ ነው።

ይህ ግድብ በኢትዮጵያውያን አዕምሮ ውስጥ የይቻላል መንፈስ እንዲጎለብት ያደረገ ነው። በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ ለመገንባት ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ብዙ ጥረት ሲደረግ በግብጻውያን ጫና ከውጭ ብድር እና እርዳታ ማግኘት አለመቻሉ ኢትዮጵያውያን ሀብታቸውን እንዳይጠቀሙ አድርጎ ቆይቷል። የዛሬ አስራ አንድ አመት ገደማ የውጭ ኃይል ድጋፍ እና እርዳታ ሳያስፈልግ በራስ ጉልበት፣ ገንዘብ እና እውቀት ግድቡን ለመገንባት መጀመሯ በኢትዮጵያውያን አዕምሮ ውስጥ የይቻላልን መንፈስ እንዲጎለብት ያደረገ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ግድቡ የወቅቱ ችግር የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ጫና ለመቋቋም ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው ነው። ግድቡ ከካርቦን ልቀት ነፃ እንደመሆኑ ለአካባቢው ስነምህዳር መጠበቅ የሚኖረው ፋይዳ ትልቅ ነው ።

የ13ቱም ተርባይኖች ግንባታ ሲጠናቀቅ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ አጠቃላይ ኃይል የማመንጨት አቅም 5 ሺህ 150 ሜጋ ዋት እንደሚደርስ የተገለጸ ሲሆን፣ ይህም በአፍሪካ ውስጥ ትልቁ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ አመንጪ ያደርገዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚስተዋለውን የኃይል መቆራረጥ ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ ፋይዳ የሚኖረው ነው።

የሚመነጨው ኃይል ከኢትዮጵያ አልፎ ለተለያዩ አገራት ኤክስፖርት የሚደረግ መሆኑ የግድቡ ፋይዳው ለቀጣናው ጭምር ነው። በኃይል እጦት ለሚቸገሩት በርካታ የምሥራቅ እና የሰሜን ምሥራቅ አፍሪካ አገራት የኃይል እጥረት ፍቱን መድኃኒት ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።


የኃይል ችግር ከመቅረፍ ባሻገር በአገራቱ መካከል ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲጠናከር በማድረግ የአገራቱ ግንኙነት የተሳለጠ እንዲሆን የላቀ ሚና ይጫወታል። በኢኮኖሚ የተሳሰሩ አገራት በሌሎች መለስተኛ ጉዳዮች የመጋጨት ዕድላቸው ስለሚቀንስ ለአካባቢው ሰላምም ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት የዘርፉ ልሂቃን ያብራራሉ።

በሌላ በኩል የአገራችን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በአገራት መካከል የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያስቀድምና ሁሉንም የተፋሰሱን አገራት ሕዝቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ «ፍትሃዊ የውሃ ክፍፍል» መርህን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ መርህም በዓለም አቀፍ ደረጃ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ነው። የህዳሴው ግድብ ሱዳንና ግብጽ ግድቦቻቸውን ከደለል የሚታደግ፣ በትነት የሚባክነውን ከፍተኛ ውሃ የሚቀንስ፣ ዓመቱን ሙሉ ተመጣጣኝ የውሃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል ከመሆኑም ባሻገር የኤሌክትሪክ ኃይል በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው ስለሆነ አገራቱን ከኢትዮጵያ ባልተናነሰ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል። የግድቡ ወጪ ሙሉ በሙሉ የሚሸፈነው በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ቢሆንም ፕሮጀክቱ የአካባቢውን አገሮች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያጠናክር ነው።

ሆኖም ከግብጽና ከሱዳን በኩል ግድቡ ውሃ መያዝ ከመጀመሩ በፊት አሳሪ ስምምነት ላይ ተደርሶ ፊርማ እንዲቀመጥ ሲወተውቱ ቆይተዋል። ለዘመናት በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ መገንባት ቀርቶ ኢትዮጵያ አንዲት ብርጭቆ ውሃ መጠቀም አትችልም የሚል አቋም ይዘው ሲንቀሳቀሱ የቆዩ የታችኛው ተፋሰስ አገራት በተለይም በግብጽ ላይ ኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ድል እንድትጎናጸፍ ያስቻለ ግድብ ነበር። ከምንም በላይ በኃይል ለማስፈራራት ጥረት ስታደርግ የነበረችው ግብጽ የኢትዮጵያን አቅም እንድትረዳ ያደረጋት ነበር። ለዘመናት እንደ መሣሪያ ስትጠቀም የቆየውን የማስፈራራት አካሄድ ትታ በጠረጴዛ ዙሪያ እንድትወያይ በማስቻል ኢትዮጵያ ከፍ ያለችበትም ነው።

ምንም እንኳ አሁንም ከግብፅና ከሱዳን ተደጋጋሚ ቅሬታዎች ቢነሳም ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ በሁለት ዙር ግድቡን በውሃ የመሙላት ሂደትን ከማከናወን አልፋ ኃይል ማመንጨት የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ደርሳለች።፡ በቀጣይም ግብጽና ሱዳን ዘመኑ ያለፈበትን የቅኝ ግዛት ዘመን ስምምነቶችን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን የሚያደርጉት ጥረት የሚያመጣው ምንም ዓይነት ለውጥ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። አገራቱ በቅኝ ግዛት ዘመን ውል ላይ ሙጭጭ ማለታቸውን ትተው ዘመኑን በመዋጀት የፍትሃዊ ተጠቃሚነት መርህ ተገዥ ሊሆኑ ይገባል።

የዚህ ግድብ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ለታለመለት የልማት ሥራ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት እስኪጀምር ድረስ ድረስ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በገንዘብ፣ በጉልበት እና በእውቀት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ አጠናክረው መቀጠል አለባቸው።



ታሳቁ የህዳሴ ግድብ ሙሉ ስሙሉ ሲጠናቀቅ የቀረው 16 በመቶ ብቻ ነው፤

# ርዕሰ አንቀፅ


## የኢኮኖሚ ነጻነታችን ማብሰሪያ የብርሃን ማህተም!

ሉዓላዊነቷ ባልተደፈረ አገር የሚኖር ነጻ ሕዝብ፣ ነጻነቱ አካላዊነቱ ብቻ ሳይሆን አዕምሮውም ጭምር ነው:: የዚህ የአእምሮ ነጻነት መመዘኛ ከሚሆኑ ጉዳዮች መካከል ደግሞ በነጻነት ሃሳብን ወደ ተግባር የመለወጥ አቅም ነው:: በዚህ መልኩ ኢትዮጵያውያን በማንነትና ክብራቸው የመጣን ሁሉ በብርቱ መስዋዕትነት በቃ ብለው ሸኝተው ታፍረው ኖረዋል፤ እየኖሩም ናቸው:: ይህ ታፍሮና ተከብሮ የመኖር የሃሳብ ከፍታ ግን ምሉዕ ይሆን ዘንድ እንደ ክብርና ሉዓላዊነቱ ሁሉ፤ ኢኮኖሚያዊ አቅም መፍጠርና አለመፍጠር ሌላኛው መመዘኛ መሆኑ አይቀሬ ነው::

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳን ነጻ ሉዓላዊ ግዛታቸውን አስከብረው የኖሩ ቢሆንም፤ ኢኮኖሚያዊ ነጻነታቸውን በዛው ልክ ማስጓዝ ባለመቻላቸው በየዘመናቱ ከፍ ያሉ ፈታኝ ሁነቶችን ሲያስተናግዱ ዘልቀዋል:: ይሄን የኢኮኖሚ ከፍታ እውን ከማድረግ አኳያም ብዙ ጥረውና ወጥነው፤ ውጥናቸው ለተግባር፤ ጥረታቸው ለፍሬ ሳይበቃ ትውልድ በትውልድ እየተተካ ነጉዷል:: የዚህ ጥረትና ውጥን አንዱ ማሳያ ደግሞ የዓባይ ወንዝን አልምቶ ራትም መብራትም፤ በማድረግ የኢኮኖሚ ልዕልናን የመፍጠር ሕልም ነው::

ዓባይን የመሳሰሉ ወንዞች ላይ የሚከወን የልማት ሥራ ሃገራዊ ኢኮኖሚውን ከማሻገር አኳያ ያለውን ከፍ ያለ ፋይዳ የተረዱት ቀደምት ኢትዮጵያውያን፤ ይሄንኑ ሃሳብ ሲያወጡና ሲያወርዱ ቢኖሩም፤ ይሄን ታላቅ ሃሳብና ሕልም ወደ ንድፍ መለወጥ የቻሉት ግን ንጉሥ አፄ ኃይለሥላሴ ነበሩ:: ይሁን እንጂ ንድፉን ወደ ተግባር የመለወጥ ሂደቱ አንድም በራስ አቅም፤ ካልሆነም በረጂ ሃገራትና ተቋማት እገዛ ላይ የተንጠለጠለ ነበር:: ሆኖም በራስ አቅም ያንን ማድረግ የማይቻል ነበር፤ በአገራት ድጋፍና በተቋማት እገዛ ማከናወን ደግሞ ኢትዮጵያን የማንበርከክ ጽኑ ፍላጎት ያላቸውን አገራት ደጅ መጥናት ነበርና ይሄ ደግሞ ፈጽሞ የማይታሰብ፤ ቢታሰብም ይሁንታ የማይቸረው ነበር::

ይሄን የተገነዘቡት ንጉሥ ኃይለሥላሴም፣ መጪው ትውልድ አቅም ሲፈጥር ይተገብረዋል ብለው ሰነዱን ለትውልድ በአደራ አስተላለፉት:: ይሄን አደራ የተረከበው የደርግ መንግሥትም ቃሉን በተግባር ለማዋል ተደጋጋሚ ምኞት ቢኖረውም፤ ይሄን ማድረግ የሚያስችለውን የእፎይታ ጊዜ ሳያገኝ፤ በውስጥም በውጪም በሚነድዱ የፖለቲካ ትኩሳቶች እንደተለበለበ ለመለወጥ በቃ:: ከደርግ ማግስት የመጣው ኢህአዴግም ቢሆን በውስጥ ያለውን ችግር ማቃለል፤ በውጭ ያለውን ጫናም የፍላጎት ተገዢነቱ ላይ ተመስርቶ




ማርገብ ቢችልም፤ የቀደምቶቹን ሕልም ወደተግባር ለመለወጥ ግን ከደርግ የሥልጣን ዘመን የላቀ ጊዜን (ሃያ ዓመታትን) ፈጅቶበት ነበር::

ሆኖም ለሁሉም ጊዜ አለውና የዓባይ ወንዝ ፕሮጀክት መተግበሪያ ወቅቱ ሲደርስ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት ይፋ ሆነ፤ ሕልም ወደ ትልም፣ ትልምም ወደ መሬት ወረደ:: በራስ አቅም ሊተገበር፤ በራስ ፋይናንስ ሊሳለጥ፤ በጥቅሉ በጦር ግንባር የታየው የአሸናፊነት ልዕልና በኢኮኖሚው መስክ ሊደገም ሁሉም ከራስ ለራስ ሆኖ ተጀመረ:: በቁጭት የኖረ ሕዝብ ከዓባይ ብርሃንን ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚው መስክ ልቆ የመታየት ልዕልና ሊጎናጸፍ በአንድ ተሰለፈ::

ይህም ጉዞ እንደ ቀደመው አቅም ነስቶ የሚገታ ባይሆንም ፈተናዎች የተለዩት አልነበረም:: በውጪ የግብጽና ግብራበሮቿ ስራውን ለማስተጓጎል ከዲፕሎማሲና ፕሮፖጋንዳ እስከ ጦር የማዝመት ፉከራ የደረሰ መፍጨርጨር በጉልህ ታይቷል:: ይሁንና የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከሌለው ቀንሶ ቦንድ በመግዛት የነገውን ብርሃን የናፈቀ ሕዝብ ግን ይሄንን የውጪ ጫና ለመቋቋም በሕብረት ከመቆም፤ መንግሥቱንም ከማበረታታት ተቆጥቦ አያውቅም፤ እናም የውጪው ጫናና ጫጫታ ከጉዞው ያገደው አልሆነም:: ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ግን የውስጥ ችግር ሌላው የፕሮጀክቱ ትብታብ ሆኖ ነበር:: ይህ ደግሞ ሕዝብ ከሌለው ያዋጣውን ሃብት እስከመመዝበር የደረሰ ሌብነትና የአሰራር ብልሹነት ለግድቡ እውን መሆን በሚደረገው ጥረት ላይ ጥላ ያጠላ የማይታለፍ ብስባሽ ሆነ::

ይሄና ሌሎች መሰል አገራዊ ችግሮች የወለዱት ለውጥም የተበላሹና መወገድ ያለባቸው የቆሸሹ ጉዳዮችን በማጽዳት ሂደት፤ የሕዳሴውን ግድብ ከባለህበት ሂድ ጉዞው እንዲነቃቃ፤ ከተኛበት ተነስቶም እነሆ የመጀመሪያውን ብርሃን ለማሳየት አበቃው:: ሕዝቡንም የጦር አውድ ነጻነቱን በልማቱም አውድ ደግሞ የኢኮኖሚ ጥገኝነቱን ታሪክ ሊያደርግ፤ ለብስራት ብቅ ያለውን የሕዳሴ ወጋገን ተከትሎ ከቦግታው ሊደርስና የማይደበዝዝ ማህተሙን ሊያሳርፍ ከዳር ዳር አነቃቃው!

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ
ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::**

# ዓባይ እያንዳንዳችንን ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በሰው ልጅ የዘመናት ታሪክ ውስጥ ብዙ ኩነቶች ይሄዳሉ ይመጣሉ። ሁሉም ባይሆኑም በሰው ልጅ ቁጥጥር ስር ሆነው የሚያልፉ ናቸው። ሆኖም አንድነትና መተባበርን ባህል ላደረገ ማህበረሰብ የትኛውም ችግር ከአቅሙ በላይ አይሆንበትም። በዘመናት የሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከሰው ልጅ አቅም በላይ ሆነው ያለፉ ችግሮች ሁሉ በአንድነትና በተባበረ ክንድ ስላልተመከቱ ነው። አንዳንድ ጊዜ በዚህ ረገድ የሚከሰቱ የመከራ ፍሬዎች ጣፋጭ ናቸው። የጥፍጥናቸው ጣዕም ሀገርና ህዝብ ላይ ሲያርፍ ደግሞ ትርጉማቸው ሌላ ይሆናል። ልክ እንደ እኛና እንደተጓዝንበት የህዳሴ ተስፋችን ሁሉም እንግልቶች ፍሬ ከማፍራታቸው በፊት መራራ ናቸው። ድካም ፍሬ ሲያፈራ፣ እንግልት ዋጋ ሲያወጣ መከራችንን እንደ አለፈ ውሀ እንረሳዋለን። የዓባይ መንገድም እንዲሁ ነው፤ ትናንት በሃሳብ ተጠንስሶ ዛሬ ለብርሃን እስኪበቃ ያለው ውጣ ውረድ ግዙፍ ነው፤ ሆኖም አባይ በትንሳኤው ያንን ሁሉ አስረሳን።

የህዝቦች አንድነት ማጣት ትንሹን ችግር ትልቅ የማድረግ ሀይል አለው። ከዛሬ መቶ ሀያ አምስት አመት በፊት ኢትዮጵያውያን በተባበረ ክንድ ወራሪውን ጣሊያንን ድል መተው ስማቸውን በወርቅ ቀለም የጻፉበት ታሪክ ነበር። በሌሎችም በርካታ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያስመዘገቧቸው ድሎች የአንድነታችን ውጤቶች ሆነው ያለፉ ናቸው። ልክ እንደትናንቱ ሁሉ ዛሬም የአሁኑ ትውልድ የጥንቱን የአባቶቹን የአልሸነፍ ባይነት ባህል በአባይ ላይ ደግሞታል። ታላላቅ ነገሮች ሁሉ በእችላለው መንፈስ የተሰሩ እንደመሆናቸው፤ እችላለው ብሎ ለተነሳ ሀገርና ህዝብ የማይቻል ነገር የለም። ታላቁ የህዳሴ ግድብም በኢትዮጵያዊያን የእንችላለን መንፈስ ተጀምሮ በእንችላለን መንፈስ እንሆ ለብርሀን በቃ፤ይህ ታሪካዊ የህዝቦች የጋራ ቅርስ ድካማችንን ወደ እልልታ የቀየረ የኢትዮጵያውያን የተስፋ ምልክት ነው።

አባይ ለዚህኛው ትውልድ የተጋድሎ፣ የመስዋዕት የአርበኝነት ጥግ ነው። ስለ አባይ እያሰቡ ኖረው እያሰቡ የሞቱ አባቶች ነበሩን። ስለ አባይ እያሰቡ ተወልደው፣ እያሰቡ ያረጁ ብዙ ናቸው። ዛሬ ግን በዚህኛው ትውልድ አባይ ከወንዝነት ወደ ግድብነት ከግድብነትም ወደ ሀይል ማመንጫነት ተሸጋገረ። አባይ ወንዝ ብቻ አይደለም፤ለእኛ ለኢትዮጵያዊያን ታሪካችን፣ እርማችን መታወቂያችንም ጭምር ነው። በላባችን ወዝ የቆመ፣ በአጥንትና በደማችን የገነባነው የማንነታችን ወጋግራ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ በብዙ ልዩነት ውስጥ አንድነትን ያስተማረን፣ በብዙ መለያየት መካከል መተሳሰብን ያሳየን፣ ፍቅርን መተሳሰብን የሰጠን በትውልድ መካከል የተሰመረ በኩራችን ነው። የህዳሴ ግድባችንን በተመለከተ እንዲህ ነው የሚሰማኝ። ይሄ የአብሮነት ስሜት እስከመጨረሻው አብሮን እንደሚዘልቅ ጥርጥር የለኝም። የመጨረሻውን ሳቅ እስክንስቅ ድረስ ከአባይ ጋር ወደ ፊት እንሄዳለን።

ምክንያቱም በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ አባይ በዝቶና ተትረፍርፎ አለ። በብዙ ድህነት፣ በብዙ ችግር ውስጥ ሆነን የተሻለ ነገን ለማየት ስንል ቦንድ የገዛን እልፎች ነን። በትምህርት ቤት፣ በስራ ቦታ፣ በሰፈር፣ በቀበሌ ለአባይ ግድብ ድምጻችንን ያሰማን ሞልተናል። መጪው ትውልድ በኩራትና በሞገስ ሲያስታውሳችሁ ይኖራል። በእናተ ነፍስ ውስጥ የአባቶቻችሁ ነፍስ እንደሚያርፉ ስነግራችሁ ከልቤ ነው። በእናንተ ዛሬ ውስጥ ተስፋ ያጡ በርካታ ትናንቶች ፍሬ እንዳፈሩ ስነግራችሁ በታላቅ እውነት ነው። አባይ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ የተሳለ ህብረ ብሄራዊ አሻራ ነው። በደስታና በሀዘን ያጌጡ፣ በውጣ ውረድ የተፈተኑ አስራ አንድ አመታትን ከአባይ ጋር አሳልፈናል። ከአፋችን ላይ ሳይጠፉ፣ ከልባችን ሳይሰወር እንሆ በብርሀን ሊያጥለቀልቀን አንድ ብሎ ከአንድ ጀመረ፤ ቀሪ ተርባይኖቹ ወደ ስራ ሲገቡ ሙሉ ብርሃን ይሆነናል።

አባይ ለእኛ ተስፋ ብቻ ሳይሆን መለያየታችንን ሊሽር በመካከላችን ለእርቅ የገባ ሽማግሌ ነው የሚመስለኝ። በብዙ ነገር ተለያይተን በአባይ ጉዳይ ግን አንድ ነን። ተኮራርፈን እንኳን ስለ አባይ አንድ ላይ የምንቆም ህዝቦች ነን። አባይ አስታራቂያችን ነው። አባይ ሽማግሌአችን ነው። አባይ የአንድነታችን ሙሴ ነው። ለዚህም ነው አባይ ከወንዝነት ባለፈ ብዙ ነገራችን ነው ያልኩት። ዛሬ ብቻ አይደለም ከአባይ ጋር ብዙ ነገዎች አሉን። ብዙ ቀናት፣ ብዙ ዘላለማት፣ እልፍ አዕላፍ አመቶች ከአባይ ጋር ይጠብቁናል። እርሱ በአባቶቻችን ልብ ውስጥ የነበረ ባለ ብዙ ውበት፣ ባለ ብዙ ቁንጅና ባለቤት ነው። ከዚያኛው ትውልድ የተረከብነው የአባቶቻችን የአደራ ሰነድ ነው። ውሀ ብቻ አይደለም ከእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ የሚፈስ የቁጭት እንባ ነው። በእያንዳንዳችን ነፍስ ውስጥ ያለ የህላዊ ደም እንዲህም ነው። አባይ እያንዳንዳችንን ነው። የእያንዳንዳችን መልክ፣ የእያንዳንዳችን ውጣ ውረድ ማስታወሻ ነው። በአባይ ውስጥ እኛ አለን። አባይ ሲነሳ እኛ ሁላችንም እንነሳለን። አባይ የመቶ ሀያ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን ወዘና ነው። የሰማኒያ ብሄር ብሄረሰብ ቀለም ነው። ባህላችን፣ ታሪካችን ነው።

ለዘመናት ከደጃችን እየፈለቀ የእትብቱ ማደሪያ የሆነውን ቀዬ ግን ውሀ እያስጠማ ባዕድ ሀገራትን ሲያረሰርስ የኖረበት ዘመን አልፎ፤ ዛሬ ላይ በአስራ አንድ ዓመት ጉዞው ዛሬ ላይ እንደተመኘነው ብርሀንን መስጠት ጀምሯል። እኛም፡-

**"አባይ ተሞሸረ..እኛም እልል አልን...**
**በተባበረ ክንድ ትንሳኤውን አየን.."**

በማለት ነገን እያሰብን የህልማችን ፍጻሜ የሆነውን የግድቡን መጠናቀቅ እያሰብን በተስፋ ቆመናል። ከሳቅን ከእንግዲህ ነው...ከበረታን...ከደመቅን ከእንግዲህ ነው። ከጊዮን ማዶ ሊስቁ ያሉ በርካታ ፊቶች ይታዩኛል። ከጥቁር ህዝቦች አብራክ ስር ተስፋ ያወገገው ጸዳል ይታየኛል። ሀዘን የረሳቸው...የሚፍነከነኩ ጸዐዳ ልቦች ፈገግ ብለው ይታዩኛል። ዘለዓለማዊ ፈገግታ...። አባይ እናመሰግናለን..አንተ ኩሩ ህዝብ ክብር ይግባህ።

በአንድ ልብ፣ በአንድ ሀሳብ ስለ አባይ እያዜምን አስር አመታትን ተጉዘናል። በነዚህ አስር አመታት ውስጥ ብዙ ነገር አይተናል..ስለ አባይ ተገፍተናል፣ ጫና ደርሶብናል። የጦርነት ነጋሪት እየጎሰሙ ከተስፋችን ሊያደናቅፉን የሚሞክሩ ነበሩ። በአንድ ላይ ሆነን ሁሉን አልፈነዋል። ከሌለን ላይ እየሰጠን፣ ካለን ላይ እየቀነስን፣ ከድህ እና መቀነት በተሰጠ አምስትና አስር ሳንቲም እንሆ ለአይናችን ከናፈቀን ማለዳ ላይ ደረስን። ከእንግዲህም በአባይ ጉዳይ ላይ የሚያቆመን የለም። አባይ ብሄራዊ መዝሙራችን ነው። ተኝተን በተነሳን ቁጥር፣ በኖርናት በእያንዳንዷ ንጋት ልክ የምናስበው የመኖራችን ዋስትና ነው። ጥንት አባቶቻችን በአድዋ ላይ እንዳስመዘገቡት ድል ሁሉ እኛም የዚህ ዘመን ትውልዶች አባይን ገድበን መጪውን ትውልድ ከድህነት የማውጣት ጀብደኝነት በእያንዳንዳችን ውስጥ አለ። በዚህ አንቀምም እንደ አባይ ያሉ ሌሎች ግድቦችንም በመገደብ ለሀገራችንና ለህዝባችን ውለታ የምንውልበት ጊዜ ላይ ነን። የድካማችንን ፍሬ የምንበላበት ብሩህ ጊዜ እየመጣ ነው። ሰላም!

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የህይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ለአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## “እናንት አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳፅ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው”

(ኤፌ 6:4)

ግርማ መንግሥቴ

በሁላችንም ዘንድ እንደሚታወቀው፣ ሁላችንም የአብ ልጆች ነን። (ዮሐንስ 1፥12-13) አንድ በጉዳዩ ላይ እየሰሩና ቀጥለን ከምንነጋገርበት ታሪክ ጋር ተያያዥነት ባለው ጉዳይ ዙሪያ በብሎጋቸው (“አስተምህሮ ዘተዋህዶ” ይሰኛል) በሚያሰራጯቸው መጣጥፎች ላይ እንዳሰፈሩት “አባቶች የሚባሉት እነማን ናቸው?” በማለት እራሳቸው ይመልሱት ዘንድ ለራሳቸው ባቀረቡት ጥያቄ መልሱን ሲሰጡ፤

በመጀመሪያ ደረጃ ‘አባት’ ማለት ልጅን የወለደ እና/ወይም ለልጅ ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ አስተዋጽኦ ያለው ማለት ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የሁሉም አባት (የነፍስና የሥጋ) እግዚአብሔር ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ “ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ” ያለው ከሁሉም አስቀድሞና ከሁሉም በላይ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው። በሥጋ የወለደን ደግሞ ወላጅ አባት ይባላል፡፡

“በዋናነት አባት የሚያሰኛቸው የአባትነት አገልግሎታቸው ነው።” ሲሉም ነው የሀሳባቸውን አንቀፅ የደመደሙት። አዎ፣ አንድን “አባት” አባት የሚያሰኘው ለአብራኩ ክፋይ ለሆነው ልጁ የአባትነት አገልግሎትን ሲሰጥ እንጂ ስለወለደው ብቻ አይደለም። የመውለድ የመውለድማ “እበትም ......” ተብሎ የለ እንዴ፤ ለዛውም ገና በጠዋቱ።

ይህ ጸሐፊ የሰውን ልጅ የዘር ሐረግ መምዘዝ መቼ እንደተጀመረ እቅጩን መናገር ባይችልም፣ የተለመደውን መልስ “እድሜ ጠገብ” ነው በማለት መመለስ ግን አያቅተውም። እናም፣ የሰውን ልጅ የዘር ሐረግ መምዘዝና እከሌ የእከሌ ዘር፣ እከሌ የእከሌ ልጅ፣ እከሌ በአባቱ ...፣ እከሉ በእናቱ ...፣ የወንድማማች ልጆች ...፣ የእህትማማች ልጆች ... (ዝርዝሩ ብዙ ነው) በማለት ሰዎችን በየወገናቸው፣ ስጋና ደማቸው መመደብ የተጀመረው ዛሬ ሳይሆን የቆየ፤ እድሜ ጠገብ ነው ማለት ነው።

ይህ ለይቶ የመመልከቻ አጉሊ መነፅር በአደጉትም ሆነ ባላደጉት አገራት፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ሳይቀር ያለ እውነታ ነው። ሰዎችን በዚህ መልክ መለየቱም ታሪካዊ ዳራው እሩቅና ጥልቅ ሲሆን፣ ምክንያቱም የዛኑ ያህል የዋዛ አይደለም።

ይህን መንደርደሪያ ከርእሳችን ጋር በማገናዘብ አንዳች ረብ ያለው ብያኔ ላይ መድረስ ይቻላልና ይህንን በዚሁ አቁመን ወደ ተነሳንበት፣ የገዛ አባቱ ሰለባ ወደ ሆነው እምቦቀቅላ ታሪክ እንሂድ። ስንሄድ ግን የጉዟችንን መጀመሪያ “እናንት አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳፅ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው።” (ኤፌ 6:4) ብናደርግ ሂደታችን ቀና ይሆናል።

ይህ፣ የዛሬው እምቦቀቅላ እንግዳችን ዮናስ ታምሩ ይባላል። የአስር አመት ታዳጊ ሲሆን በጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (ጌዴኦ ዞን፣ ዲላ ከተማ) የሶስተኛ ክፍል ተማሪ ነው።

ታሪኩ እንደ ማንኛውም ልጅ “ልጅ” ይሁን እንጂ፣ እንደ ማንኛውም ተማሪ “ተማሪ” ይሁን እንጂ ... ከጓደኞቹ የሚለየው ነገር አለ። ይህ ልዩነቱ ደግሞ በራሱ የመጣ፣ ወይም ተፈጥሮ የሰጠችው አይደለም። ይልቁንም ተፈጥሮ ሙሉ አድርጋው በማይታመን ሁኔታ የገዛ አባቱ ነው ለልዩነቱ መፈጠር መንስኤ። በጉዳዩ ላይ ታሪኩ በሚማርበት ጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአካል ተገኝተን አነጋግረነዋል።

እግርህን ምን ሆነህ ነው?

አባቴ ነው።

አባትህ ምን አደረጉህ?

በቢላ ነው እንደዚህ ያደረገኝ።

ለምን?

እናቴን እመታለሁ ብሎ።

እንዴት አድርገው?

ቢላውን ወደ እሷ ሲወረውረው እግሬን መታኝ።

ስንት ሰአት ይሆናል?



ፎቶ፡- አብነት ሽፈራው

አስራ አንድ ሰአት።

(ይህንን እዚሁ ላይ አቁመን ወደ ትምህርቱ ሄድን።)

ስንተኛ ክፍል ነህ?

ሶስተኛ።

ትምህርቱ እንዴት ነው?

ጥሩ ነው፤ ደስ ይላል።

ትምህርት ትወዳለህ፣ መማር ትወዳለህ ማለት ነው?

አዎ፣ እወዳለሁ። እወዳለሁ .... (መናገር የሚፈልገው ነገር እንዳለ እያስታወቀበት፤ ግን ደግሞ ሊገልፀው ያልፈለገው ....)

እንዴት ዳንክ ታዲያ አሁን?

ሀኪም ቤት፣ ሀኪሞች ሀኪም ቤት ወስደው አከሙኝና ዳንኩ።

አሁን ያምሀል?

አይ።

ማን ነው ያከመህ?

ዶክተሮች።

ማን ነው የሚረዳህ አሁን።

እነሱ ናቸው።

ሌላ ማንም የለም?

የለም።

ይሄንን (መደገፊያውን) የሰጠህ ማን ነው?

ዶክተሮቹ ናቸው።

ደብተር .... የሚገዛልህስ ማን ነው?

እነሱ፣ አሁን ያቆማሉ። ሌላ የሚገዛልኝ ባገኝ ...

(እኛም ከእሱ ጋር እያደረግን ያለውን ውይይት በዚሁ አቆምን።)

ታዳጊ ዮናስ እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነው እግሩን ያጣው። ገና ምኑንም ሳያየው አካለ ጎደሎ የሆነው። የገዛ አባቱ ነው ገና ከጓደኞቹ ጋር እንኳን ሮጦ ሳይጠግብ በድጋፍ መሳሪያ ይንቀሳቀስ ዘንድ የዳረገው። ከላይ “እናንት አባቶች ሆይ፣ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሳፅ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው።” ያልነውን የጌታ ቃል በግልባጩ በተረዳ አባቱ ምክንያት ነው ዮናስ ለእንደዚህ አይነቱ አካላዊ ስቃይና ስነልቦናዊ ጉዳት የተዳረገው።

ዮናስ በአባት ይጠራል እንጂ አባት የለውም። አባቶቹ ነፍሱን ያዳኑት ዶክተሮቹና ችግሩን ተረድተው እንደ ባህርይው እያስተማሩት ያሉት መምህራኖቹና ዙሪያውን ያሉት ጓደኞቹ፤ እንዲሁም አሁን ላለበት የገንዘብና የመማሪያ ቁሳቁስ የሚታደጉት በጎ አድራጊዎች ናቸው። በቃ፣ እነዚህ ናቸው የዮናስ እናትና አባቶች። በ”መዝ 68፥5” እንደተጠቀሰው፣ አባት ለሌለው አባት የሆኑትና የሚሆኑት ናቸው የዮናስ አባቶች። አባቱማ . . .

የዮናስን ጉዳይ ከዮናስ ጋር ጨረስን እንጂ ስለ ታዳጊው ዮናስ ማውራታችንን አልጨረስንም።

ስለ ዮናስ የሚያውቁ፤ አውቀውም ልባቸው በሀዘን የደማ ..... የጮራ ትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላት ጥቂት ወይም ብዙ ሳይሆኑ ሁሉም ናቸው። ሁሉም ስለ ታዳጊና ተማሪያቸው ሲነሳ ፊታቸው የሀዘን ድባቡን ባንዴ ይከናነባል። ይተክዛሉ፤ በልባቸው ኤዲያ ደሞ አባት ብሎ ሰው የሚሉ ሁሉ እስኪመስሉ ድረስ ጥልቅ ሀዘናቸው ያስታውቅባቸዋል። በዚህ ሁሉ መሀል ደግሞ ተስፋም አላቸው።

ተማሪ ዮናስ ትምህርቱን የሚወድና በሚገባም የሚከታተል ልጅ ነው። ሁሌም ሲጠየቅ ለትምህርት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለው ከመናገር ውጪ ሌላ ሀሳብ የለውም፤ ሁሌም ትምህርቱን እንደሚወድ ሲናገር ነው የሚሰማው። ይህ ደግሞ ሁሌም ለመምህራኖቹ ተስፋን የሚያጭር በመሆኑ የአካል ጉዳተኛነት ከምንም እንደማያስቀር በመተማመን የዮናስን የወደፊት ማንነት ከወዲሁ በማየት ይፅናናሉ። ይህ ሁሉ ከጓደኞቹ ጀምሮ በሁሉም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ልብ ውስጥ ያለ ሀሳብ ስለ መሆኑ መጠራጠር አይቻልም። አዎ፣ አካል ጉዳተኝነት ከምንም አያስቀርምና ዮናስ የዛሬ አበባ የነገ ፍሬ መሆኑ የሚያሻማ አይሆንም። ይህ የሚሆነው ግን የዮናስ ዛሬ እንዳይጨልም ከተደረገ ብቻ ነው። አዎ፣ ዮናስ ዛሬ ረዳት ይፈልጋል፤ የሚያስተምረውና ከአባቱ በደል የሚፈውሰው ሰው ይፈልጋል። ባለቅኔው፡-

ሰው ማለት ሰው ማለት፤

ሰው የሆነ ነው ሰው የጠፋ’ለት።

እንዳለው ሁሉ ዮናስ ነገው ብሩህ ሊሆን የሚችለው ዛሬ ሰው ባጣ ጊዜ ሰው ሆኖ ሰው ሊያደርገው የሚፈልግ ሰው ካገኘ ብቻ ነው።

የዮናስን ጉዳይ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ (የታከመበት ዲላ ሪፈራል ሆስፒታልም ቢኬድ ያው ነው ብለውኛል) በሙሉ ቢጠየቅ የሚለው እንደሚኖር ይታወቃል። ይሁን እንጂ ሁሉንም ማነጋገር አይቻልምና ወካይ ሊሆን የሚችል አንድ ሰው መፈለግ፤ ወደ ርእሰ መምህሩ ቢሮም ማቅናት ግድ ሆነ። ተገናኘን። ፍቃደኛም ሆኑ።

የጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር አብነት ሽፈራው ስለ ዮናስ ያላቸውን አስተያየት እንዲህ አቅርበነዋል።

ዮናስ የሶስተኛ ክፍል ተማሪያችን ነው። ጎበዝና ታታሪ ነው። ለትምህርት ልዩ ፍቅር አለው። ከሆስፒታል እራሱ ነው ልማር ወደ ትምህርት ቤት ውሰዱኝ በማለት ሊመጣና ሊማር የቻለው።

ተማሪ ዮናስ ጤነኛ የነበረ ልጅ ነው። በአባትና እናቱ ፀብ መሀል ነው በአባቱ ምክንያት ለዚህ የተዳረገው። በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው። በጣም .... ሁሉም ነገር እንደሚያልፍ እየታወቀ ለእንደዚህ አይነቱ ፀፀት መዳረጉ ተገቢ አልነበረም። ንዴትም ለጊዜው ነው እንጂ እንደሚያልፍ ይታወቃል።

ዮናስን የታደጉት የዲላ ሪፈራል ሆስፒታል የጤና ባለሙያዎች ናቸው። አሁንም እየረዱት ያሉት እነሱ ናቸው። ምግብም ሆነ መኖሪያ እያገኘ ያለው ከእሱው (ግቢ ውስጥ) ነው። አሁን እነሱ ድጋፋቸውን ወደ ማቆሙ ናቸው የሚል ነገር አለ። ከህክምናም ውጪ ሆኗል (ህክምናውን ጨርሷል)። እንደዛ ከሆነ ዮናስ ከሚወደው ትምህርቱ ሊለይ ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ልክ አይሆንምና ረዳት ያሻዋል። ግብረ ሰናይ ድርጅቶችም ቢሆኑ ዮናስን ሊያስቡት ይገባል።

ዮናስ በተለይ የሚያገኘው ልዩ የትምህርት አሰጣጥ ድጋፍ የለም። ከመደበኛ ተማሪዎች ጋር ነው የሚማረው፤ የሚወዳደረውም። ያም ሆኖ በሚገባ እየተከታተለ ነው። የስነ ልቦና ጫና አለበት። ከተማሪዎች ቀድሞ በጠዋት በመነሳት ነው ትምህርት ቤት የሚደርሰው። ጭቃ ሲሆን በጣም ይቸገራል። እንደ ጓደኞቹ ኳስ አይጫወትም። አይቦርቅም። ቤተሰብ አለኝ ብሎ የሚያፅናናው ነገር የለም። እናትየዋም ስራ የላትም። አባትየውም በህግ ተፈርዶበት ማረሚያ ቤት ነው ያለው።

ቤተሰብ በመነጋገር፣ በሰለጠነ መንገድ ... ነው ችግሮችን መፍታት ያለበት። ንዴት እንደሚያልፍና እንደሚበርድም መታወቅ አለበት። ከዘላለም ፀፀት ለመዳን መታገስ ተገቢ ነው። ያ ባለመሆኑ ነው እንግዲህ ተማሪያችን የሆነው ዮናስ ገና በልጅነቱ ለእንደዚህ አይነቱ አስከፊ ጉዳትና አካል ማጣት የተዳረገው።

ርእሰ መምህር አብነት ሽፈራው ሀዘን በነካው ስሜት ሀሳባቸውን እየገለፁ ነው። እንደ ርእሰ መምህር አብነት ከሆነ ተማሪ ዮናስ የደረሰበትን ችግር ለመቋቋም፤ ከደረሰበት ስነ-ልቦናዊም ሆነ ፋይናንሻል (የገንዘብ) ጉዳት ለመላቀቅ ዘላቂ መፍትሄ ይፈልጋል። በተለይ ሰብአዊ ተቋማት አለን ሊሉት ይገባል። እርዳታ ሰጪ ድርጅቶችም ሆኑ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች፤ አልያም በልጆች ላይ እየሰሩ ያሉ መንግስታዊም ሆኑ አልሆኑ ለተማሪ ዮናስ ሊደርሱለት፤ አለንልህ ሊሉት ይገባል።

ተማሪ ዮናስ ከፍተኛ የሆነ ትምህርቱን የመከታተል ፍላጎት አለው። ይህ በምንም መንገድ ሊስተጓጎልበት አይገባም። እንዳይስተጓጎልበት ደግሞ ቋሚ ድጋፍን ይሻል። ድጋፍን ካገኘ ዮናስ በትምህርቱም ሆነ በአጠቃላይ ህይወቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የማይደርስበት ምክንያት የለም፤ ይደርሳል። ለዚህ ደግሞ የእሱው ክፍል መምህርት የሆነችው (የምታስተምረው) መምህርት ማርታ ታምራት በየነ በቂ ማሳያ/ምሳሌ ነች።

(ርእሰ መምህር አብነት ሽፈራው መምህርት ማርታ ታምራት በየነ ከ20 አመት በፊት የገዛ አባቷ ሁለት ቀን ሙሉ እጆቿን ወደ ኋላ አስረዋት ከቆዩ በኋላ ስትፈታ እጆቿ ከጥቅም ውጪ በመሆናቸው ቀኝ እጇ የተቆረጠ መሆኑን፤ ማርታ ግን ከዛ ሁሉ የህይወት ምስቅልቅሎሽ ውስጥ ወጥታ፣ ተምራ፣ ተመርቃ ዛሬ የጮራ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርትና የአንድ ልጅ እናት ለመሆን የበቃች መሆኗን አጫውተውናል።)

### የርእሰ መምህር አብነት ሽፈራው የማጠቃለያ ሃሳብ

አይደለም ሰው እና ሰው እግርና እግርም ይጋጫል። ይህ እውነት ነው። ችግሩ ያለው ያንን ችግር ወይም ግጭት ለመፍታት የሚኬድበት መንገድ ነው። ለሚያልፍ ቀን፣ ለሚያልፍ ንዴት፣ ለሚያልፍ ስሜት ... ተብሎ እራስን የማያልፍ ፀፀት ውስጥ መክተትም ሆነ፤ ሳይታሰብ የሰውን ህይወት አደጋ ላይ መጣል በፍፁም ተገቢ አይደለም። እንደዛ ማድረግ እራስን እማይወጡት ፀፀት ውስጥ መክተት ነው። ቢፀፀቱም እንኳን ተመልሰው የማያገኙትን፣ የማያድኑትን ስህተት ነው የሚፈፅሙት። እንዲህ አይነት ነገሮች እየተበራከቱ ነው። ይኸው እዚህ እኛ ጋ እንኳን ሁለት የድርጊቱ ተጎጂ ሰዎችን አየን። ይህ የሚያሳየን ጉዳዩ እየተበራከተ እንጂ እየቀነሰ አለመሆኑን (ጉዳዩ ከሴቶች መብት አኳያ ሊታይ የሚችል) ነው። በመሆኑም ይህ አይነቱ ተገቢ ያልሆነ ተግባር እንዳይቀጥል ሁሉም ሊረባረብና ሊያከስመው ይገባል። የሀይማኖት አባቶችም ለተከታዮቻቸው ሊያስተምሩ ይገባቸዋል። እንዲህ አይነቱ ተግባር በፈጣሪ የሚወደድ አለመሆኑን ሊያስተምሩ ይገባል።

አሁን የፈሰሰ ውሀ አይታፈስምና ዮናስና እሱን መሰል ህፃናት ሳይወዱ በግድ ከመጣባቸው ስነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካላዊ ... ጉዳት ሊታደጉ ይገባል። አቅም ያለው ሁሉ አለሁ ሊላቸው ይገባል። እንደ ዜግነትም ሊረዱ፣ ሊደገፉ ... የግድ ነው።

እኛም እንላለን፤ መጽሐፉ “አባት ልጁን ይወዳል” (ዮሐ 3፥35) ይላል እንጂ “... ይጠላል” አይልም። ታዳጊና ተማሪው ዮናስም ባይናገረውም “... አባቴ እና እናቴ ቢተውኝም፣ ጌታ በእቅፉ ይቀበለኛል።” (መዝሙር 27:10) አይልም፤ ወይም አላለም ማለት አይቻልምና በእቅፉ የሚቀበለው ሰው፣ ወገን፣ ድርጅት .... አያጣም ብለን እናስባለን። ዮናስም እንደ አስተማሪው ማርታ ትልቅ ቦታ ደርሶ የምናይበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።

የር/መ/ር አብነትን “ ... ዮናስ ዘላቂ መፍትሄን ይሻል ... ቋሚ ድጋፍ ያስፈልገዋል ...” የሚለውን እኛም እየደገምን፤ ለዮናስ መልካም ምኞትን፤ ለዮናስ አባት አይነቶች ልቦናን ይሰጥልን ዘንድ እንመኛለን።

# ስፖርት

# የአውሮፓ ቻምፒዮንስሊግ ዋንጫ በኢትዮጵያ

**ብርሃን ፈይሳ**

በርካታ ተመልካቾች ያሉት የአውሮፓ ቻምፒዮንስሊግ ዋንጫ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ታቅዷል። ከዋንጫው ጋር ዝነኛው አውሮፓዊ የቀድሞ እግር ኳስ ተጫዋችና አሰልጣኝ እንደሚመጣም ታውቋል።

በዓለም ዙሪያ ተወዳጅና በርካታ ተመልካቾችን ያፈሩት የአውሮፓ እግር ኳስ ውድድሮች በኢትዮጵያም ከፍተኛ አትኩሮትን ማግኘት ችሏል። የአህጉሩ ትልቁ ዋንጫ የሆነውና ታላላቅ ክለቦች የሚዋደቁለት የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ ደግሞ በእግር ኳስ ቤተሰቡ ዘንድ ተጠባቂ ከሆኑት መካከል ነው። ዋንጫው በተለያዩ የዓለም ሃገራት እየተዘዋወረ የሚጎበኝ ሲሆን፤ ኢትዮጵያም ከመዳረሻዎቹ የአፍሪካ ሃገራት መካከል አንዷ ናት። በመሆኑም በመጪው ሚያዚያ 02 ቀን 2014 ዓ.ም ባለ ትልቅ ጆሮው ዋንጫ በአዲስ አበባ ለስፖርት ቤተሰቡ እይታ የሚቀርብና ፎቶ የመነሳት መርሀ ግብር እንደሚዘጋጅ ሃይንከን ኢትዮጵያ፣ በውጪ ግንኙነትና ሰስቴኔብሊቲ ስራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ በሻህ በኩል አስታውቋል።

ከዋንጫው ባሻገር ከአውሮፓ የቀድሞ ኮከብ እግር ኳስ ተጫዋቾች መካከል አንዱ የሆነው ክላረንስ ሴዶርፍ በአዲስ አበባ የአንድ ቀን ቆይታ የሚኖረው መሆኑም ታውቋል። በተዘጋጀው መርሃ ግብር መሰረት በሸራተን አዲስ ሆቴል እና በአበበ ቢቂላ ስታዲየም ከአድናቂዎቹ ጋር በቅርበት የሚገናኝበት አጋጣሚ ተፈጥሯል። ተጫዋቹ በአበበ ቢቂላ ስታዲየም በሚኖረው ቆይታም ከኢትዮጵያ ወጣት ብሄራዊ ቡድን ጋር ጨዋታ ያደርጋል። ይኸውም የሚሆነው የመጀመሪያውን ግማሽ የጨዋታ ሰዓት ከአንደኛው ቡድን ጋር ቀሪውን ደግሞ ከሁለተኛው ቡድን ጋር በመጫወት ነው።

አቶ ፍቃዱ በመግለጫቸው፤ ተቋማቸው ብሄራዊ ቡድኑን ከማገዝ ጀምሮ የኢትዮጵያ እግር ኳስ እንዲያድግ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ መሆኑን ገልጸዋል። በተለይ ወጣት ተጫዋቾች እንዲነቃቁና ምሳሌ የሚሆናቸው የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ወደ ኢትዮጵያ በማስመጣት አርዓያ እንዲሆናቸው የማድረግ ስራ ይከናወናል። ተጫዋቹ ከወጣት ቡድኑ ጋር በሚያደርገው ጨዋታም የቡድኑ አባላት ተነሳሽነትና በእርሱ መንገድ እንዲቀረጹ ይረዳቸዋል። የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫው በመላው ዓለም በሚያደርገው ጉዞ 31 ሃገራትን ያዳርሳል። በኢትዮጵያ በሚኖረው ቆይታም የእግር ኳስ አፍቃሪው አስደሳች ጊዜ እንደሚያሳልፍ አመላክተዋል።

ድርጅታቸውም መርሃ ግብሩን ያዘጋጀው የኢትዮጵያ እግር ኳስ አፍቃሪያን የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫንና የጨዋታውን ኮከብ በቅርበት የማየትና የማግኘት ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግ መሆኑን ጠቁመዋል። ዋንጫውን የማስጎብኘቱ መርሃ ግብር የ13 ዓመታት ታሪክ ያለው ሲሆን፤ በአፍሪካ፣ እስያ እንዲሁም ሰሜንና ደቡብ አሜሪካ አህጉራት በሚገኙ የተለያዩ ሃገራት ይዞራል። የዘንድሮው ጉዞም ‹‹ውዳሴ ለሁሉም የኳስ አፍቃሪያን፤ ውዳሴ ለኳስ ተጠባቢያን›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ዋንጫው በአፍሪካ አራት



ሃገራት ቆይታ ሲኖረው በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ኪንሻሳ፣ በሞዛምቢክ ማፑቶ፣ ኢትዮጵያ አዲስ አበባ እንዲሁም ናይጄሪያ ሌጎስ እና አቡጃ ከተማዎች ላይ ለእይታ ይቀርባል።

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ የተገኙት የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሰለሞን ገብረስላሴ፤ የኢትዮጵያን እግር ኳስ ከማሳደግ ከፌዴሬሽኑ ጋር በአጋርነት ከሚሰሩት አካላት መካከል ሃይንከን ኢትዮጵያ ቀዳሚ መሆኑን ጠቁመዋል። የተጫዋቹ መምጣትም በተለይ በወጣቶች ዘንድ ትልቅ የሆነ መነቃቃትን ይፈጥራል። በመሆኑም የእግር ኳስ ቤተሰቡ በመርሃ ግብሩ ላይ እንዲገኝ ጥሪያቸውን አስተላልፈዋል።

ሆላንዳዊው የቀድሞ የእግር ኳስ ኮከብ ሴዶርፍ ከተጫዋችነቱ ባለፈ በአሰልጣኝነትም ይታወቃል። ተጫዋቹ በሪያል ማድሪድ፣ ኢንተርሚላን እና ኤሲሚላን ክለቦች በተለይ የሚታወቅ ሲሆን፤ በሁለቱ ክለቦች ሶስት የቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫዎችን አንስቷል። የቻምፒዮንስ ሊጉ ምርጥ የመሃል ሜዳ ተጫዋችነት ክብርንም አግኝቷል።

በዚህ መልኩ የአውሮፓ እግር ኳስ ከዋክብትን ወደ ኢትዮጵያ ሲያስመጣ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው አለመሆኑ የተጠቆመ ሲሆን፤ ከዚህ ቀደም በዚህ መርሃ ግብር ብራዚላዊው የባርሴሎና ኮከብ ተጫዋች ሮናልዲኒሆ ጎቹ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከአድናቂዎቹ ጋር በአዲስ አበባ ስታዲየም መገናኘቱ የሚታወስ ነው። በሪያል ማድሪድ እና በቼልሲ ክለቦች የሚታወቀው የቀድሞ የፈረንሳይ ብሄራዊ ቡድን ተጫዋች ክላውድ ማካሌሌም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ፍጻሜ ጨዋታን ከደጋፊዎች ጋር መመልከቱ የሚታወስ ነው።


## በጉምሩክ ኮሚሽን ሞጆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
## የተተው ዕቃዎች የግልፅ ጨረታ ቁጥር ሞ68/2014 ጨረታ ማስታወቂያ

በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አስመጪዎችን በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 አንቀፅ 51፤ ንዑስ አንቀፅ 1 እና በተሻሻለው የጉምሩክ አዋጅ 1160/2011 አንቀፅ 13 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ዕቃቸውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ፈጽመው ባለመውሰዳቸው ዕቃዎቻቸው እንደተተው ተቆጥረዋል። ስለሆነም በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ንብረቶች ስለሚወገዱበት ሥርዓት በአወጣው መመሪያ ቁጥር 167/2012 አንቀጽ 9 መሠረት የተወረሱ ንብረቶችን ማለትም የወፍጮ አሎሎ ፣ ሊፍት፣ማሽን፣ ግራናይት፣ ብረታ ብረት ፣ ባነር እና ሌሎች ዕቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል። በዚህም መሠረት ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለመጫረት የሚፈልጉና ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልፃለን።

1. ተጫራቾች የዕቃዎቹን ዝርዝር ፣ ዓይነት፣ ብዛት ፣ የጨረታ ሠነድ እና መመሪያ መግለጫ እንዲሁም የጨረታ ዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ዘወትር ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 6፡00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡00 እስከ ቀኑ 10፡30 እና ዓርብ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5፡00 ከሰዓት በኋላ ከቀኑ 7፡30 እስከ ቀኑ 10፡30 እንዲሁም ቅዳሜ ከጠዋት 2፡00 እስከ ቀኑ 5፡30 የማይመለስ ብር 100 (አንድ መቶ) በመክፈል ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ገቢ ሂሳቦች ቡድን መውሰድ ይችላሉ።
2. ተጫራቾች በጨረታ ከሚሸጠው ዕቃ ጋር በዘርፉ የፀና ንግድ ፈቃድ ያላቸው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤ 15% የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው ፤ ሆኖም ግምታዊ ዋጋቸው ከብር 500,000.00 በታች የሆኑ ማንኛውንም ዕቃ ለመግዛት የ15% የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ ሳያስፈልግ መወዳደር ይችላሉ።
3. ማንኛውም ተጫራች ለጨረታው ማስከበሪያ የሚሆን የሚጫረትበትን ጠቅላላ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ጨረታ ከመከፈቱ በፊት በቅድሚያ ማስያዝ ይኖርበታል። ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ አሸናፊው እንደታወቀ በ3 (ሶስት) የሥራ ቀናት ውስጥ የሚመለስላቸው ሲሆን አሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፈበት ዋጋ ላይ የሚታሰብላቸው ይሆናል። ተጫራቾች የሚያስይዙት CPO በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥም ETHIOPIAN CUSTOMS COMMISSION MODJO BRANCH OFFICE በሚል ሲሆን የግል ባንክ ከሆነ ከአዲስ አበባ አስተዳደር ቅርንጫፎች ፤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከሆነ ደግሞ ከአዲስ አበባ ፤ አዳማና ሞጆ ቅርንጫፎች መዘጋጀት አለበት። ተሳታፊዎች ዋጋ መሙላት የሚችሉት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተዘጋጅተው ማህተም ያረፈበት ሠነድ ላይ ብቻ መሆን ይኖርበታል።
4. የግልፅ ጨረታ ተሳታፊ ተጫራቾች እያንዳንዱን ዕቃዎች ለመግዛት የሚያቀርቡት የመጫረቻ ዋጋ፤ የሞሉበት ሠነድ፤ በተራ ቁጥር 2 የተገለፁትን ማስረጃዎች ኮፒ እና ያቀረቡት የመጫረቻ ዋጋ 5% ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO በኤንቬሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ8 ተከታታይ ቀናት ጠዋት 4፡45 ሰዓት ድረስ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይቻላል።
5. የጨረታ ሣጥኑ ከታሸገ በኋላ የሚመጡ የመጫረቻ ሰነዶች ተቀባይነት አይኖራቸውም።
6. የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ የወጣበት ቀንን ጨምሮ በ8ኛው የሥራ ቀን ከጠዋቱ 4:45 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ዕለት ጠዋቱ 5፡00 ላይ ተጫራቾቹ ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ በአዘጋጀው ቢሮ ውስጥ ይከፈታል ።
7. ማንኛውም በግልጽ ጨረታ የሚሳተፍ ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ ዋጋ መቀየር ወይንም የሌላ ተጫራቾችን ዋጋ ተንተርሶ ዋጋ አሻሽሎ ማቅረብ አይችልም።
8. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ጨረታውን ለማሸነፍ ሲል መደለያ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ ማንኛውም ተጫራች ከጨረታው ይወገዳል። ጨረታው ከተካሄደ በኋላም ቢሆን ጨረታ አሸናፊው ጨረታውን ያሸነፈው በህገ-ወጥ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ የጨረታው ውጤት ይሰረዛል ።
9. ማንኛውም የጨረታ ሽያጭ የዕቃው አስመጪ ወይም ባለቤት እና ቤተሰብ የነበሩ ሰዎች በጨረታው መሳተፍ አይችሉም።
10. ማንኛውም ተጫራች ጨረታው ከተከፈተ በኋላ እራሱን ከጨረታው ውድድር ማግለል አይቻልም።
11. ማንኛውም ተጫራች የሰጠው የመወዳደሪያ ዋጋ የጨረታው ግምገማ ተጠናቆ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የጨረታውን ውጤት እስከሚያሳውቅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል ።
12. የግልጽ ጨረታው አሸናፊ ጨረታውን ስለማሸነፋቸው ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ በማድረግ ዕቃውን መረከብ አለበት። በ5 (አምስት) ቀናት ውስጥ ገንዘቡ ገቢ ካልተደረገ ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ በተረጋገጠ CPO ያስያዙት ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ይደረጋል። ያሸነፉት ዕቃም በድጋሚ ለጨረታ ሽያጭ ይቀርባል ።
13. በተራ ቁጥር 12 በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የአሸነፉበትን ዕቃ ዋጋ ገቢ አድርጎ ዕቃውን ያላነሳ/ያልተረከበ እንደሆነ ለሚቆይበት ለተጨማሪ ጊዜ የመጋዘን ኪራይ ይከፍላል ። ሆኖም ዕቃው በ2 (ሁለት) ወራት ውስጥ ካልወጣ እንደተተወ ተቆጥሮ በጨረታ ሽያጭ ይወገዳል።
14. አሸናፊው ተጫራች ዕቃዎችን ለመረከብና ለማጓጓዝ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ ራሱ ይሸፍናል ።
15. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ለጨረታ የአቀረበውን ዕቃ ብዛት ለመጨመርም ሆነ ለመቀነስ ሙሉ መብት አለው።
16. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ዕቃዎቹን ለመሸጥ የተሻለ አማራጭ ወይም ዘዴ ከአገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
17. ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቀጥር 022-236-90-94 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ ።

**በገቢዎች ሚኒስቴር ጉምሩክ ኮሚሽን**
**የሞጆ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**